## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

## የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የእንጦጦ ርእሰ አድባራት ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች

በ

ሣምራዊት አረጋዊ

ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

ጥር 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የእንጦጦ ርእሰ አድባራት ደብረ ኃይል  ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች

ለአማርኛ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ

የቀረበ ጥናት


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

በ

ሣምራዊት አረጋዊ

አማካሪ

ዘላለም መሠረት (ዶ/ር)



ጥር 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የእንጦጦ ርእሰ አድባራት ደብረ ኃይል  ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች

በ

ሣምራዊት አረጋዊ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

## የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም:- -------------------------------------- ፊርማ:--------------------

የውስጥ ፈታኝ ስም:- ------------------------------ ፊርማ:--------------------

የውጭ ፈታኝ ስም:- -------------------------------- ፊርማ:-------------------

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህንን ያደረገ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ ይህንን ጥናት ስሠራ ጥናቱን በማረም ላማከሩኝ ለዶክተር ዘላለም መሠረት ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ለጥናቱ መሳካት ገንዘብ፣ ጊዜ፣ ጉልበት፣ መቅረጸ ድምፅ በመስጠት የተለያዩ ሐሳቦችን በማመንጨት ከጎኔ ያልተለየሽኝ ውድ እሕቴ ፍሬሕይወት አረጋዊ ይህ የአንቺም ውጤት ነው፡፡ እንዴት እንደማመሰግንሽ አላውቅም እግዚአብሔር ያሰብሽውን ያሳካልሽ፡፡

የተለያዩ ገንቢ ሐሳቦችን በማንሣት ከጎኔ ላልተለያችሁኝ ጥናቴን ጀምሬ እስከምጨርስ ድረስ በሀሳብና በማንኛውም  መንገድ ያልተለያችሁኝን ጽጌ በዛብህ፣ ሰብለወንጌል ደበበ፣ ምእራፍ ሐዱሽ፣ መታሰቢያ የኔነህ፣ አዜብ ቦጋለ፣ ናትናኤል ሀድጉ፣ ራሄል አረጋዊ፣ ፍስሀ ገብረትንሳኤ፣ ቢንያም አረጋዊ እና ሊያ አበበ በጠቅላላ ልባዊ ምስጋናዬን ላቅርብላችሁ እወዳለሁ፡፡

የተለያዩ የሚያስፈልገኝን መረጃ እና መጻሕፍት በመስጠት ቤተሰባዊ ፍቅር ያሳያችሁኝ ዲያቆን ዮሐንስ ወልደጊዮርጊስ፣ ዲያቆን ኃይሉ ጌታነህ፣ አቶ መኩሪያ ሣህሉ፣ ርእሰ ደብር አጋፋሪ ሰሎሞን ጌታነህ፣ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ መልአከ ኃይል ቆሞስ አባ ሳሙኤል አስፋው፣ አባ ወልደጊዮርጊስ ገብሬ፣ሊቀ ህሩያን ቃለፅድቅ ሀይሌ፣ ፣በትረ ትጉሀን ቀሲስ ክንፈሚካኤል ጥላሁን፣ዲያቆን ሳሙኤል አስረስ ፣ቄስ ባየ ሲሻዉ፣ ቄስ በለጠ ምስጋናዉ፣ አቶ ጥሩነህ ሀይሉ እና አቶ ተክሉ ማሞ ጊዜያችሁን ሠውታችሁ ስለረዳችሁኝ  እግዚአብሔር ይስጥልኝ ለማለት እወዳለሁ፡፡

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


*ምስጋና* ........................................................................ *i*

አጠቃሎ.......................................................................... viii

*የፎቶግራፍ ማውጫ* ............................................................... *v*

*ምዕራፍ አንድ* ................................................................... *1*

*1. መግቢያ* ......................................................................... *1*

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................ 1

1.2 የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት ........................................................ 2

1.3 የምርምር ጥያቄዎች ............................................................. 2

1.4 የጥናቱ ዓላማ ...................................................................... 3

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ................................................................... 3

1.6 የጥናቱ ወሰን ....................................................................... 4

1.7 የጥናቱ ዘዴ .......................................................................... 4

1.7.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ........................................................ 4

1.7.2 የመረጃ አተናተን ዘዴ ......................................................... 5

1.8 ቅድመ ዝግጅት፣መስክ ቆይታ፣ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች.....6

*ምዕራፍ ሁለት* ................................................................... *9*

*2. ክለሳ ድርሳናት*................................................................. *9*

2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት ............................................................. 9

2.1.1.ተረክ (Narrative).................................................................. 9

2.1.2. ቁሣዊ ባህል (Material Culture)............................................ 16

2.1.3.የቁሳዊ ባህል አተናተን ሂደቶች ............................................... 18

2.2.ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ................................................................. 19

2.2.1. ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (Functional Approach) ........ 19
2.3. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ........ 21
ምዕራፍ ሦስት ........ 27
*3.አካባቢያዊ ዳራ ........ 27*
3.1. የእንጦጦ አጠቃላይ ገጽታ ........ 27
3.2. የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር ........ 27
3.3. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚከበሩ ዐበይት በዓላት ........ 29
*ምዕራፍ አራት ........ 32*
*4. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮች ትንተና ........ 32*
4.1. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮች ........ 32
4.2. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ክብር ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ተረኮች ........ 36
4.3. ከራእይ ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ........ 38
4.4. ከተአምር ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ........ 41
4.5. ከፈዉስ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ........ 45
4.6. የታቦቱ አመጣጥ እና ከእንጦጦ ወደ መርካቶ ቤተክርስቲያን መሸኘት ........ 50
4.7. የነገስታቱ እና የተለያዩ መንግሥታት ድርሻ በቤተክርስቲያን ውስጥ ........ 54
4.8. የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ያፈራቸው ሰዎች ........ 56
*ምዕራፍ አምስት*
5. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ሙዚየም የሚገኙ እና ወደ መርካቶ ቅዱስ ራጉኤል የተዛወሩ ቁሳዊ ባህሎች ትንተና ........ 61
5.1. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎች ........ 61
5.1.1 የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን የህንፃ አሰራር ........ 61

5.1.2 የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ዉስጣዊ ገጽታ........................................................................................64

5.2. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ሙዚየም ውስጥ የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎች........................................................................................ 78

5.3. ከእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ወደ መርካቶ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን የተዘዋወሩ ቁሳዊ ባህሎች ........................................................ 93

*ምዕራፍ ስድስት ........................................................................................ 102*

*6.ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ........................................................................ 102*

6.1. ማጠቃለያ ........................................................................................ 102

6.2. የመፍትሄ ሀሳቦች ................................................................................ 104

*ዋቢ ጽሁፎች ........................................................................................ 105*

*አባሪዎች........................................................................................ 108*

*1. ለመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገሉ ጥያቄዎች................................................ 109*

*2. የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ ................................................................ 1*

*3. የመጀመርያዎቹ የደብሩ ካህናት ........................................................................ 3*

*4. በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ስዕላት........................................................ 5*

*5. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተ ክርስቲያንና ሙዚየም ውስጥ የሚገኙ ቁሶች....... 7*

*6. በመርካቶ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ መጽሐፍቶች ..................................... 9*

*7. አጥኚዋ በመጠየቅ ላይ እና የጥምቀት በዓል አከባበር ስነ ስርዓት.................................. 10*

## ፎቶግራፍ ማውጫ


ምስል 1 ፡ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚከበሩ ዐበይት በዓላት ምስል.........31

ምስል 2፡ አጥኚዋ ከቤተክርስቲያኑ መርጌታ ከርእሰ ደብር አጋፋሪ ሰሎሞን ጋር.................38

ምስል 3፡ አጥኚዋ መምህር ወልደጊዮርጊስ ገብሬ ከተባሉ የቀድሞ የቤተክርስቲያኑ የአብነት መምህር ጋር........................................................................................411

ምስል 4፡ ተአምር የሰራው ድርሳነ ራጉኤል..................................................................433

ምስል 5 ፡ በቤተክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ የሚገኝ አነስተኛ ጉድጓድ....................................466

ምስል 6፡ ጠበል ቤት............................................................................................48

ምስል 7፡ የንብ ቀፎ.............................................................................................48

ምስል 8፡ የታቦት ማደርያ ድንኳን    የድንኳኑ ውስጣዊ ክፍል       የድንኳን መወጠሪያ.....50

ምስል 9 የጸሐፊ ትእዛዝ ገብረስላሴ እና የልጃቸው እማሆይ ሐመልማል ገብረስላሴ መቃብር58

ምስል 10፡ የቀኛዝማች ተስፋ ገብረስላሴ መቃብር ላይ የተሰራ ወመዘክር...........................60

ምስል 11፡ የቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ሕንፃ ቤተክርስቲያን..............................................64

ምስል 12፡ ጥንታዊ ቅዱስ ራጉኤል ምስል.......................................................................66

ምስል 13፡  ቅዱስ ራጉኤል ለዐፄ ምኒልክ በትረ መንግሥት ሲሰጥ የሚያሳይ ምስል........677

ምስል 14፡ የነቢዩ ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ሲያርግ እና ነቢዩ ኤልሳእ ምስል.......................68

ምስል 15፡ ኮርኒስ................................................................................................68

ምስል 16፡ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የሚገኙት መሰላሎች.................................................69

ምስል 17 ፡ የዋሻው ውጫዊ ገጽታ ..........................................................................71

ምስል 18፡ ውስጣዊ ገጽታ .......................................................................71

ምስል 19፡ አጥኚዋ ከርእሰ ደብር አጋፋሪ ሰለሞን ጌታነህ ጋር........................................72

ምስል 20፡ ስእለ ማርያምና መንበር...........................................................................73

ምስል 21፡ ከቤተክርስቲያኑ በስተሰሜን ምዕራብ ያለ ዋሻ................................................74

ምስል 22፡ የመላእከ ኃይል ተድላ ወልደ ፃዲቅ ዋሻ........................................................75

ምስል 23፡ የአብነት ትምህርት ቤት ........ 766
ምስል 24፡ በቤተክርስቲያኑ ጊቢ ውስጥ የሚገኙ አጸዶች ........ 77
ምስል 25፡ ዝክር ቤት እና ፉካ ........ 78
ምስል 26፡ በቤተክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ የሚገኝ ሙዚየም ........ 80
ምስል 27፡ የካህናት፣ የዲያቆናት፣ ሚኒስቲሮች፣ አጋፋሪዎችና የቤተመንግስት ሰራተኞች አልባሳት ........ 81
ምስል 28፡ የዐፄ ምኒልክ ካባ ........ 82
ምስል 29፡ የተለያዩ ከእንጨት፣ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሐስ የተሰሩ ጥንታዊ መስቀሎች ........ 82
ምስል 30፡ ማሕተም ........ 83
ምስል 31፡ መጥረቢያ ........ 83
ምስል 32፡ ፅዋዎች ........ 84
ምስል 33፡ መጻሕፍት ........ 855
ምስል 34፡ ባንዲራ እና ነጭ ድባብ ........ 86
ምስል 35፡ የቆዳ ሳጥን ........ 866
ምስል 36፡ የእቴጌ ጣይቱ አልጋ ........ 877
ምስል 37፡ ከቀንድ ከቀርክሀ የተሰሩ የጠጅ እና የጠላ መጠጫዎች ........ 877
ምስል 38፡ ከበሮ ........ 88
ምስል 39 ፡ ጥላዎች ........ 88
ምስል 40፡ ጋኖች ........ 89
ምስል 41፡ የፊት መስተዋት ........ 89
ምስል 42፡ አገልግል ........ 90
ምስል 43፡ የቅዱስ ራጉኤል ታቦት ድባብ ........ 90
ምስል 44፡ የመኪኖንት ለምዶች ........ 91
ምስል 45፡ የእጅ መታጠቢያ ጆግ እና ሰሀን ........ 91

## *አጠቃሎ*

*የዚህ ጥናት ትኩረት በእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን በዙሪያው የሚነገሩትን ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች በመመርመርና በመተንተን ለማኅበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳና አገልግሎት ማሳየት ነው። ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች በቃለመጠይቅ እና በምከልታ ተሰብስበዋል፤ የተሠበሰቡት መረጃዎችም በቪዲዮ ካሜራ፣ በካሜራ፣ በመቅረጸ ድምፅ እና በማስታወሻ ደብተር ተይዘዋል። መረጃዎቹንም በተግባራዊ፣ በተረክ እና በቁሳዊ ባህል ንድፈ ሐሳብ ላይ በመመሥረት ተተንትነዋል። ከጥናቱ ጋራ ተያያዥነት ያላቸው ዘጠኝ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፎች ተቃኝቷል። የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደተመሠረተ የሚገልፁ ፣የቦታዉን ጥንታዊነት የሚዘክሩ፣ ክብር ከፍ ከፍ የሚያደርጉ፣ ከራእይ ጋራ ተያይዞ የሚነገሩ፣ ከተዓምር ጋራ ተያይዘዉ የሚነገሩ፣ ከፈውስ ጋር ተየይዘው የሚነገሩ ተረኮች በሚሉ ርእሶች ቀርበዋል። ተረኮቹ ስለስፍራው ታላቅነት የማስተማር ተግባር አላቸው። በተጨማሪም በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ሙዝየም የተሰበሰቡ እና ወደ መርካቶ ቅዱስ ራጉኤል የተዘዋወሩት ቁሳዊ ባህሎች ትንተና፣ አገልግሎት፣ በማን እንደተበረከቱ፣ የመሥራቹን ቅድስና የሚያወሡ፣ የቤተክርስቲያኗን ጥንታዊነት፣ ታሪካዊነትና ቅድስና  የማጉላት ተግባር የሚገልጹ መኾናቸውን የጥናቱ ዉጤት ያመለክታል ። በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች የጥበብ መገለጫ፣ የዘመን መንፈስ መፈተሻ፣ ማኅበረሰቡን በእምነታቸው ለማጽናት፣ ታሪካዊነቱን ለመዘከር፣ የአከባቢያቸውን እድገት፣ እንዲሁም የእምነቱ ተከታዮች ኾኑ ሌሎች ታዋቂ እና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያኑ እንዲመጡ በማድረግ ሕግና ሥርዓቱን እንዲጠብቁ የማገዝ ፋይዳ አላቸው።*




ምንጭ፡ ETHIO GIS & Google EARTH, 2012

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ተረኮች ማጥናት የማኅበረሠቡን ሥነ ልቡናዊ እና ማኅበረሰባዊ ማንነት ለመረዳት ያስችላል። እምነቶች ደግሞ መሠረታቸውን የሚያጸኑት በተረኮቻቸውና በቁሶቻቸው ነው። ይህ ጥናት የተካኼደውም በእንጦጦ ርእሰ አድባራት ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች በመሰብሰብና በመተንተን ፋይዳቸውን ለማሳየት ነው።

ይህ ጥናት በስድስት ምዕራፎች ተከፍሎ ቀርቧል። በመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሣሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ፣ ቅድመ ዝግጅት፣መስክ ቆይታ፣ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ተመልክተዋል።

በሁለተኛው ምዕራፍ ተረክና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ፅንሰ ሐሳቦች እና ንድፈ ሀሳብ ከጥናቱ ጋራ ተያያዥነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች ተዳሠዋል። ሦስተኛው ምዕራፍ የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን አካባቢያዊ ዳራ የቤተክርስቲያኑ አስተዳደራዊ መዋቅርና መተዳደሪያ፣ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የሚከበሩ በዓላት የቀረቡበት ነው። ምዕራፍ አራት ከመስክ የተሰበሰቡ በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮች ተተንትነዋል። በምዕራፍ ዐምስት በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ሙዚየም የተሰበሰቡ እና ወደ መርካቶ ቅዱስ ራጉኤል የተዛወሩ ቁሳዊ ባህሎች ተተንትነዋል። በምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ፣ የይሁንታ ሀሳቦች፣ ዋቢ ጽሑፎችና አባሪ ቀርበዋል።

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎችን በማበርከት በኩል ደግሞ የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ድርሻ አለው ። ከዚህም ባሻገር በቤተክርስቲያኑ ተፈጸመዋል ተብለው የሚነገሩት ቃላዊ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች በቤተክርስቲያኑ ለሚኖሩት እና ተረኮቹን ለሚሰሙት የእምነቱ ተከታዮች ደግሞ የራሳቸው የሆነ ፋይዳ ይኖራቸዋል።

Dorson “ኀይማኖታዊ ፎክሎርን በዘውግ ከፋፍሎ ማጥናት አስቸጋሪ ነው፤ ኀይማኖታዊ ፎክሎርን በዘውግ ስንከፋፍል የሃይማኖት ዋና ጉዳይ የሆነው እምነት ዕንቅፋት ይፈጥራል።” (1972፣219) በማለት ገልፀዋል። ኀይማኖታዊ ፎክሎር ኃይማኖታዊ እና ከኃይማኖቱ ውጪ ያሉ ልማዳዊ ጉዳዮችን የምንመረምርበት በመሆኑም እንደ እምነት እና ሌሎች ትውፊታዊ

ጉዳዮች ያሉት በኹሉም ዘውጎች ሊንጸባረቁ ስለሚችሉ ክፍፍሉን አስቸጋሪ ያደርገዋል (Danielson, 1986: 52-53)::

በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ላይ በማተኮር የተሠራው ይህ ጥናት ከቤተክርስቲያን አመሠራረት ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና ቁሣዊ ባህልን ተመልክቷል፡፡ የእምነቱ ተከታዮች በተረኮቹና በቁሳዊ ባህሎቹ አማካይነት ከየት መጥነቱን፣ ማንነቱን፣ እምነቱን ባህሉን እና አስተሳሰቡን እንደሚገልጽ ከጥናቱ ማወቅ ይቻላል፡፡

የተለያዩ የታሪክ ባለሙያዎች፣ የመንፈሳዊ ትምህርት ልሂቃን፣ የፎክሎር አጥኚዎች ወዘተ... በአገሪቱ የሚገኙ ኀይማኖቶችን በተለይም ክርስትና፣ እስልምና እና የተለያዩ ሀገር በቀል እምነቶችን በየመስካቸው አጥንተዋል፡፡ የፎክሎር ተማሪዎች የተለያዩ ገዳማትንና አድባራትን ቁሳዊ ባህል፣ የበዓል አከባበር ክዋኔ፣ የገዳማት አመሠራረትና ከገዳማቱ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና የገዳም ሥርዓቶች ላይ ምርምር አካኺደዋል፡፡ እንዲሁም የመዝሙር ግጥሞች፣ የቆሎ ትምህርት ፎክሎራዊ ገጽታዎች፣ መንዙማዎች ወዘተ... ተጠንተዋል፡፡

ነገር ግን እስከአሁን እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ተሰብስበው ጥናት አልተካኼደባቸውም፡፡ በመኾኑም ይህንን ክፍተት በማየቴ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች አጥንቻለሁ፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማድረግ ካነሣሡኝ ምክንያቶች መካከል በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ የተለያዩ አጫጭር በራሪ ፅኁፎች እና መጽሄቶች የተፃፉ ቢኖሩም በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ላይ በቀጥታ የተደረገ ጥናት አለማግኘቴ ፣ ቤተክርስቲያኑን በጎበኘሁበት ወቅት ጥንታዊነቱና ከቤተክርስቲያኑ ጋር ተያይዘው የሚነገሩትን ተረኮች መስማቴ፣ አማንያኑ የሚገለገሉባቸውና ቅርስ ሆነው የተቀመጡ ቁሳዊ ባህሎች በማየቴ እንዲሁም ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለማሳየት ያለኝ ፍላጎት ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸዉ፡፡

## 1.3 የምርምር ጥያቄዎች

- ✓ የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን እንዴት ተመሠረተ?
- ✓ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ከቤተክርስቲያኑ ጋር ያላቸው ቁርኝት ምን ይመስላል?

- ✓ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚነገሩት ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ለእምነቱ ተከታዮች ምን ፋይዳ አላቸው?
- ✓ የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ምን ምን ናቸዉ?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን አመሠራረት ጋራ ተያያዥነት ያላቸው ቃላዊ ተረኮች እና በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የሚገኙት ቁሳዊ ባህሎችን መተንተን ነዉ፡፡ ይህን ዋና አላማ ለማሳካት የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖራሉ ፡፡

- ✓ የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ሀይማኖታዊ አስተምህሮቻቸውን እና ተረካቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ  ለማስተላለፍ እንዴት እንደተገለገሉበት ማሳየት
- ✓ በቤተክርስቲያኑ ከሚነገሩ ተረኮች ጋር ተያይዘው የሚጠቀሱ ቁሳዊ ባህሎችን መተንተን
- ✓ ቤተክርስቲያኑን እና የአካባቢውን ማኅበረሰብ ትስስር በተረኮቹ አማካኝነት መመርመር ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ላይ መደረጉ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፤

- ✓ በተለያየ ዘርፍ ምርምር ለማካኼድ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች መረጃን ለመስጠት ይጠቅማል፤
- ✓ በተረኮቹና በቁሶቹ መካከል ያለውን ተያያዥነት በማሳየት ረገድ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል፤
- ✓ ደብዛቸው በመጥፋት ላይ የሚገኙትን ተረኮች እና ቁሣዊ ባህሎችን በመሰብሰብ በጽሑፍ ለማስቀመጥ ፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን አመሠራረት ታሪክ ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን ለቤተክርስቲያኑ እና ለአማንያኑ ያላቸውን ፋይዳ በመመርመር ላይ ትኩረት በማድረግ ይወሰናል፡፡ ቤተክርስቲያኑን በማስመልከት በቦታው በርካታ ተረኮች ይነገራሉ፡፡ ቁሳዊ ባህል ለቤተክርስቲያን የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ምን ይመስላል? በሚለው ጉዳይ ላይ ትኩረት በማድረግ መረጃዎቹንም በቤተክርስቲያን ውስጥ ከሚኖሩ አማንያን አባቶች እና ስለ ቤተክርስቲያኑ ከሚያውቁ የአከባቢው ነዋሪዎች ሰብስቢያለሁ፡፡

ይህ ጥናት በቃል ተረኮች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ በቤተክርስቲያኑ አመሠራረት ታሪክ ውስጥ ስለመሥራቾቹ የቅድስና እና የተጋድሎ ህይወት እንዲሁም በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ተፈጸመ የሚባሉ ፈውስ፣ ንግር፣ክብርን ከፍ ከፍ የሚያደርጉ፣ራእይ፣ ትንቢት ተአምራትና ስለሚከተልዋቸው አስተምህሮዎች የሚነገሩ ተረኮችን አገልግሎት ይመለከታል ፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

### 1.7.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

የቃለ መጠይቅ ዘዴ ሙሉ መረጃ ሊሰጥ ከሚችል እና ከሚታመንበት የመረጃ አቀባይ በጥያቄና መልስ ስለ ክዋኔው የተፈጠሩትን ኹነቶች የምንጠይቅበት ዘዴ ነው፡፡ (Goldstein, 1964: 77-78)፡፡

ለቃለመጠይቅ ዘዴ የሚዘጋጁ ጥያቄዎች የተለያየ ቴክኒክ አላቸው ክፍት ጥያቄዎች እና ዝግ ጥያቄዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ክፍት ጥያቄዎች የሚባሉት ተጠያቂዎች ነፃ ሆነው መረጃ የሚሠጡባቸው ቀድመው ያልተዘጋጁ ነገር ግን በቃለምልልሱ ወቅት የሚነሱ ሁነቶች የሚጠሯቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ዝግ ጥያቄዎች ደግሞ ቁርጥ ያለ መልስ ለማግኘት የሚጠየቁ ጥያቄዎች ናቸው (ፍቃደ አዘዘ፣ 1991፣101)

በዚህም መሠረት ለጥናቴ የሚጠቅመኝን መረጃ ለማግኘት ወደ መስክ ከመሔዴ በፊት ለመነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎች አዘጋጅቻለሁ፡፡ ነገር ግን መስክ ላይ ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር እንደነበረኝ ግንኙነት እና እንዳገኘሁት መረጃ ክፍት ጥያቄዎችን በማቅረብ መረጃዋን ለመሠብሠብ ችያለሁ፡
:

በምልከታ እና ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሠብሠብያ የሚሠበሰቡ የመስክ መረጃዎች በቪድዮና ፎቶ ካሜራ እንዲሁም መቅረፀ ድምፅን በመሳሰሉ አጋዥ መሣሪያዎች መታገዝ አለባቸው (Goldstein, 1964: 97-99)። ስለዚህ እኔም መረጃዎቼን በመሰብሰብ በምልከታ ያገኘኃቸውን ለጥናቴ የሚያስፈልጉኝን በምስል አስቀርቻለሁ። በቃለመጠይቅ ወቅት እንደ አስፈላጊነቱ ያደረኳቸውን ቃለመጠይቆች ሁሉ በመቅረፀ ድምፅ ቀርጫለው።

መረጃ የሠበሠብኩት ከቀዳማይ እና ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ነው። ቀዳማይ የመረጃ ምንጮቼ በቤተክርስቲያን የሚኖሩ አባቶች፣ ስለ በቤተክርስቲያኑ የሚያውቁ የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው። ሌላው የመረጃ ምንጭ ደግሞ ለጥናቴ የሚበጁ ንድፈሃሳቦች ፣ ፅንሠ ሀሳቦች ፣ በራሪ ጽሁፎች፣ መጽሄቶች ፣ የተለያዩ መፅሕፍት እና ልዩ ልዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ናቸው።

ለፎክሎር ጥናት የመስክ መረጃዎች በምልከታ (observation) እና ቃለመጠይቅ (interview) ሊሠበሠቡ ይችላሉ (Goldstein, 1964: 77)። ምልከታ (observation) በመስክ ስፍራው በተደጋጋሚ ተገኝቼ የሚከወነውን፣ የሚታየውን እና የተመለከትኩትን ነገር በመመዝገብ በቦታው ላልተገኘና የመመልከት እድሉን ላላገኘ ሰው በጽሁፍ ያስቃኘሁበት ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ በአግባቡ ከተተገበረ ከሌሎች የመረጃ መሠብሠቢያ ዘዴዎች በተሻለ ተጨባጭ መረጃን ለመሠብሠብ የሚያስችል ነው። በምልከታ ወቅት ከአይን እይታ በተጨማሪ ሁሉንም የስሜት ህዋሳቶቻችንን በሙሉ በማንቃት እና በማጣመር ስለተከወነው ነገርና ስለከዋኙ ወይም በአጠቃላይ ስለክወና ዓውዱ የተሻለ መረጃ ለማግኘት ያስችላል (Goldstein, 1964: 77)። በዚህ ጥናት በምልከታ ወቅት ቦታው ላይ በመገኘት ፣ በመመልከት እና በመጠየቅ መረጃ ሰብስቤያለሁ።

### 1.7.2 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በምልከታ እና በቃለመጠይቅ የመረጃ መሠብሠቢያ ዘዴዎች ሰብስቢያለሁ። በዚህ ጥናት በበቤተክርስቲያኑ ውስጥ የሚነገሩት ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ለቤተክርስቲያኑ ሥርአት እና ለቤተክርስቲያኑ ህይወት ያላቸውን ፋይዳ ለማሣየት ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ /functional theory/ የተረክ ንድፈ ሀሳብን (oral narrative theory) እና ቁሳዊ ባህል (material culture) ተጠቅሚያለሁ።

## 1.8 ቅድመ ዝግጅት፣መስክ ቆይታ፣ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

### ቅድመ ዝግጅት

በዚህ ክፍል ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ሞክሬያለሁ፡ በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮችና ቁሣዊ ባህሎች ለማጥናት በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ የተፃፉ የተለያዩ መፅሄቶች፣በራሪ ፅሁፎች፣መዝገበ ቃላት፣ ከቤተክርስቲያን፣ ከቤተመፃሕፍት፣ ከኢንተርኔትና ከግለሰቦች እጅ አሰባስቢያለሁ፡፡ እንዲሁም ከጥናቱ ጋር ተያዥነት ያላቸው የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች ሰብስቤ አንብቤያለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በመስክ ቆይታ ወቅት መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉና በቆይታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ግዥና ዝግጅት አድርጌያለሁ፡፡

### የመስክ ቆይታ

ስለቃላዊ ተረክ ቁሣዊ ባህል እና ስለተግባራዊ ንድፈሀሳብ በተለያዩ ገዳማት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ላይ የተሰሩትን ጥናቶች እና ስለሚጠናው አካባቢ የተጻፉ ጽሑፎችን ከቤተመጻሕፍት አንብቢያለሁ፡፡ በቀን 04/12/2012 ዓ.ም ወደ እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን በመሄድ የቤተክርስትያኑ ሃላፊዎች በማግኘት በቤተክርስትያኑ ቃላዊ ተረክ እና ቁሳዊ ባህል ላይ ጥናታዊ ጽሁፌን ላከናውን እንደሆነ ህጋዊ ደብዳቤ ካመጣሁ እንደሚተባበሩኝ ነግረውኝ ተመልሻለሁ፡፡ በዚህም መሠረት ከትምህርት ክፍሉ ለደብረ ሀይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን የትብብር ደብዳቤ ተሰጥቶኛል፡፡

ጥናቴን ሳዘጋጅ ለጥናቴ የሚጠቅሙኝን ጽሑፎች ሳነብ እና ለመስክ የሚያስፈልጉኝን ቁሳቁሶች ሳሟላና ቅድመ ዝግጅቴን ሳደርግ ቆየሁ፡፡ የተፃፈልኝን የትብብር ደብዳቤ ይዤ የቤተክርስትያኑ ጽኀፈት ቤት በመሄድ የቤተክርስቲያኑ ሙዝየም አስጎብኚ አግኝቼ የመጣሁበትን አላማ ተናግሬ ህጋዊ ደብዳቤውን ሰጠኃቸው፡፡ ከሁለት ቀን በኂላ እንድመለስ ቀጠሮ ሰጡኝ፡፡ በቀጠሮም መሠረት ተገኝቼ ፍቃድ እንዳገኘሁና ጥናቴን መጀመር እንደምችል ተነገረኝ፡፡ ከዛም መረጃ አቀባዮቼን ወደ መምረጥ ገባሁ፡፡ ስለ ቤተክርስትያኑ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉትን አካላት እንዲጠቁሙኝ በመንገር ከአካባቢው ማሕበረሰብ ደግሞ ስለ ቤተክርስትያኑ የበለጠ መረጃ የሚሰጡኝን ለማወቅ መጠየቅ ጀመርኩኝ፡፡ በዚህ መሠረት በመጀመርያ ያገኘሁት ዲያቆን ዮሀንስ ወልደጊዮርጊስ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ስለነበረ የመጣሁበትን ጉዳይ አስረድቼ አስፈላጊውን መረጃ ሊሰጠኝ ተነጋግረን ተለያየን፡፡ በመቀጠልም ጥያቄዎቼን መከለስ እና ስለ

ቤተክርስትያኑ ከሰማኃቸው መረጃዎች ጋር አዛምጄ አስተካከልኩ። በጠዋት ወደ ቤተክርስትያኑ በማቅናት መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ ሰዎች ዲያቆን ዮሃንስ ወልደጊዮርጊስ እንዳገኝ አመቻቸልኝ። እነዚህ መረጃ እንዲሰጡኝ የተመረጡበትም ምክንያት በቤተክርስትያኑ ውስጥ ካላቸው ኃላፊነትና የረጅም ጊዜ ቆይታ እና እውቀት አንጻር ነው።

በመስክ ቆይታዬ ያገኘኋቸው መረጃ አቀባዮቼ የቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ መልአከ ኃይል ቆሞስ አባ ሳሙኤል አስፋው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ርእሰ አድባራት ወገዳማት እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ፣ ዲያቆን ዮሃንስ ወልደጊዮርጊስ የቤተክርስቲያኑ ሙዚየም ዋና አስጎብኚ፣ ዲያቆን ሀይሉ ጌታነህ የቤተክርስቲያኑ ሙዚየም ምክትል አስጎብኚ፣ ርእሰ ደብር አጋፋሪ ሰለሞን ጌታነህ የቤተክርስቲያኑ መርጌታ ፣ አቶ መኩሪያ ሳህሉ የቤተክርስቲኑ አገልጋይ፣ ከአከባቢው ነዋሪዎች ደግሞ መምህር ወልደጊዮርጊስ ገብሬ የቀድሞ የአብነት ትምህርት ክፍል ኃላፊ ፣ ዲያቆን ሳሙኤል አስረስ የቤተክርስቲያኑ መምህር፣ በትረ ትጉኃን ቀሲስ ክንፈሚካኤል ጥላሁን የዕቃ ቤት ሀላፊ፣ ቄስ በለጠ ምስጋናው የቤተክርስቲያኑ አገልጋይ እና የኢትዮ ቴሌኮም ሰራተኛ ፣ አቶ ጥሩነህ ሀይሉ እና አቶ ተክሉ ማሞ የኢትዮ ቴሌኮም ሰራተኞች፣ አባ ባዬ ሲሻው የመርካቶ በደብረኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ሙዚየም ጠባቂ፣ ምዕራፈ ስብሃት በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን የቀድሞ አገልጋይ ወይም የመፅሐፍ መምህር በአሁኑ ግዜ የአስኮ ቅዱስ ገብርኤል አገልጋይ፣ ሊቀ ጉሩያን ቃለ ጽድቅ ሀይሌ በእንጦጦ ማርያም መምህር። እነዚህ ሁሉ መረጃ አቀባዮቼ ጋር በመሄድ በቃለመጠይቅ እና በምልከታ ፎቶ በማንሳት፣ ስለ ቤተክርስቲያኑ ፣ ስለ ዋሻው ፣ስለ ሙዝየሙ ፣ስለ ጸበል ቤቱ ፣ስለ ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች እንዲሁም ለጥናቱ የሚስፈልጉኝን የተለያዩ መረጃዎች እንዲሁም ለጥናቱ የሚጠቅሙኝን አንዳንድ ጠቃሚ መፃህፍትን፣ መጽሔቶች፣ በራሪ ወረቀቶች እና ጋዜጦች በመስጠትና ለጠየቅኳቸው ጥያቄዎች ትህትና በተሞላበት መንገድ በመመለስ አስፈላጊውን መረጃ እንዳገኝ ተባብረውኛል።

መረጃዎቼን ሳገላብጥ ለሚፈጠሩብኝ ጥያቄዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተገናኘሁ የመረጃዎቼን ክፍተቶች እየሞላሁ ቆየሁ። ከዚህ በኋላ ከሰበሰብኳቸው ተረኮችና እና ቁሳዊ ባህሎች በመነሳት ዳግም ምልከታ አደረኩኝ። በአጠቃላይ በመስክ ቆይታዬ ያገኝኃቸው ሰዎች የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች በመስጠት ቆይታዬ የተሳካ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተውልኛል።

### ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄዎች

በመስክ ቆይታ ወቅት የተለያዩ ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡ በመስክ ወቅት የገጠመኝ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እንዳለ ሆኖ የአካዲሚውና የማኅበረሰቡ መራራቅ ዋነኛው ነው፡፡ በአካዲሚዉ ውስጥ “ተረክ” የሚለው ስያሜ “narrative” የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል በመተካት ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ አገልግሎት ላይ ውሏል (ዮናስ አዴማሱ፣ 1992፣ 84)፡፡

ነገር ግን ይህ ቃል ጥናቴን በሰራሁበት ማኅበረሰብ ዘንድ አሁንም እንዲህ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ይህም በአካዲሚው እና ማኅበረሰቡ መካከል ያለውን ክፍተት የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን የገጠመኝን በስያሜ ላይ የጋራ ግንዛቤ አለመኖር ለመፍታት የማኅበረሰቡን ዘይቤ በመከተሌ “ታሪክ” የሚለውን ስያሜ በመጠቀም ተረኮችን መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

በተጨማሪም በአካባቢው ተወልደው ያደጉ እና ስለእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ብዙ መረጃ የሚያውቁ የእድሜ ባለፀጋ አባት ርእሰ ደብር ደብረህሊና ግርማ የተባሉ ግለሰብ ጋር ተገናኝተን በቀጠሮ ከተለያየን በኋላ በቀጠሮም ጊዜ ስሄድ በህመም ምክንያት በማረፋቸዉ ይህንንም ክፍተት ለመሙላት አሁን ቤተክርስቲያኑ ላይ በተለያየ የስራ ዘርፍ የሚያገለግሉ አባቶች፣ ዲያቆናት፣ በአከባቢው ተወልደው ያደጉ ነዋሪዎች እንዲሁም ከዚህ በፊት እንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ያገለግሉ የነበሩ አሁን በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የሚሠሩ ሰዎች ጋር ካሉበት ቦታ ድረስ በመሄድ መረጃ ሰብስቤአለው፡፡ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ይሆኑኛል ብየ ከያዝኳቸው ውስጥ አንዱ ለትምህርት ከከተማ ወጥተው በመቆየታቸው እና ሰነዶች በቤተመጻህፍት ተቀምጠው አገልግሎት መስጠት ሲገባቸው በግል መኖሪያ ቤት ውስጥ በመሆናቸው ለማግኘት ተቸግሬ ነበር፡፡ ሆኖም ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች እና ሌሎች ጥቃቅን ችግሮችን በመፍታት  ለጥናቱ የሚጠቅም መረጃዎችን ለማግኘት ችያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳናት

### 2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት

#### 2.1.1. ተረክ (Narrative)

የተረክን ምንነት በማስመልከት የተለያዩ ምሁራን ሀሳባቸውን አስፍረዋል፡፡

ተረክ የሰው ልጅ የፅሁፍ ጥበብ ከመጀመሩ በፊት ጀምሮ የነበረ፣ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ ስለ አለም አፈጣጠር፣ ስለነገሮች አመጣጥ፣ ስለእምነቱ፣ ስለባህሉ እና ስለማንነቱ ለመግለፅ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡ ተረክ ከሰው ልጅ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው፣ በማንኛውም ቡድን ወይም ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኝ፣ ዘመንና ባህል የሚሻገር፣ በሁሉም የኪነጥበብ ቅርጾች የተለያዩ ጉዳዮችን ማስተላለፍ የሚችል፣ በቃል ወይም በፅሁፍ፣ በቅርጽ ወይም በስዕል፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ፣ በዝርው ወይም በግጥም ቅርፅ ሊቀርብ የሚችል በርካታ የማኅበረሰቡን ሁነቶች የሚያሳይ መግባቢያ መንገድ ነው (Barthes, 1975: 237, Degh, 1972: 54) ፡፡

ተረክ ታሪኩን፣ ትረካውን፣ ታሪኩ የሚቀርብበትን ሁኔታና መንገድ ሁሉ ጠቅልሎ የማይዝ ፅንሠ ሀሳብ ነው፡፡ በሠፊ አገባቡ ተረክ በቃል አልያም በፅሑፍ ሲቀርብ በግጥም ወይም በዝርው ሊተረክ ይችላል፡፡ ከዚያም አልፎ ሊዘፈን ሊተወን ሊደነስ ሊሳል ሊቀረፅ በተለያዩ መንገዶች ሊከወን የሚችልም ቅርፅ ነው (ቴዎድሮስ 2000፡259-260) ፡፡

ተረክ የግለሰብን ወይም የአንድን ማህበረሰብ ልምድና ገጠመኝ በወጉ የተደራጁ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም አንድ የተከሰተ ሁነትን ማሳያ ወይም ማቅረቢያ መንገድ ነው ፡፡ ተረክ ሁነቶች እና ድርጊቶችን ማሳያ ከሆነ አንድ ማኅበረሰብ ወይም ግለሰብ ገጠመኙን፣ ባህሉን፣ ልማዱን፣ እምነቱን እና አስተሳሰቡን ያንፀባርቅበታል፡፡ (Oring, 1986፡ 121) ፡፡

ተረክ ተከታታይነት ያላቸው ድርጊቶች፣ ሁነቶች እና ክስተቶች የሚፈጸሙበት፣ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቦታና ጊዜ የሚያሳይ፣ የአንድን ማኅበረሰብ ወይም ቡድን ልማድ፣ ባህልና ዕምነት የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ ፈጠራውና ተስተላልፎቱ ቃላዊ የሆነ፣ ከአንዱ ትውልድ በላይ የሚዘልቅ፣ ከሰው ልጅ የስልጣኔ ታሪክ ጋር አብሮ የሚጓዝ፣ እንደየዘመኑ ማኅበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታ ራሱን በመቀያየር የሚኖርና የሚተረክ ነው ፡፡ (Degh, 1972: 54 ፤oring, 1986: 122) ፡፡

ፈቃደ ሰዎችን ተረክን እንዴት ይገለገሉባቸው እንደነበር ሲገልጹ፡- በጥንት ዘመን ሰዎች ተረት በመተረክ ጊዜ ያሳልፉ ይዝናኑ፣ ይደሰቱ ይማሩ ነበር፡፡ ዛሬም ቢሆን በተመስጦ ያነቧቸዋል ያዳምጧቸዋል፡፡ ስለ አማልክትም ስለ ቅዱሳንም ስለ ነቢያትም...ወዘተ እንዲሁ በተመስጦ ያነባሉ ያዳምጣሉ፡፡ ከነዚህም ክንዋኔዎች ደስታን ትምህርትን ምግባርን ወዘተ ይቀስማሉ፡፡ (ፈቃደ ፣1991፡53) ፡፡

ተረክ ማኅበረሰብ ወይም ግለሰብ ማንነቱን፣ ወግና ልማድን፣ ባህልን፣ ገጠመኙን እና እምነቱን የሚያንጸባርቅበት ከትውልድ ትውልድ ትውፊታዊ እሴቶችን ለማሸጋገር የሚገለገሉበት መንገድ ነው፡፡ Harvilahti “Folklore and Oral Tradition” በሚለው ጽሁፋቸው “ተረክ በአብዛኛው ትውፊታዊ በሆነ ማኅበረሰብ ውስጥ ማኅበረሰቡ ባህሉን፣ ልማዱን እና የተለያዩ ገጠመኞችን ለትውልዱ የሚያስተላልፍበት ቃላዊ ጥበብ ነው” በማለት የላይኛውን ሀሳብ ያጠናክራሉ፡፡ (2003: 200)፡፡ ተረክ የሌለው ማኅበረሰብ ወይም ቡድን የለም፡፡ ሁሉም ተረኩን የሚያቀርብበት መንገድ ቢለያይ እንጂ ማንነቱን፣ ባህሉን እና ትውፋቱን የሚያዘልቅበት ተረክ አለው፡፡ ይህንንም ሀሳብ ፍቃደ ”ትረካ በማንኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ ያለ በዕለታዊ ህይወት በተለያየ መልክ የሚከወን ጉዳይ ነው” (1991፣ 52፣) በማለት ገልጸዋል::

### ኃይማኖታዊ ተረክ

ኃይማኖታዊ ተረኮች ማጥናት የማህበረሰቡን ሥነልቦናዊ እና ማህበረሰባዊ አኗኗር ማንነት ለመረዳት ያስችላል፡፡

ተረኮች የተለያዩ ኃይማኖቶች እምነትን ለማስረፅ፣ የኃይማኖቶች ሥርዓት ተጠብቆ እንዲቆይና ለትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ የተለያዩ ኃይማኖቶች (ለምሳሌ ክርስትና፣ እስልምና፣ ሂንዱ...ወዘተ) የኃይማኖቱን ማዕከላዊ ጉዳይ እምነት የሚያሰርጹት እና ኃይማኖታዊ እሴቶቻቸውን የሚያፀኑት በተረክ ነው፡፡ ኃይማኖታዊ ተረኮች በኃይማኖት ቅደሳን እና ነቢያት የሚባሉትን ሰዎች የህይወት ታሪክ እና ኃይማኖታዊ ተጋድሎ በውስጣቸው የሚይዙ ናቸው፡፡ ይሄንንም ለማረጋገጥ የክርስትና ኃይማኖት መሰረት የሆነውን የብሉይ እና የሀዲስ ኪዳን መጽሀፍት፣ እንዲሁም የእስልምና ኃይማኖት መሰረት የሆነውን ቁርዓን ማየት ይቻላል፡፡ይህንን በማስመልከት Dorson ካምብሌን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት የሰው ልጆች የህይወት እና ሞታቸውን ጣጣ በተረክ አማካኝነት ይገልጻሉ፡፡ ተረኮች የሰውን ስነልቦና የሚያንጹ የኃይማኖትና የዕምነት ምንጭ ናቸው (1973: 108) ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ

“የሰውን ልጅ የአስተሳሰብ ደረጃና እሴቶችን አካቶ የያዘው ስርዓተ አምልኮ በሐተታ ተፈጥሮ እና በአፈ ታሪክ አማካኝነት ይገለፃል” (Messenger,1972: 220) በማለት ተረክ ለኃይማኖቶችና ለእምነት የጀርባ አጥንት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ተረኮች የተራኪውን ማኅበረሰብ አመለካከት የያዙና የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህን ተረኮች በማጤን የማኅበረሰቡን አመለካከት፣ እምነት፣ ባህል፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ፍልስፍና፣ ወዘተ. ማወቅ ይቻላል በዘመናችን በተለያዩ ቤተ እምነቶች የተለያየ ይዘት ያላቸው ተረኮች ይተረካሉ፡፡ እነዚህ ተረኮች ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የመጡ፤ በተለያዩ አጋጣሚዎች ምዕመኑን ለማስተማር እና የእምነቱን ስርዓት ጠብቆ እንዲጓዝ ለማድረግ የሚፈጠሩ እና የሚከወኑ ናቸው፡፡ (Sims, 1963: 168) ፡፡

**ቃል ተረክ (Oral narrative)**

ተረኮች በተለያየ ቅርጽ ይቀርባል ካልን የዚህ ጥናት ትኩረት ቃላዊ ዝርው ተረኮች (oral prose narrative) ናቸው፡፡ ቃላዊ ዝርው ተረክ የስነቃል አንድ ክፍል ሲሆን ግጥማዊ ባልሆነ መልክ በቃል የሚተረክ፣ ተለጣጣቂነት ያላቸው ድርጊቶችና ሁነቶች የሚፈፀሙበት፣ የድርጊቱ ተሳታፊ የሆኑ ገጸ ባሕርያት የሚገኙበት፣ እንዲሁም ድርጊቱ የሚፈፀምበትን ቦታና ጊዜ የሚያመላክት ታሪክ ነው (Oring, 1986: 122) ፡፡

ቃል ተረክ (Oral narrative) አንዱ የስነ ቃል ዘርፍ ሲሆን የሰዎችን የማስታወስ ችሎታ መሰረት በማድረግ በቃል ለበዙ ዘመናት ሲተላለፍ የኖረና ለዛሬው ትውልድ የደረሰ ነው ፡፡ ቃል ተረክ በዝርው የትረካ (prose narrative) ስልት የሚቀርብ ሲሆን ስለሚነገረው ሁነት (event) ሰፋ ያለ ማብራሪያ ወይም መግለጫ የሚሰጥ ነው ፡፡ ይህ ጥበብ የሰው ልጅ ከልደት እስከ ሞት የሚኀዝበትን ህይወት የሚገልጽበት በመሆኑ በማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ የሚገኝ ነው (ሰለሞን ተሾመ ፣2007፣83) ፡፡

ከዋኞቹ ቃል ትረካዎችን የሚያቀርቡት ከዚህ በፊት የሰሙትን በአዕምሮዓቸው በማስታወስና በቃል በመንገር ነው፡፡ ይህ የትውስታዊ ሂደትና የቃላዊነት ባህርይ ከዋኙ ቃለ ትረካዎችን ከሚቀርቡበት አውድ በመነሳት በራሱ እንዲያሻሽል ወይም ድግመ ፈጠራ (re-creation) እንዲያካሂድ ያደርጋሉ፡፡ ድግመ ፈጠራ በክወና ወቅት መኖሩ ቃለ ትረካዎች ያለፈውን ሁኔታ ብቻ የሚገልጹ ሳይሆኑ የአሁን ሁኔታንም የመግለጽ ባህርይ እንዲኖራቸው ምክንያት ይሆናል፡፡ (ሰለሞን ተሾመ ፣2007፣83)

ቃል ተረክን አስመልክቶ በጻፈው መጽሀፍ “በአለም የሚገኙ ቃል ተረክ ስፍር ቁጥር የላቸውም፡፡” የተረኮች ጥናትም አስገራሚ የሙያ ዘርፍ ነው፡፡ ቃል ተረክ በተቀላጠፈ ቋንቋ ንግግር፣ በጽሁፍ፣ በቆሙና በተንቀሳቃሽ ምስሎች (Fixed or Moving Image) በተለያዩ አይነት መገለጫዎች የሚቀርቡ ናቸው በማለት ብያኔ ይሰጣል (Barthes፣79) ፡፡

ቃል ተረክ የአንዱን ልምድ /ተሞክሮ/ በቃሉ ማስተላለፍ መሆኑን ይገልጻል፡፡ እንደ ርእሱ አገላለፅ ከሆነ ተረክ የአንዱ ቡድን ወይም ማህበር የተሞክሮ እና አስተምህሮ መለዋወጫ መንገድ መሆኑን ይጠቅስልናል፡፡ (Oring፣ 122)

ቃል ተረክ የሚተላለፉባቸው የአፍ ተረክ ገድላት ፌብል /Bab Brunesle) ታሪክ፣ትራጄዲ፣ ኮሜዲ፣ ድራማ፣ የመስታወት ሥእሎች፣ ሲኒማና የቀልድ መፅሐፎችን ነው፡፡ የሰውን ልጅ በማናቸውም እድሜ እና ቦታ ከጥንት ጀምሮ ከተረክ ውጭ አንድነቱን ማሡብ እንደማይቻል ይገልፃል፡፡ (Barthes፣79)

ቃል ተረክ ቃላዊ ባህሪ ያለው ነው፡፡ ነገር ግን ቃላዊ መሆኑ የተለየ ቅርጽና ባህሪ እንዳይኖረው አያደርግም፡፡ ይልቁንም ከሌሎች የስነ ቃል ዘርፎች የሚለይበት የራሱ ቅርጽና ማዕቀፍ አለው፡፡ ይህ ማዕቀፍ (Frame Work) ቃል ተረክን ሙሉ ትርጉም የሚሰጥና ስርዓታዊ ያደርገዋል፡፡ Barthes ይህንኑ ጉዳይ በማንሳት ዋና ዋናዎቹ የቃል ተረክ ማዕቀፎች ከቋንቋ አንጻር አገነባቡ (Organization) እና ከመቼት አንጻር ያለው ወቅታዊነት መሆናቸውን ይገልጻል (Bruner 43) ፡፡

በአጠቃላይ ተረክ የማኀበረሰብ እና የግለሰብ መግለጫ ሲሆን ሰፊውን የሰውን ልጅ አስተሳሰብና ስሜት ያንፀባርቃል፡፡ ተረክ በግልም ሆነ በማኅበር የሚነገር የታሪክ ማሳያ ነው፡፡ በግል ይነገራል ሲባል ሰዎች ስለራሳቸው የሚተርኩት ታሪክ ነው፡፡ ተረክ ግለሰባዊ ተናጋሪነትን የሚፈጥር፤ ዕሴትን እና እምነትን የሚያሳይ፤ የሰውን የወደፊት ህይወት መስመር ማስያዝ የሚችል ነው፡፡ ተረክ የግለሰብን አስተሳሰብ እና ገጠመኝ ብቻ የሚያንፀባርቅ ሳይሆን በባህል ውስጥ የሚመላለስ፣ ስለአንድ ቡድን ከየት መጣነቱን ፣ ገጠመኝ፣ ቃላዊና ቁሳዊ ጥበባት እና ስለማኅበረሰቡ አኗኗር ይተርካል፡፡ ተረክ ማለት የአንድን ማኅበረሰብ ወይም ቡድን እና ግለሰብ አመለካከት፣ ባህል፣ እምነት እና ማኅበራዊና ስነልቦናዊ ማንነት ለማወቅ የሚያስችል፤ ሁነቶችንና ድርጊቶችን የሚያሳይ፤ ዓረፍተ ነገሮች በአግባቡ ተዋቅረው የሚያደራጁት፣ ታሪክ ያለው፣ ታሪኩን የሚያስኬድ ገጸ ባሕርያት ያሉት የሀሳብ ማስተላለፊያ መንገድ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## የተረክ አይነቶች

የተረክ አይነቶችን በተመለከተ አለም አቀፋዊ የሆነ ክፍፍል ባይኖርም ሚት፣ አፈታሪክ እና ተረት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ ክፍፍሎች እንደሚኖሩና ቀልዶች እና ትዝታዎች (የግል ትውስታዎች) በተረክ ውስጥ እንደሚካተቱ መታወቅ አለበት (Bascom: 1965:5)

## ሚት (Myth)

ሚት ማለት የሰው ልጅ አከባቢን እና ተፈጥሮን ለመረዳት በአምሮ የሚመላለሱ የማንነት እና የምንነት ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚረዳ መንገድ ነው ፡፡ ይህን በማስመልከት ቴዎድሮስ እንደሚከተለው ያስረዳሉ ፡፡ ሚት የሰው ልጅ ስሜት ህዋሱን ከሚያግደው አድማስ አምልጦ በመውጣት በሜታፊዚክላዊ ሀይል አይን አለማቱን ለማየት፣ ለማወቅ ያወቀውን ለመበየንና ለመቆጣጠር የሞከሩበት ፍልስፍና ነው፡፡ ሚት በምርምር የማይደረስበትን ተግባር ሙከራ የማይረጋገጥን ልእለ አካላዊ ጉዳይ በመንፈስ በምናብ ሀይል የምናቀርብበት ስርአት ነው፡፡ (ቴዎድሮስ 2001፡67-68)

ሚት ማህበረሰቡ በአከባቢው የሚያስተውላቸው ተፈጥሯዊ ሁነቶች ያላቸውን ባህርይ አፈጣጠራዊ ሂደት ከየት መጣነት መልስ ለማግኘት የሚጥርበት ነው፡፡ የአካባቢውን የባህል እሴት መሠረት በማድረግ ለራሱ የአሰተሳሰብ አድማስ ለአለም ያለውን ግንዛቤ የሚገልፅበት የተረት አይነት ነው፡፡

ሚት ስነ ፍጥረት እና ስለ ተፈጥሮ፣ ስለ ተፈጥሮና ስለ ፈጣሪ የሚተርክ ልእለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ያላቸው መናፍስት በገፀ ባህርይነት የሚንቀሳቀሱበት በተራኪው ማህበረሰብ እውነት ተደርጎ የሚቆጠር ተረክ ነው፡፡ (Bascom: 1965:5)

ከሚት አይነቶች ውስጥ ሐተታዊ ተፈጥሯዊ ሚት፣ መንፈሣዊ ሚት፣ የባህል ታጋይ ሚት፣ ጊዜያዊና የዘላለማዊ ሚት፣ ዘመናዊ ማህበረሰብ ሚት፣ ጂኦሚቴዎሎጂ ወዘተ ይጠቀሳሉ (ሰለሞን ተሾመ 2007, 101)

ይህ የሰዎች የወል ሀብት የሆነ ሚት በተረክ የተገነባ ሲሆን የሰዎች ማን ነኝ? ወደየት እሄዳለሁና የተፈጥሮ ሥርዓት እንዴት ይመራል? የሚሉና መሰል ጥያቄዎችን የሚመልሱበት ሚት ባለበት ማኅበረሰብ ቅቡል በመሆኑ የሰዎችን የአእምሮ ክፍተትም ይሞላል። የሰው ልጅ የሚኖርበትን ማኅበረሰብ ሚታዊ ተረክ አክብሮና በማመን ተቀብሎ ለምኞቱና ለፍላጎቱ መነሻና መድረሻ እየተገለገለበት ዘመን ይሻገራል።

**ተረት** (Foktale)

ተረት ሰው ልጆች እንስሳት መናፍስትና ሌሎች ፍጡራን ገፀ ባህሪ ሆነው የሚቀረፁበት ሙሉ ለሙሉ ፈጠራ የሆነ መቼት የሚያደርገው ጊዜና ቦታ በውል የማይታወቅ የራሱ አጀማመር እና አጨራረስ ስርአት ያለው ተረክ ነው (ቴዎድሮስ 2001፡ 259)

ተረቶች በሚተረቱበት ወቅት ታሪክ ውስጥ የሚቀርቡ ድርጊቶች የተከሡቱበትን ጊዜና ቦታ በግልፅ የሚያሳይ በሞራል የምንፈጥራቸው ናቸው፡ ስለሆነም ተረቶች እንደ እውነተኛ ታሪክ ከመውሰድ ይልቅ በሚፈጥሩት ደስታ የምንዝናናባቸው ናቸው በማለት (Benamos, 1992: 102) ይገልፃል።

የተረቶች ዋና ዋና ውጫዊ ቅርፆች ውስጥ የተረት መግቢያ፣ የተረት አጀማመር፣ የተረት አጨራረስ፣ የተረት መዝጊያ እና የተረት ክዋኔ (ትረታ) ይጠቀሳሉ። (ፈቃደ፣ 1999፡63)

**አፈ- ታሪክ** (Legend)

የአፈ ታሪክን ምንነት በማስመልከት ቴዎድሮስ እንደሚከተለው ገልፀዋል። ባለቤቱ በሆነው ማህበር ዘንድ ከእውነት ተቆጥሮ የሚነገር ቃላዊ ተረክ ነው። በአፈታሪክ ውስጥ ከሚሣሉ ገፀ ባህርያት መሀል ዋና ዋናዎቹ በብዛኛው ታሪክ (history) የሚያውቋቸው ተረኩ መቼት ባደረገው ዘመንና ስፍራ በእውን የነበሩ ሰዎች ናቸው። ሰዎቹ በታሪክ የተሳተፉባቸው ታላላቅ ሁነቶችና በሁነቶቹ ውስጥ የፈፀሟቸው ተጋድሎዎች (እንደተረኩ አይነት መንፈሳዊ እና አለማዊ ተጋድሎዎች) በአብዛኛው በተረኩ ውስጥ ሥፍራ ያገኛሉ። አፈ ታሪክ በከፊል ታሪካዊ በከፊል ደግሞ ፈጠራዊ (ምናባዊ) በመሆን ከዋኙ በፈጠራው መካከል ሚዛን ምጣኔና ሀብር ይኖር ዘንድ በእጅጉ ይደክማል (ቴዎድሮስ 2001፡ 262-263)።

> *አፈ ታሪክ በእውነት ላይ የተመሠረተ ልማዳዊ የሆኑ ነገሮች የሚመረመሩበት ገፀ ባህርያቱ ሰዎች የሆኑ በእራሳቸው የሚቆሙ ሳይሆኑ እራሳቸውን አሳልፈው ሰዎችን ነፃ የማውጣት ባህርይን የተላበሱ፣ ገፀባህርያቱ የሚተወኑበትን*

*መንፈሳዊ፣ ስጋዊ ጉዳይም የሚያነሳ፣ በዚህኛው አለም የፈተፀመ የቅርብ ኃላፊ ጊዜ ያለው፣ መቼቱ አንዳንዴ የሚታወቅ፣ እውነትነት ያለው፣ ስለ ሰዎች ስለቦታዎች ስለታሪኮች እና የተለያዩ ክስተቶች የሚተርክ ማለት ነው። (Bascom፡1965:6)*

እንደ እርሳቸው ገለጻ በሚት፣ በአፈታሪክና በተረት መካከል ያለው ልዩነት በሚቀጥለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡-

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቅርጽ (Form ) ሚት (Myth) | የሚታመነው (Belief) እውነት (Fact) | ጊዜ (Time) በጣም ሩቅ (Remote Past) | ቦታ (Place) የተለያዩ ዓላማት (Different World other or Earlier) | ጠባይ (Attitude) የተቀደሰ (Sacred) | ዋና ገጸ ባህርይ (Principal) ሰው ያልሆኑ (Non human) |
| ሌጀንድ (Legend) | እውነት (fact) | የቅርብ ሩቅ (Recent past) | የምንኖርበት አለም (world of today) | ቅዱስ ወይም አለማዊ (secular or sacred) | ሰዎች (Human) |
| ተረት (Foktale) | ልቦለድ (Fiction) | ማናቸውም ጊዜ (Any time) | የትም ቦታ (Place) | አለማዊ (Secular) | ሰዎችም ሰዎች ያልሆኑ (Human non human) |

(Bascom፡1965:7)

በአጠቃላይ አፈታሪክ ቃላዊ በሆነው ተስተላልፈው አድማጩን በማስተማር፣ በማንቃት ወይም ለአድማጩ መረጃ በመስጠት ታሪክ በማሳወቅ ወዘተ.... ረገድ የራሱ የሆነ ከፍተኛ ድርሻ አለው።

### ተረክን የማጥናት አስፈላጊነት እና የአጠናን ስልት

ተረክን ለማጥናት የሚነሳ ሰው ትኩረት ሰጥቶ ሊመልሳቸው የሚገቡ መሠረታዊ ጥያቄዎች አሉ። እነሡም የተረኩ መልእክት ምንድን ነው? ለተረኩ መፈጠር ምክንያት የሆነው ጉዳይ ምንድነው? እና ተረኮቹን ተራኪዎቻቸው እና አድማጮቻቸው እንዴት ይመለከታቸዋል? የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው። (Deigh፡ 1972:54)

ተረክን ማጥናት ደግሞ የተራኪውን ማህበረሰብ ማንነት፣ እምነት፣ አስተሳሰብ ወዘተ ለመረዳት ያስችላል፡፡ይህንንም በማስመልከት ተረኮች የተራኪውን ማህበረሰብ አመለካከት የያዙና የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህን ተረኮች በማጤን የማህበረሰቡን አመለካከት እምነት፣ ባህል፣ ርእዮተ አላማዊ ፍልስፍና ወዘተ ማወቅ ይቻላል ፡፡ (Sims: 2005:168)

ተረክ ስናጠና ተረኩን ብቻ ወስዶ ትንታኔ ከመስጠት ይልቅ የተረኩ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ ለተረኩ ያለው አመለካከት፣ ባህል፣ የመከወኛ ቦታና የመከወኛ ጊዜ ማወቁ በተረኩ ውስጥ ያሉትን ትእምርቶችና ሀሳቦች ለመረዳት ያስችላል፡፡

በተረክ ላይ ጥናት የሚያደርግ አጥኚ ስለተረኮቹ የጠለቀ እውቀት እንዲኖረው እንዲሁም በተረኮች ላይ እውቀት አዘል ትርጉም ለመስጠት እንዲያስችለው አነዚህን አራት አውዶች መረዳት እንደሚጠበቅበት ይገልፃል፡፡ እነሱም፡-

1. ባህላዊ አውድ፡- ይህ የአውድ አይነት በተረኮች ውስጥ ያሉ ሐሳቦችን፣ ትእምርቶችን እና በተረኩ የሚገለገሉትን ቡድኖች ባህሪ የምንለይበት ነው፡፡
2. ማህበራዊ አውድ፡- ተረኩን ማህበረሰቡ እንዴት እንደሚገለገልበት በተረኩና በማህበረሰቡ መካከል ያለው ዝምድና ምን እንደሚመስል የምናይበት ነው፡፡
3. ግላዊ አውድ፡- ተረኮች ከአንድ ግለሰባዊ ታሪክ ጀምረው እስከ ሰፊው ማህበረሰባዊ ጉዳይ ድረስ የሚሄዱ ናቸው፡፡ ግላዊ አውድም የአንድን ገለሰብ ግላዊ ብቃትና የህይወት ልምድ ልናውቅበትና ልንገመግምበት እንችላለን፡፡ ይህንንም ስናደርግ በግለሰቡ በአብዛኛው የሚተረክልን ተረክ የትኛው ነው? ለምንስ ነው ይህንን የመረጠው? የተራኪው ማንነትስ ከተረኩ ጋር ያለው ግኑኝነት ምንድነው የሚሉትን ነገሮች በጥልቀት የሚያሳይ ነው፡፡
4. ንፅፅራዊ አውድ፡- ይህኛው አውድ ከላይ ከተጠቀሱት ከሶስቱ የአውድ አይነቶች በተወሰነ ደረጃ የሚለይ ነው፡፡ ይኸውም ንጽጽራዊ አውድ የአለምን የፎክሎር ተረክ የሚያነሳ እና በትረካው ላይ ከሚታዩ ሁነቶች ውጪ በመውጣት ተረኩ ሌላ ተረክን የሚጠራ መሆኑ የምንቃኝበት ነው፡፡ እነዚህን አውዶች መረዳት እና ከግንዛቤ ማስገባት ተረኮቹ ለማህበረሰቡ ምን እንደሆኑ እና ሚናቸውን ለማወቅ ያስችላሉ፡፡ (Oring 1986: 135-142)፡፡

### 2.1.2. ቁሣዊ ባህል (Material Culture)

ቁሣዊ ባህል የምንላቸው የሠው ልጅ በስሜት ህዋሳቱ አማካኝነት የሚያያቸው የሚዳስሳቸው የሚያሸታቸው.... የመሣሰሉትንና ተፈጥሮ በለገሠችው ነገር የራሱ የፈጠራ ብቃት ጨምሮ የሚሠራቸው ነገሮች ሲሆኑ ዘመናዊ ስልጣኔ ከመታየቱ በፊት የሠው ልጅ የእለት ተእለት ክንዋኔውን ይከውንባቸው የነበሩ ቁሳቁሶችን አጣምረው የያዙ ነገሮች ናቸው፡፡

ከአራቱ ፎክሎር ዘውጎች መካከል ቁሣዊ ባህል አንዱ ነው፡፡ በቁሣዊ ባህል ሥርም የምናገኛቸው ሀገረ ሰባዊ እጅ ሥራ፣ ሀገረ ሰባዊ ልብስ፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራር እና ሀገረ ሰባዊ ሥእል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው (Dorson1964፡110)፡፡

ቁሣዊ ባህል ጥናት በተፈጥሮና በባህል መካከል ያለን ልዩነት በአእምሮአችን በመሣል የእለት ተእለት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ፍላጎታችንን በማስቀደም ተፈጥሮን መልሰን መላልሰን የምንለዋውጥበት አዲስ አቅጣጫ የምናስይዝበት መንገድ እና የምናጤንበት ዘዴ መሆኑን ይገልፃል፡፡ (Classic1991፡1)

ቁሳዊ ባህል የአንድን ዘመን ምንነት/አሻራ የሚያመለክት ሲሆን የዘመኑን ማህረበሰብ ፖለቲካዊ አቋሙ ንቃተ ህሊናው የፈጠራ ብቃቱ፣ ወጉ፣ እምነቱና ፍልስፍናው ምን ይመስል እንደነበር የምናውቅበት አይነተኛ መሣሪያ ነው፡፡

ሃይማኖታዊ ጉዳይን ለማጥናት የሚነሣ ተመራማሪ የሚያምንበትም ይሁን የማያምንበት ከውስጥ ተነሥቶ መሆን እንደሚገባ ያስረዳሉ፤ ስለዚህ በቅድሚያ ቁሶቹን ሃይማኖቱ ምን ይላቸዋል? እንዴት ይገለገልባቸዋል? የሚሉትና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በመመርመር ወደ ፎክሎር ገፅታቸው ማምጣቱ የተሻለ እነደሚሆን ይገልፃሉ፡፡ (Danielsan 986:101)

ይህም ጥናት በዋናነት ትኩረቱ እምነታዊ (በቤተክርስቲያን) ግልጋሎት የሚሰጡ ቁሶች ላይ ነው፡፡ ስለሆነም የእምነታዊ አገልግሎት ሥርዓት ማከናወኛ ቁሶች ምን ይባላሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች ሊያጭር ስለሚችል እግረ መንገዴን መልስ መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ የቤተክርስቲያን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ማከናወኛ ቁሶች ንዋያተ ቅዱሳት በመባል ይጠራሉ፡፡ ንዋያተ ቅዱሳት ማለት ቅድስና፣ ንጽህና ፣ ሰማያዊ የሆነው የእግዚአብሔር ስም የሚመሰገንባቸው፣ ሥርዓተ አምልኮት የሚፈጸምባቸው፣የተለዩና የከበሩ የቤተክርስቲያን ንብረቶች ወይም ሀብቶች ናቸው፡፡ የንዋያተ ቅድሳቱ ዐይነትና ቅርጽ እግዚአብሔር ለሙሴ ባሳየውና መጠናቸውንም ለክቶ በሰጠው መሠረት የሚሠሩ ናቸው (ዘፍ፡ 24-28)፡፡

ከብያኔው እንደምንረዳው ሰዎች በውስጣቸው ያለውን ነገር በእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው እንደሚገልጹበት ሁሉ የዚህ ስሜት መግለጫ ከሆኑት ነገሮች መካከል አንዱ ቁሳዊ ባህል መሆኑን የሚጠቁም ነው። ይህም ቁሳዊ ባህል በሥሩ ምን ምን ነገሮችን እንደሚይዝ ወይም የቁሳዊ ባህል ዐይነት የምንላቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ የተወሰኑ ግንዛቤዎችን ማስጨበጥ የሚያስችል መሆኑን ነው።

የቁሣዊ ባህል የመተንተኛ ስልት እንደ ሞዴልነት የሚጠቀሱት የጥበብ ነፀብራቅነት፣ ተምሣሌታዊነት፣ ባህላዊነት፣ አገልግሎት ሰጭነት፣ መዋቅራዊነት፣ አካባቢያዊነት፣ ባህሪ ገላጭነትና ማህበረሰባዊ ታሪካዊነት የሚባሉት ናቸው። ቁሣዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎቹ ከቁሱ ውጫዊ ገፅታ እስከ ተምሳሌታዊ ትርጓሚያቸውና እንድምታዊ ትንታኔ ድረስ የሚዘልቁ ናቸው፡ ፡ በእነዚህ ሞዴሎች በኩል ስንጓዝ የቁሶችን ቀለም ለስላሳነትና ሸካራነት በመመልከት ጥበባዊ መስህብነታቸውን መግለፅ ቁሶቹ በውክልና የቆሙላትን ነገር ማሣየት የተገልጋዩን ማህበረሰብ ባህል በመግለፅ ረገድ ያላቸውን ድርሻ መፈተሽ ሲሰሩ የታቀደላቸውን ተግባር መለየት፣ ቁሱ እንዴት ተሠራ፣ ከምን ተሠራ ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት አካባቢው በቁሱ ላይ ያሳደረውን ተፅእኖ መፈተሽ በቁሶቹና በማህበረሰብ መካከል ያለው መስተጋብርና ቁሶቹ በህዝቡ ላይ አንዳች ያመጡት የተለየ ባህሪ ካለመፈተሽ እንዲሁም ቁሱ ከየትኛው ዘመን ማህበረሰብ እንዲፈለቀና ዘመኑን መፈተሽ የሚሉት ይጠቀሳሉ (David Brown 1971:201)::

በአጠቃላይ የቤተክርስቲያኑን ሀይማኖታዊ ስርአት ማከናወኛ ነዋያተ ቅድሳት ማለት ንጽህና፣ ቅድስና፣ ሰማያዊ የሆነውን የእግዚአብሔር ስም የሚመሰገንባቸው ስርዓተ አምልኮት የሚፈጸምባቸው የተለያዩና የከበሩ የቤተክርስቲያን ንብረቶች አሉት። ይህም ጥናት ትኩረት በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ያሉት ቁሶች ምን ምን ይባላሉ? ምን አገልግሎት ይሠጣሉ የሚለውን ይመልሳል።

### 2.1.3. የቁሳዊ ባህል አተናተን ሂደቶች

ቁሳዊ ባህል የሚተነተነባቸው የተለያዩ የመተንተኛ ዘዴዎች አሉ። ቁሶችን በምድብ በምድብ ከፋፍሎ ማስቀመጥ አስቸጋሪ መሆናቸውን ይገልፃሉ። ምክንያቱም የመጀመሪያው የቁሶች አይነትና ቁጥር ብዙ ሆኖ መገኘት ሲሆን ሌላው የሚያስማማ አንድ ወጥ የሆነ መስፈርት አለመገኘት ናቸው። ይሁን እንጂ የራሱ የመተንተኛ ሂደቶች አሉት። እነሱም፡- ገለፃ (Description)፣ ትርጓሜ (Deduction)፣ ማመላከት (Speculation) ናቸው በማለት አስቀምጧል። Brown (1982:2)

## 2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

### 2.2.1. ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (Functional Approach)

ተግባር ስንል በአንድ ስርአት ውስጥ የታቀፈ አንድ ሁነት ለአጠቃላይ ሁነት የሚያበረክተው ድርሻ ነው፡፡ አንዱ ማህበረሰብ በቋንቋው ወይም በባህሉ አማካኝነት የሚገልጸው ጉዳይ ተግባር የሚባለው የማህበረሰቡ ማህበራዊ መዋቅር ባለበት ሁኔታ ተጠብቆ እንዲዘልቅ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ነው፡፡ (Dorson 1972፣25)

ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች በቤተክርስቲያኑ ለምን ተግባር ይውላሉ? የተረኮቹ መነገር ለቤተክርስቲያኑ ምን ፋይዳ አላቸው? የሚሉትንና ሌሎች ጥያቄዎችን ለመመለስ እንዲያስችል ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ተመርጧል፡፡ ከተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ጥናቱ ትኩረት ያደረገው ሃይማኖታዊ ተረኮችና ቁሣዊ ባህሎች ላይ ነው፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ወይም ፎክ ቡድን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሎሮች በፎክ ቡድኑ ወይም በማህበረሰቡ የሚሰጡትን ተግባር በቡድን ውስጥ ያላቸውን ትእምርታዊ ሆነ አውዳዊ ትርጓሜ በማሳየት ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡

ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ቃላዊ፣ ልማዳዊና ቁሳዊ ፎክሎሮችን ለማህበሩ ምን እና እንዴት ይጠቅማሉ የሚለውን ማጥናት ያስችላል፡፡ ይህንንም በማስመልከት ፎክሎር ይህንን ንድፈ ሀሳብ ወደራሱ ሲያመጣው በተወሰነ ደረጃ ለራሱ እንዲስማማ አድርጎታል፡፡ በፎክሎር ጥናት ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ በፎክሎሩ ይዘት፣ በፎክሎሩ ባለቤት አጠቃቀም እና በሚሰጠው ትርጉም ላይ ተመስርቶ ፎክሎሩን ለመተንተን የሚያስችል ግኝት የሚያመጣ ንድፈ ሀሳብ አድርጎ ነው፡፡ እንደ ፎክሎር አጥኚዎች ትኩረት ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ በፎክ ግሩፕ ውስጥ ያለውን ስነ ቃላዊና ጽሁፋዊ ጉዳዮች በመመርመር ሰዎቹ በፎክሎሩ ምክንያት የሚያገኙትን ጥቅም ማሳየት እና ለምን ጉዳይ እንደተገለገሉበት በመመርመር ተግባሩን የሚያሳይ ንድፈ ሀሳብ እንደሆነ በመግለጽ፣ የፎክሎር ባለሙያው በዚህ ሂደት ውስጥ ከፎክሎሩ የሚገኘውን ትርጉም ግላዊና ማህበራዊ ጥቅም በአትኩሮት መመርመር አለበት፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ አንድ ማህበረሰብ ቃላዊ፣ ልማዳዊ እና ፅሑፋዊ ጉዳዮች በመመርመር ሰዎች እነዚህን ጉዳዮች ለመጋራት ካላቸው

ጥቅም አኳያ ለምን እና እንዴት በሚሉ ጥያቄዎች አማካኝነት ፈትሾ ተግባራቸውን የሚያሳይ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ (Sims, 2005፡ 175) ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ ቤተክርስቲያኑ ተረኮቹና ቁሣዊ ባህሎቹን ለምን አገልግሎት ያውሏቸዋል? በቤተክርስቲያኑ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ እና ስርዓት ተረኮቹ፣ ቁሳዊ ባህሎቹ ምን አገልግሎት አላቸው? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ተመራጭ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የሥነቃልን ተግባራት በአምስት አበይት ክፍሎች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም፡-

1. የመግለጥ ተግባር፡- ገላጭ ትረካዎች በየአከባቢው ለሚኖሩ ሰዎች መሠረታዊ ጥያቄዎችን መልስ ለመስጠት የሚሞክሩ ናቸው፡፡ አከባቢያቸውን፣ ሰውን፣ አንስሳትን፣ እፀዋትን … ማን ፈጠራቸው እያሉ ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራሉ፡፡ የኬት መጣ (Origin) ትረካዎች ለዓለማቸው አንድ የተወሰነ ቅርጽና አደረጃጀት ለማበጀት የሚጥሩ ናቸው፡፡
2. የማጠናከርና የመትከል ተግባር፡ ማህበራዊ ድርጅቶቻቸውና ልዩ ልዩ ባህሎቻቸውን በስነቃል አማካኝነት ያጠናክራሉ፡፡ ከልደት እስከ ሞት የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች አስፈላጊነቱና ተገቢነት እያሳመኑ ክንዋኔዎቹ እንዳይከስሙ፣ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በተለይ የገጠሩ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከናወኑትን ከልደት፣ ከግርዘት፣ ከጋብቻ፣ ከጀግንነት፣ ከሞት ወዘተ ጋር የተያያዙትን ድርጊቶች ቀጣይነት በስነቃል ያረጋግጣሉ፤ መሰረታቸው እንዳይናጋ አጥብቀው ይተክላሉ፡፡
3. የማምለጫ ተግባር፡- የሰው ልጅ ከወትሮአዊ የለተለት የህይወት ውጣ ውረድ ማምለጫ ይፈልጋል፡፡ ከአሰልቺ እና ከተደጋጋሚ የህይወት ክስተቶች ሸሽቶ በምናቡ አዲስ ዓለም ውስጥ መግባት ይሻል፡፡ ይህንን ተግባሩን ከመሬታዊውና ከአከባቢው ኑሮ ተጣልቶ ወደ ሰማያዊውና ወደ ሩቅ ለጊዜው እንደማረግ፣ እንደመሰደድ ልናየው እንችላለን፡፡ ሥነቃል አንዱ የማረፊያው፣ የማምለጫው መንገድ ነው፡፡
4. የማስተማር ተግባር፡- በተለይ ምሳሌአዊ አነጋገሮች፣ ፋቡላዎች፣ የተጠንቀቅ ትረካዎች እና ኑዛዜአዊ ዘፈኖች፣ የአኗኗር ስርዓት ምግባርና ብልሃት ያስተምራል፡፡ የአበላል፣ የአጠጣጥ፣ የአለባበስ፣ የአቀማመጥ፣ የአነጋገር፣ የአካሄድ ስርዓትን ያሳውቃሉ፡፡
5. የመግታትና የመቆጣጠር ተግባር፡- የአኗኗር ብልሃትንና በጎ ምግባርን ያስተምራሉ ያልናቸው ስነቃሎች የጥዩፍ ባህርያትን፣ መስፋፋትን ሲቆጣጠሩ ይገኛሉ፡፡ ስርቆትን፣

መዋሸትን፣ ስስትን፣ ክፋትን፣ ፈሪነት ይገስፃል፡፡ በቀልድ ዘፈኖችና ትረካዎች አማካኝነት በእነዚህ ጠባያት ይሳለቁባቸዋል፣ ያጥላሉዋቸዋል፣ ያላግጡባቸዋል፡፡ እነኚህ እሴቶች በልዩ ልዩ የሥነቃል ቅርፆች የሚቀረጹና የሚነገሩትን እንደተግባራዊ የህይወት መመሪያ እንዲያገለግሉ ነው፡፡ በአንዳንድ ቦታ እንደ እውነተኛ ታሪክ ሲቆጠሩ ይታያል፡፡ ማህበሩ ምስጉንና ድንቅ ከሚላቸው እሴቶች የሚያፈነግጡትን ወይም ለማፈንገጥ ገና ዳርዳር የሚሉትን በአርፈህ ተቀመጥ ግሳጼ ወደ ብዙኃኑ አስተሳሰብ መመለስ ነው፡፡(ፈቃደ አዘዘ 1991፡20-22)

ይህ ጥናት የተጠኚውን ማህበረሰብ እምነት መሠረት በማድረግ ከቤተክርስቲያኗ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና ቁሣዊ ባህሎች ለቤተክርስቲያን ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው የተረኮቹንና የቁሣዊ ባህሎቹን ፍቺ ለማወቅ ይረዳል፡፡

የቁሳዊ ባህል ጥናት ሰዎች የሚገለገሉባቸውን ቁሶች ከሚሠጡት ግልጋሎት ባሻገር ያላቸውን ትርጉም በመፈተሽ የሰዎቹን እሴቶች አመለካከትና ፍላጎት እንዲሁም የዘመንን መንፈስና የማህበረሰቡን ሕይወት ልምድ ለማንጸባረቅ የሚያስችል ነው፡፡ይሄን ለማድረግ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን በመጠቀምና ለቁሣዊ ባህሉ ትንታኔ መስጠት ተሞክሯል፡፡

በአጠቃላይ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ቃላዊ፣ ልማዳዊና ቁሣዊ ባህሎችን የያዙ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ለተተኳሪው ማህበረሰብ ምን እንደሚጠቅሙ ማህበራዊ ባህላዊ እና ግላዊ አውዱን መሰረት በማድረግ የሚያጠና ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

### በኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ክፍል የተደረጉ ጥናቶች ዳሰሳ

በእንጦጦ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን በዙሪያው የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ጥናት በሚል ጥናት ጋር በቀጥታ የተገናኘ ጥናታዊ ጽሁፍ አላገኘሁም፡፡ ሆኖም በዚህ ክፍል ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ጥናታዊ ፅሁፎች ተቃኝተዋል፡፡ እነሱም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መጻህፍት ውስጥ ባደረግኩት ዳሰሳ ደግሞ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተሰሩት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥናታዊ ጽሁፎች ማግኘት ችያለሁ፡፡ እነዚህን ጥናቶች መምረጥ የቻልኩት ገዳም ላይ በመመስረት ተረክን የተወሰኑት ደግሞ ቁሳዊ ባህልንም ስላጠኑ ነው፡፡

የጥናቶቹ አጠቃላይ ገፅታ ከእኔ ጥናት ጋር ያላቸው ዝምድና ክፍተት እና የእኔ ጥናት ከጥናቶቹ በምን እንደሚለይ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

መሪማ መሀመድ (2009 ዓ.ም) "የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት ገዳም አመሰራረትና በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት፡፡" የጥናቱ ዓላማ በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩ ቃላዊ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች መመርመር፣ መግለጽና መተንተን ነው፡፡ በጥናቱ ምልከታንና ቃለ መጠይቅን ተጠቅማለች፡፡ መረጃዎቹን በተረክ ቁሳዊ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ በመጠቀም ተንትናለች፡፡ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹን በትንታኔ አብራርታለች፡፡ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ በመጠቀም ጥናቷን አብራርታ ተግባራቸውን በማሳየት በመከፋፈል ለመተንተን ሞክራለች፡፡ የጥናቱ ደካማ ጎን በምእራፍ አንድ ላይ የጥናቱን ዳራ እና የምርምር ጥያቄዎች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ቢሆኑም አለመካተቷ ደካማ ጎኑን ያሳየናል፡፡ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ገዳም ላይ መመስረቱ፣ አካባቢው እንጦጦ መሆኑ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹን ማጥናቱ ልዩነታችን ደግሞ ጥናታችንን ያደረግንበት ስፍራ እና የመተንተ ስልቱ ነው፡፡

አቤል አሰፋ (2008 ዓ.ም) "የጣራ ገዳም ዋሻ ተክለሀይማኖት አብያተ ክርስቲያናት በዙሪያቸው የሚነገሩ ተረኮች ጥናት፡፡" የጥናቱ ዓላማ በገዳማቱ ስለ ሀይማኖት አስተምህሮ የተለየ ትኩረት የሚሰጡትን ጉዳይ አስተምህሮቻቸውና ታሪካቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ እንዴት እንደተገለገሉበት ማሳየት እና በአብያተ ክርስቲያናቱ ከሚነገሩት ተረኮች ጋር ተያይዘው የሚጠቀሱ ቁሳዊ ባህሎቹን ማሳየት ነው፡፡ የጥናቱ ጠንካራ ጎን የሶስቱንም አብያተ ክርስቲያናት ተረኮች በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ ዘዴ ሰብስቦ በተግባራዊና በተረክ ንድፈ ሀሳብ ተንትኖ አቅርቧል፡፡ የጥናት ደካማ ጎን በምእራፍ አንድ ላይ የምርምር ጥያቄዎችን አለማካተቱ፣ ምእራፍ ሁለት ተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ላይ በትምህርት ክፍሉ በርካታ ጥናቶች የተደረጉ ቢሆንም አጥኚው ግን የተወሰኑትን ብቻ ማየቱ ተገቢ አልነበረም፡፡ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በቤተክርስቲያን ተረኮች ላይ እና የመተንተኛ ስልት ሲሆን ከእኔ ጥናት ጋር የሚለየው የጥናቱ ቦታ እና የእርሱ ጥናት የተመሰረተበት ገዳም የተለያየ በመሆኑ እና ከተረኩ ጋር ቁሳዊ ባህልን ማጥናቴ የአቀራረብ ስልት ከእኔ ጥናት ጋር ያለያየዋል፡፡

ወንድወሰን ሞላ (2007 ዓ.ም) "በጻድቅኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ጥናት" የጥናቱ ዓላማ፡- በገዳሙ የሚነገሩ ተረኮችን መተንተን፣ መመርመር፣ ተረኮቹ ውስጥ የዘለቁትን ሚታዊ ሀሳቦች መፈተሽ፣ የገዳማውያኑ እና የአካባቢው ማህበረሰብ ትስስር

በተረኮቹ አማካኝነት መመርመር ነው፡፡ መረጃዎቹንም በተግባራዊና በተረክ ንድፈ ሀሳብ ተንትኗል፡፡ በጥናቱ ምልከታና ቃለ መጠይቅን ዘዴዎች ለመረጃ መሰብሰቢያነት ተገልግሏል፡፡ የጥናቱ ጠንካራ ጎኖች፡- አጥኚው የገዳሙን አመሰራረት የሚያሳዩ ተረኮችን ሰብስቦ ከፋፍሎ በመመደብ ተንትኗል፡፡ በንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ጥናቱን አብራርቶ አቅርቧል፡፡ አላማው ግብ እንዲመታ ያቀረባቸው መረጃዎች ጥሩ ናቸው፡፡ ተረኮቹም የአካባቢውን ህልውና የማስጠበቅ ሚና እንዳላቸው በጥናቱ ግኝት አሳይቷል፡፡ የጥናቱ ደካማ ጎን፡- በተዛማጅ ጽሁፍም ሶስት በትምህርት ክፍሉ የተሰሩ ጥናቶችን ብቻ መፈተሹ የሌሎችን አጥኚዎች ጥንካሬና ድክመት አለማካተት ሲሆን ሁለታችንም በቤተ ክርስቲያን ተረኮች ላይ መስራታችንና የመተንተኛ ስልታችን ይመሳሰላል፡፡ ልዩነታችን ደግሞ ጥናት ያደረግንበት ስፍራ እኔ ተረክ እና ቁሳዊ ባህል ላይ ማጥናቴ ያለያየናል፡፡

ዮሴፍ ቦኪ (2007 ዓ.ም)፡፡ "የደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም ታሪክ ጥናት፡፡" አላማው በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩ ተረኮችን መመርመር፣ መፈከር እና መተንተን እና የተረኮቹን ፋይዳ ማብራራት ነው፡፡ በጥናቱ ምልከታንና ቃለመጠይቅን ተጠቅሟል፡፡ መረጃዎቹ በገላጭ በተግባራዊ እና በስነ ተረክ ንድፈ ሀሳብ ተተንትነዋል፡፡

በምዕራፍ ሁለት የተለያዩ ምሁራንን በመጥቀስ አብራርቶ አቅርቧል፡፡ ተረኮቹንም በትንታኔ አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ተረኮቹን በትንታኔ ማብራራቱ ሲሆን የጥናቱ ደካማ ጎን ጥናቱ ላይ የሀሳብ መደጋገም መታየቱ ነው፡፡ ሌላው የመስክ መረጃዎቹን ስብስብ መረጃ አቀባዮች 40ዎቹ እድሜ ላይ ያሉ ብቻ ከመሆኑ በእድሜ ገፋ ያሉትን ቢያካትት ለጥናቱ የተሻለ መረጃዎችን ያገኝ ነበር፡፡ የተሰበሰቡት ተረኮች 97 መሆናቸው ጥሩ ጎን ቢሆንም የመረጃ አቀባዮቹ ቁጥር እና የተረኩ ቁጥር ግን አይመጣጠንም፡፡ ይህም ተአማኒነት ይቀንሰዋል፡፡ የዮሴፍን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ተረኮቹ ላይ ማተኮሩ ሲሆን ከእኔ ጥናት ጋር የሚያለያየው የጥናቱ ስፍራ ከተረኮቹ በተጨማሪ ቁሳዊ ባህሎቹን ማጥናቴ እንዲሁም የተጠቀምኩት የትንተና ስልት ነው፡፡

ፍፁም ኩራባቸው (2006 ዓ.ም) "የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት" በሚል ርእስ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ አላማው ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ ምሳሌ ዘይቤና ትእምርት አንድምታ መርምሮ እና ተምሳሌታዊ ፍቺያቸውን ፋይዳውንም በማብራራት አቅርቧል፡፡ በጥናቱ ዘዴም ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ በምልከታ በርካታ ጉዳዮችን ከነአውዳቸው ተመልክቷል፡፡ ይህም

የጥናቱ ጠንካራ ጎን ነው፡፡ በተዛማጅ ጽሁፉም ሰባት ጥናቶችን ቃኝቷል፡፡ ሶስቱ በትምህርት ክፍሉ የተሰሩ ሲሆኑ 4ቱ ደግሞ ከትምህርት ክፍሉ ውጭ የተሰሩትን ጥናቶች በጥልቀት ፈትሿል፡፡ ከአላማቸው እስከ መጨረሻ ግባቸው ድረስ መርምሯል፡፡ የጥናቱን ጠንካራ እና ደካማ ጎንም አብራርቷል፡፡ እዚህ ላይ የጥናቱ ደካማ ጎን በትምህርት ክፍሉ በርካታ ጥናቶች የተደረጉ ቢሆንም አጥኝው ግን ሶስት ጥናቶች ብቻ ማየቱ ተገቢ አልነበረም፡፡ በጥናቱ ተግባራዊ የተረክ እና ቁሳዊ ባህልን ፅንሰ ሀሳብ በስፋት ተንትኗል፡፡ ጠንካራ ጎኑ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ የሀይማኖት ማፅኛና የማንነት መገንቢያ መሣሪያዎች መሆናቸውንም አረጋግጧል፡፡ ጥናቱ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ገዳም ላይ መመስረቱ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹን ማጥናቱ የመተንተኛ ስልቱ የሚያለያየው ደግሞ ጥናታችንን ያደረግንበት ስፍራ እና የደረስንበት ግብ ይሆናል፡፡

ቴዎድሮስ ይበልጣል (2005 ዓ.ም) "የደብረወርቅ ማርያም ገዳም አመሰራረትና በገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና" ዋና አላማው ከአመሰራረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቁሳዊ ዝርው ተረኮች በገዳማውያኑና በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ የሚኖራቸውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ መረጃውን በቃለ መጠይቅና በምልከታ ዘዴ ሰብስቦ በገላጭ የምርምር ዘዴ ተተንትኗል፡፡ የጥናቱ ጠንካራ ጎን በንድፈ ሀሳባዊ ዳራ አጥኚው ስለ ተረክ ምንነት አይነቶችና ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ጥናቱን አብራርቶ ማቅረቡ አጥኚው የገዳሚን አመሠራረት የሚያሳዩ የተለያዩ ተረኮችን ሰብስቦ ተግባራቸውን በማሳየት ተረኮቹ እንደሚያነሱት ጉዳይ በይዞታ ለመመደብ እና ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም ቃላዊ ተረኮቹ የእምነቱ ተከታይ እምነቱን ፀንቶ እንዲቆይ በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳላቸው አሳይቷል፡፡ ደካማ ጎኑ የጥናቱ ዘዴ ላይ ስለ ገላጭ ዘዴ ምንነት እና ለምን እንደመረጠው አብራርቶ አላቀረበም፡፡

ይህ ጥናት ገዳም ላይ መመስረቱ፣ ተረክን ማንሳቱ፣ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን በመተንተኛ ስልትነት መጠቀሙ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ከእኔ ጥናት ጋር የሚለያየው ጥናት ያደረግንበት ገዳም የተለያየ መሆኑ ሲሆን በተጨማሪም ከተረኩ ጋር ቁሳዊ ባህልን ማጥናቱ ነው፡፡

ተስፋዬ ተገኝ (2003 ዓ.ም) "በደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሠራረትና ቁሣዊ ባህል ጥናት" ጠንካራ ጎኑ ጥናቱ እንደ አጠቃላይ ሲታይ የገዳሙን አመሠራረት ተረኮቹን በማንሣት፣ ቁሣዊ ባህላቸውን በመመርመር ተምሣሌታዊ ፍቺ ለመስጠትና ፎክሎራዊነታቸውን በትንታኔ ለማሣየት መነሣቱ ገዳማዊ ህይወት አጀማመርና

መስፋፋት በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል አይነታቸውን በዝርዝር በጥናቱ አካቷል፡፡ ደካማ ጎኑ ጥናቱ ዳራ የለውም የጥናቱ ወሰን የዳራውን ሀሳብ ይዟል፡፡ የጥናቱ ዘዴ ላይ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ምልከታና ቃለ መጠይቅን እንደተጠቀመና መረጃዎቹን በገላጭ የምርምር ዘዴ ተንትኗል ሆኖም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹና የትንተና ስልቶቹ በስርዓት አልቀረበም፡፡

በተዛማጅ ጽሁፍም አላማቸውንና የጥናቱን ዝርዝር ሀሳብ አላቀረበም ደካማና ጠንካራ ጎናቸውና፣ ዘዴያቸውን፣ አላማቸው ግብ መምታት አለመምታቱን አይገልጽም ትንታኔው ላይ ቁሶቹ በስፋት አልተተነተነም፡፡ ተረኮቹ ቁሳዊ ባህሎቹን ንድፈ ሀሳብ በግልጽ አላሳየም መረጃዎቹ በጣም የላላ ነው፡፡ በምዕራፍ ሦስት የቀረበው መረጃም ግልፅነት ይጎድለዋል፡፡ በምዕራፍ አራት ተምሳሌታዊ ፍቺ፣ ፋይዳ የሚል ነገር አላነሳም፡፡ የተስፋዬ ጥናት በገዳም አመሠራረትና ቁሳዊ ባህል ላይ መስራቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ልዩነታችን ደግሞ በእኔ ጥናት የተረኮቹና የቁሶቹን አገልግሎት አብራርቻለሁ፡፡ ሌላው የተመሠረተበት ገዳም ቦታ እና በመተንተኛ ስልት እና በአቀራረብ ስልት ልዩነት በመካከላችን አለ፡፡

ሞገስ ጀምበር 2003 ዓ.ም "ከዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሠራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና አምልኳዊ ስርአቶች" ጠንካራ ጎኑ በዚህ ጥናት ተረኮች ገዳማዊ ህይወትን የመትከልና የማጠናከር ተግባር እንዳላቸውም ገልጿል፡፡ የአምልኳዊ ስርአቶችም ገዳማዊ ህይወትን የማፅናት ተግባር እንዳላቸውም አሳይቷል፡፡ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተገለገለባቸው ዘዴዎች ምልከታና ቃለ መጠይቆች ናቸው፡፡ የተመረጠው ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ አላማውን አሳክቶለታል በጥናቱ የአባሪ ክፍሎችም ፎቶዎች እና የቃለ መጠይቅ መረጃዎችን ማስቀመጡ የጥናቱን ጥንካሬ ያሳያሉ፡፡ የጥናቱ ደካማ ጎን የጥናቱ ዳራ ስለተረኩና ቁሳዊ ባህል ጉዳዮችን በማንሣት ማመልከት ሲኖርበት ሰፊውን ገለፃ ያደረገው ስለ ኢትዮጵያ ስነ ቃል ስብስብና ጥናት ነው መረጃዎችን የሰበሰበበት ዘዴ ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታና የታተሙ ፅሁፎች እንደሆኑ ቢገልፅም አብራርቶ አላቀረበም፡፡ ተዛማጅ ስራዎችን በሚቃኝበት ወቅት የአጥኚዎቹን ጥንካሬና ድክመት አለማካተቱ ሲሆን የእኔ ጥናት ከሞገስ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለታችንም በገዳማዊ ተረኮች የአመሰራረት ላይ መመስረታችን እና የመተንተኛ ስልታችን ነው፡፡ ጥናቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያለው ልዩነት የእኔ ጥናት ተረክና ቁሳዊ ባህል ላይ ማጥናቴ የእሱ ጥናት ተረክና አምልኳዊ ስርአቶችን የቃኘ ነው፡፡ የደረስንበት ግብም ያለያየዋል፡፡

ምህረት ተስፋዬ (2003 ዓ.ም) "ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋራ ተያያዥነት ያላቸው ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት" መረጃዎቹን በቃለ መጠይቅና በምልከታ ዘዴ ሰብስቦ

በገላጭ የምርምር ዘዴ ተንተኗል። ጠንካራ ጎኑ የጥናቱ ዓላማ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ በገዳማውያን ዘንድ እምነትን በመትከልና በመጠናከር ረገድ ያላቸውን ሚና ማሳየት ነው። ሌላው ቁሳዊ ባህሎቹን ተንተኗል አላማው ግብ እንዲመታ የቀረባቸው መረጃዎች በጣም ጥሩ መሆናቸው እንደ ጠንካራ ጎን ይታያሉ። ሌላው በተረኮቹና በቁሶቹ የስፍራውን ህልውና የማስጠበቅ ሚና እንዳላቸው በጥናቱ ግኝት ውስጥ አሳይቷል። ደካማ ጎኑ ዘዴው ላይ ቃለ መጠይቁና ምልከታ  ዘዴ ለምን እንደተመረጡ እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚውሉ ማስረጃ አያቀርቡም። የተጠቀመችው ተምሳሌታዊ መስተጋብራዊ ንድፈ ሀሳብ ምንነት የተብራራ ነገር አለመግለጽ፣ ተዛማጅ ጥናቶችን በጥልቀት አለማየት በምዕራፍ ሦሥት በተረኮቹ ላይ በቂ የሆነ ማብራሪያዎች ሲሰጥባቸው አይታይበትም። በምእራፍ አራትም ቁሶቹ ላይ ተምሳሌታዊ ፍቻቸውንም ሆነ ፋይዳቸውንም አያነሳም። ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በገዳም ላይ መመስረቱ እና ተረክና ቁሳዊ ባህል ማጥናቱ። ነገር ግን የእኔ ጥናት የሚመሰረትበት ቦታ እና የመተንተኛ ስልቱ ከእኔ ጥናት ጋር ይለያያል።

በአጠቃላይ ከላይ ያሉት ጥናቶች ውስጥ 9 ሲሆኑ ጥናቶቹ ያተኮሩት የገዳሙ አመሰራረትና ተረክ፣ ቁሳዊ ባህል፣ ተረክና ቁሳዊ ባህል፣ ተረክና አምልኳዊ ስርአቶች፣ ተረክ ከስርዓተ ክዋኔ ጋር ተጣምሮ ፎክሎራዊ ገጽታን መሰረት አድርገው የተሰሩ ናቸው። የእነዚህ ጥናቶች ልዩነት ለማጥናት የተመረጡበት ስፍራዎች ናቸው። ጥናቶቹ ውስጥ የተጠኑ ተዛማጅ ስራዎች ላይ የእነሱ ጥናት ከቀደሙት ጥናቶች የሚለያዩባቸው የሚመሳሰሉባቸውም ሆነ የተለየ አዲስ ነገር ይዞ የመጣውን ምንነት አለማብራራት ይታይባቸዋል። ከእነዚህ ጥናቶች ውስጥ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉም የሚለያዩም ጥናቶች አሉ። በእኔ ጥናት አካባቢ የሚነገሩ ቃላዊ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች በሚመሰረቱበት ቤተ ክርስቲያን በመስራቹ አንዳንዶቹ ደግሞ በመተንተኛ ስልቱ ስለሚለያዩ እና የተገኘው ውጤት የተለያየ ነው።

## ምዕራፍ ሦስት

# 3. አካባቢያዊ ዳራ

## 3.1. የእንጦጦ አጠቃላይ ገጽታ

የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን የተተከለበት ቦታ ውብና ደስ የሚያሰኝ፣ በዙሪያው የሚገኘውን መልክአ ምድር ለመቃኘት የሚያስችል በጎብኚዎች የሚዘወተር ስፍራ ነው። ከዚህ ተራራ ላይ በመኾን በስተግራ የኤረርን ሰንሰለታማ ተራራ፣ በፊት ለፊት ደግሞ የዝቋላን ተራራና የፉሪን ጋራ ለማየት ይቻላል። በስተቀኝ በሱልልታ ሜዳ የሚታየውን ሳተላይት ጣቢያና የሰላሌ ከፍተኛ ቦታዎች በርቀት ይታያሉ። የአዲስ አበባን ከተማም በስተሰሜን፤ በስተምዕራብና በስተምሥራቅ አጅቦት ለከተማዉ ደጀን ኾኖታል። ከዚህም በላይ እንጦጦ የመስሕብ ስፍራ ናት፤ ከ800 ጫማ በላይ ከፍታ ያላት በመኾኑ ነፋሻማና በዙሪያዉ ያለዉ የመሬት አቀማመጥ ተፈጥሮን ለማድነቅ አመቺ ነው። በዚህ ድንቅ የኾነ የተፈጥሮ ጥበብና ነፋሻማ ንጹህ አየር ምክንያት ብዙ ጎብኚዎች ከውጭ ከሀገር ውስጥ ሰዎች በመምጣት የዕረፍት ጊዜያቸውን በዚሁ ሥፍራ ያሳልፋሉ። በዚህ ሥፍራ ላይ በኪነ ሕንጻዊ ውበት የተደነቀውና ለየት ያለ አሠራር ያለው የቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ይገኛል። ቤተክርስትያኑ በእንጦጦ ተራራማና ደጋማ አከባቢ ይገኛል። ዐፄ ምኒልክ በ1870 ዓ.ም አካባቢ 50 ሺህ ሰራዊታቸውን ይዘው እንጦጦ አካባቢ ሰፍረው እንደነበር ታሪክ ያስረዳል *(የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት 2ኛ ዕትም ታኅሣሥ 2000፣7)።*

## 3.2. የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር

መልአከ ሰላም አባ ሳሙኤል አስፋው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የርእሰ አድባራት ወገዳማት እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተ ክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ ስለአሁኑ እና ቀደምት የቤተክርስቲያኑ አስተዳደራዊ መዋቅርን እንደሚከተለዉ ተንትነዋል።

ይሄ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ የርእሰ አድባራት እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን በመቁነን የሚተዳደር ሳይኾን በሰበካ ጉባኤ የሚተዳደር ነው። የቁምስና ማዕረግ ከምንኩስና ማዕረግ በላይ ስለኾኑ በቁምስና ማዕረግ ያሉ አሁን ሌላው ቤተ ክርስቲያን እና ደብር ላይ ቄሶች አለቃ ኾነው ይሾማሉ። እዚህ ግን ቄሶች አለቃ ኾነው አይሾሙም፤ ነገር ግን በቅስና ሊያገለግሉ ይችላሉ። ይኼ የኾነበት ምክንያት ጥንታዊ ርእሰ

አድባርነቱን እና ዕድሜ ጠገብነቱ ነው፡፡ “ርእሰ” የሚለው ከኹላቸውም የበላይ ለማለት ነው፡፡ ርእሰ አድባራት እንጦጦ ደብረ ኃይል እዚህ ቦታ ላይ የሚሾመው ሀላፊ አለቃ “መልአከ ኃይል” በመባል ይጠራል፡፡ በ1948 ዓ.ም የተሠራችው የመርካቶ ራጉኤል ቤተክርስቲያንም ደብረ ኃይል የሚል ስያሜ የተሰጠው ጽላቱ እና ንዋያተ ቅድሳቱ ከዚህ ከእንጦጦ ስለኼደ ነው፡፡ (መልአከ ሰላም አባ ሳሙኤል አስፋው 8/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)፡፡

*መተዳደሪያ*

ዐፄ ምኒልክ ለእንጦጦ ማርያም እና ለቅዱስ ራጉኤል የሠጡት ርስት አላቸው፡፡ አጠቃላይ በባሕር ዛፍ የተሸፈነው በሙሉ የዚህ የቤተክርስቲያኑ ርስት ነው ከአስፋልት ጀርባ በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ ወደ 3-5 ሄክታር የርስት ቦታ አለው፡፡ በዘመኑ የነበሩ አባቶች እያረሱ ነበር ስንዴው እና ሌሎች እህሎች ገቢ የሚያደርጉት፤ ከዚህ ወደ ሽንቁሩ መኼጃም ርስትም ነበረው፡ ፡ ነገር ግን ተመልካች በማጣቱ ገበሬዎች እየገፉ ትንሽ ቀርቶታል፡፡ ወደ 12 ሄክታር መሬት ገብስ እና ስንዴ እየተዘራ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ይህ ርስትም የቤተክርስቲያኑ ነው፡፡

በ1882 ዓ.ም ጠቅላላ ወደ 100 ሄክታር የሚኾን ቦታ፣ በጊዜው የነበሩ የሰበካ ጉባኤ አባላት፣ በከተማ ያሉ ባለሥልጣናት መጥተው ዙሪያውን ዐይተው 29 የወሰን ድንጋዮች በመትከል 3 ገጽ ጀርባ ላይ አሠርተው የቤተ ክርስቲያኑን ወሰን ኹሉ ስማቸውን ጠቅሰው በዚያ በቤተ ክርስቲያኑ ማንም እንዳይገባ ብለው የተፈራረሙት የሰነድ ማስረጃ አለ፡፡ ከጊዜ በኋላ ከዚያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዕርከን በመሥራት ዘመናዊ የኾኑ ዕፀዋቶችን መትከል ጀመረ፡፡ የቤተ ክርስቲያኑ አባቶች ዕፀዋት ስለማይቃወሙ ዝም አሏቸው፡፡ ከተተከሉ በኋላ ግን ባለስልጣኑ ባሕር ዛፉ የእኛ ነው ቤተ ክርስቲያንዋም ቦታው የኛ ነው በማለት ጉዳዩ በክርክር ላይ ይገኛሉ፡፡

ቀደም ሲል በኦሮሚያ ክልል የተሠሩ ሕጋዊ የኾኑ የካህናት ቤቶች አሉ ትዳር ያላቸው ካህናት አገልጋይ የሚኖሩበት 2004 ዓ.ም ወደ 22 ክፍል ቤቶች ተሠርተው ተከራይተው ገቢው ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ይውላሉ፡፡ (መጋቤ ምስጢር አባ ስብሐት አድማሱ 09/08/2012 ቃለ መጠይቅ)

የአሁኑ የቤተክርስቲያኗ አስተዳዳሪ እንደሚገልፁት ሌላዉ ገቢ በምእመናኑ በተለያየ ጊዜ የሚሰጠዉ የዐሥራት፤ የስእለት እና መባ ስጦታዎች ናቸው፡፡ በቤተክርስቲያኑ 65 አገልጋዮች አሉ፡፡ የሚተዳደረው በሰበካ ጉባኤ እና በሙዳይ ምጽዋት ነው፡፡ የቤተክርስቲያንዋ ይዞታ ቦታ

በካርታ ውስጥ የተካተተ ነው። (መልአከ ኃይል የቆሞስ አባ ሳሙኤል አስፋው የ10/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)

### 3.3. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚከበሩ ዐበይት በዓላት

በንጉሡ በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የንግስ በዓላት በደማቅ ሹኔታ እራሳቸው ንጉሡ ባሉበት ይከበር እንደነበር ይነገራል። ንጉሡም፣ በተለይም የመስከረም 1 እና ግንቦት 1 ቀን በዓለ ንግሡን ያከብሩ ነበር። ከእንጦጦ ወደ አዲስ አበባ ከወረዱም በኋላ ታቦቱን ማንገሣቸውን አላቋረጡም ነበር። በወቅቱ ታቦቱ ሲወጣና ዑደቱ ሲደረግ ዐስራ ኹለት ጊዜ መድፍ ይተኮስ ነበር። የጠመንጃ ተኩሱ እጅግ የተጧጧፈ ነበር ምኒልክ በከፍተኛ አጀብ በቤተክርስትያኑ ይገኛሉ፤ የእንግሊዝ ዲፕሎማቶችም በበዓሉ ስፍራ ላይ ይገኙ ነበር። 15,000 ያህል ወታደሮች ይሰለፋሉ ንጉሡ ከመቀመጫቸው ተነሥተው ጠመንጃቸውን አንግተው ሦሥት ጊዜ በዝግታ በቤተክርስትያኑ ከታቦቱ ጋራ ዑደት ሲያደርጉ የደመቀና የሞቀ በእጅጉ ሐሤት የሚንጸባረቅበት መንፈሳዊ ሥርዓት እንደነበር ይነገራል። በእንጦጦ ራጉኤል የሚከበሩ ዐበይት በዓላት እንደሚከተሉት ተዘርዝረዋል። (ርእሰ ደብር አጋፋሪ ሰለሞን ጌታነህ 04/02/2013 ቃለመጠይቅ)

*መስከረም 1 ቀን የቅዱስ ራጉኤል በአለ ሲመት*

የሊቀመናብርት ቅዱስ ራጉኤል በመስከረም 1 ቀን የምናከብረው በዓለ ሲመቱን በብርሃናት ላይ የተሰጠውን ሥልጣን መሠረት በማድረግ ሲኾን መጋቤ ብርሃናት ቅዱስ ራጉኤል በተራዳኢነቱ በጠበሉም ሚያዚያ 17 የተሰረቀውን ንብረቱን ግንቦት 1 ቀን 1999 ዓ.ም በ15 ኛው ቀን ማስገኘቱ በቂ ምስክር ስለኾነ ይማፀኑታል፡(የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት ኹለተኛ ዕትም ታህሳስ 2000፡ 33)።

*ታኅሣሥ 1 ቀን ነብዩ ቅዱስ ኤልያስ መሰዋእት ያሳረገበት*

ቴስብያዊ ኤልያስ በንጉሡ በአክዐብና በንግሥቲቱ በኤልዛቤል ዘመን አምልኮተ እግዚአብሔር በመተው በአምልኮተ ጣዖት ሕዝቡን በማሠማራታቸው በዘመኑ የነበረው ነቢይ ቅዱስ ኤልያስ ስለአምልኮተ እግዚአብሔር ተነሣሥቶ አስተምሮ መሥዋዕትነቱን ያሳረገው ታኅሣሥ 1 ቀን

ስለኾነ ምእመናን በጸሎትና በአንቃዕድዎ ያከብሩታል፡፡ (የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት ኹለተኛ ዕትም ታህሳስ 2000፡ 33)፡፡

### ጥር 6 ቀን ነብዩ ቅዱስ ኤልያስ ያረገበት

በሕይወት አርጓል ሊቀ ብርሃናት ቅዱስ ራጉኤል በችግሩ ኹሉ ሳይለይ ይረዳው ስለነበረ በዓሉ ከዕለቱ ጋር ሊተባበር ችሏል፡፡ ድርሳነ ኤልያስ ተመልክት (መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ 16-18)፡፡ የነቢዩ ኤልያስ ልደት ነሐሴ 22 ቀን ነው፡፡(የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት ኹለተኛ ዕትም ታህሳስ 2000፡ 33)፡፡

### ኅዳር 24 ኻያ አራቱ ካህናተ ሰማይ በዓል

ኅዳር 24 ቀን የሚከበረው የኻያ አራቱ ካህናተ ሰማይ በዓል ነው፡፡ ኻያ አራቱ ካህናተ ሰማይ በጽርሐ አርያም በሰዓትና በደቂቃ ሳይገደቡ ሰማያዊ አምላክን የሚያገለግሉ ሰማያውያን መላእክት ናቸው፡፡ ለሰው ወገን ይማልዳሉ፣ የቅዱሳንን ጸሎት ያሳርጋሉ፡፡ በዙፋኑ ዙሪያም ኻያ አራት ዙፋኖች ነበሩ፤ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ኻያ አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ነበር፡፡ (ራእ. 4፡4)፡፡ ካህናተ ሰማይ ነጭ ልብስ ለብሰው መታየታቸው የንጽሕናቸውና የቅዱስናቸው መገለጫ ሲኾን፣ በራሳቸው ላይ የተቀዳጁት ዘውድ በእግዚአብሔር ዘንድ የተቸራቸውን ዘመን የማይሽረውን ክብር ያሳየናል፡፡ "ኻያ አራቱ ሊቃናት በበጉ ፊት ወደቁ እያንዳንዳቸው በገናና የቅዱሳን ጸሎት የኾነ ዕጣን የሞላበት የወርቅ ዕቃ ያዙ፡፡" (ራዕ 5፣8) እንዲል ጽንሓሕ ይዘው የቅዱሳንን ጸሎት በጸሎት ዕጣን ያሳርጋሉ፡፡ ምእመናን በዚህ ዓለም ሳሉ የጸለዩትን ጸሎት፣ ምድራውያን ካህናት ያጠኑትን ማዕጠንት ተቀብለው ምዑዝ በኾነ ዕጣናቸው መንበረ ጸባዖትን እያጠኑ ከምስጋና ጋራ ጸሎታችንን ኾነ መሥዋዕታችንን ያሳርጋሉ፡፡ ኹሉን ቻይ የኾነ አምላክ ተቀብሎ የቸርነቱን ሥራ ይሠራልናል ብለው ያምናሉ፡፡ (የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት ኹለተኛ ዕትም ታህሳስ 2000፡ 34)፡፡

### ግንቦት 1 ቅዱስ ራጉኤል ብርሃናት ይዞ ያከበረበት

ግንቦት 1 ቀን እመቤታችን ድንግል ማርያም በአድባረ ሊባኖስ (ቤሩት) በተወለደችበት ቀን ብርሃናትን ይዞ ዕለተ ልደቷን በማክበሩ ነው በዚህ ቀን በዓሉ በድምቀት ይከበራል፡፡ (የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት ኹለተኛ ዕትም ታህሳስ 2000፡ 34) ፡፡



ምስል1 ፡ እንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን የመስከረም አንድ (ቅዱስ ራጉኤል) በዓል ሥነስርዓት ምስል (01/01/2013 በሳምራዊት )

# ምዕራፍ አራት

## 4. በእንጦጦ ቅዴስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮች ትንተና

### 4.1. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮች

የቤተክርስቲያን ታሪክ ማለት የክርስትና እምነትና አማኞች ታሪክ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ቤተክርስቲያን የተመሰረተችው በክርስቶስ ደም ስለሆነ ነው፡፡ የሐዋ.ሥራ 20/28

ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት "የቤተክርስቲያን መረጃዎች" በሚለው መጽሐፉ ስለ እንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን አመሰራረት እንደጻፈው በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በእንጦጦ ተራራ ላይ የሚገኝ ደብር በ1877/78 ዓ.ም ዐፄ ምኒልክ ወጨጫ ላይ ከተሙ፡፡ በመቀጠልም 1882 ዓ.ም ወደ እንጦጦ መጡ፡፡ የቀድሞ የዐፄ ዳዊት ፍርስራሽ በተገኘ ግዜ ዐፄ ምኒልክ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በኛ ዘመን ከተገለጠ መስራት ይገባናል ብለው ስራው ተጀመረ፡፡ የቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን የመሰረት ድንጋይ የተጣለው በ1877 ዓ.ም ነበር፡፡ ታቦቱ የመጣው ከጎንደር መሆኑ ይነገራል፡፡ በዐፄ ምኒልክ እና በዐፄ ዮሃንስ መካከል የሊቼ ስምምነት 1871 ዓ.ም ከተፈረመ በኂላ ዐፄ ምኒልክ ታቦቱን ከጎንደር አመጡት ይባላል(አንዳንዶች ደግሞ ከስምምነቱ በኂላ ዐፄ ዮሃንስ ከርሳቸው ጋር የነበረ የቅዱስ ራጉኤል ታቦት ሰጧቸው ይላሉ፡፡) በሌላ በኩል ደግሞ ዐፄ ምኒልክ መምህር ወልደመስቀል መምህር ገብረህይወት፣ መምህር ደምሴ እና አባ ወልደመስቀል የተባሉትን መርጠው ወደ ጎንደር በመላክ ታቦቱን ሲያስመጡ ዐፄ ዮሃንስ ባለ ስምንት መዐዘን ድንኳን መስጠታቸው ይተረካል፡፡ (ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፣ 2012፡ 293).

እንጦጦ በዐሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን የንጉሥ ዳዊት ከተማ ነበረች፡፡ ከወጥ ድንጋይ አስፈልፍለው ያሳነጹት የሰባት መቶ ዓመት ዕድሜ ባለጸጋ የዋሻ ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ምንም የመጎዳትና የመጎሳቆል ምልክት ሳያሳይ ከነሙሉ ግርማ ሞገሱ እንጦጦ ራጉኤል ሕንጻ ቤተክርስቲያን ጎን በቀኝ በኩል አለ፡፡

ይህ ዋሻ በተለይ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጥ የነበረው በጦርነትና ቤተክርስቲያን በማቃጠልና በማውደም ዘመቻ ከተለያየ ቦታ የመጡትን ጽላቶችን፣ ወርቅና የተለያዩ ንዋየ ቅድሳትን ለመደበቅ ነበር፡፡ ዋሻው ሦስት ክፍሎች ያሉት ሲኾን እንደ መቅደስ፤ ቅድስት እና ቅኔ ማሕሌት ያገለግል ነበር፡፡ በዮዲት ጉዲት ዘመን በሽሽት ወደ ዝዋይ ደሴት ከተወሰዱት ጽላቶች ውስጥ ወደ አንኮበር፣ ከዚያም ወደ እንጦጦ ያመጡትን ጽላት ወስደው ዋሻው ውስጥ

እንዲቀደስበት አድርገዋል፡፡ ሕንጻ ቤተክርስትያኑንን ለመጀመር ከመናገሻ ዕንጨት በማስመጣትና ድንጋይ በመሰብሰብ በወቅቱ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ አራት መቶ ምሕላ ተይዞ በጳጳሱ እጅ በየማእዘኑ አራት የመሠረት ድንጋይ አኑረዋል፡፡ (ዲያቆን ዮሃንስ ወልደጊዮርጊስ 09/01/2013፡ ቃለመጠይቅ)

የእንጦጦ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ባለሦስት ፎቅ ሕንጻ ሲኾን ፎቁ የተከፈለው በዕንጨት ነው፡፡ ጣራው፣ ማገሩ እና ወራጁ በጣውላ የተሠራ ነው፡፡ የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተ ክርስትያን አመሠራረት እና ታሪክ በመጀመርያ በ1262 ዓ.ም የነገሡት ዐፄ ይኩኖ አምላክ በዋናነት ቤተ አማራ ደጋውሎ መካነ ሥላሴ አድርገው የእንጦጦ ተራራን በኹለተኛ ከተማነት እንደመሠረቱት በዚያ ጊዜ የእንጦጦ ተራራ በነገደ ጋፋት ቋንቋ እንዶጥናህ ተብሎ ይጠራ ነበረ፡፡ በ13ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት ዐፄ ይኩኖ አምላክ የያኔው እንዶጥናህን የአሁኗ እንጦጦ ኹለተኛ ከተማቸው አድርገዋት ነበር ፡፡ ከእርሳቸውም በኋላ ዐፄ ዳዊት በዚህ ስፍራ ላይ ቤተ መንግሥታቸውን አንጸዋል፡፡(መጋቤ ምስጢር አባ ስብሐት አድማሱ 09/01/2013፡ ቃለመጠይቅ)

በ1370 ዓ.ም የነገሡት ዐፄ ዳዊት በዚህ ተራራ ላይ ቤተ መንግሥታቸውን መሥርተው የከበሩ ዕቃዎች ወይም ንብረቶችን ማስቀመጫ በግምጃ ቤትነት የሚያገለግል የወርቅ፣ የአልማዝ ተያያዥነት ያላቸው ንብረቶች ማስቀመጫ የሚኾነው በ1375 ዓ.ም ከአንድ ወጥ ድንጋይ ሦስት ክፍል ዋሻ በማስፈልፈል ዋሻው እሰኪፈጸም ድረስ ሲገለገሉበት እንደቆየ ታሪክ ዘግቧል፡፡ አሁንም ዋሻው በቤተ ክርስትያኑ ግቢ ውስጥ ለጎብኚዎች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ከዚያ በኋላም በ1508 ዓ.ም ዐፄ ልብነ ድንግል ማራኪና ውብ የኾነ ቤተ መንግሥት አሠርተዉ በዚህ በእንጦጦ ተራራ ላይ አገልግሎት ሲሰጥ ከቆየ በኋላ በ1527 ዓ.ም ግራኝ መሐመድ መጥቶ የከበሩ ንብረቶቹን በመዝረፍ ከወሰደ በኋላ ቤተ መንግሥቱን አቃጥሎባቸዋል፡፡ ከዐፄ ልብነ ድንግል በኋላ ግን ለበርካታ ጊዜያት እንጦጦን የረገጠ ንጉሥ አልነበረም፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በስፍራው የነበረውን ኹሉ በማጥፋቱ ነበር፡፡ ግራኝ በወረራው ወቅት “እንዶጥናህ” “ዲልዲላ” የሚል ስያሜ ሰጥቶ ከ1527 ዓ.ም እስከ 1532 ዓ.ም ድረስ የጦር ስፍራው አድርጓት ነበር፡፡

በ1877 ዓ.ም አጠቃላይ የሥዕሉም፣ የግንባታውም፣ የጣራውም ሥራ ተከናውኖ ጽላቱ ለሰባት ዓመታት ዋሻ ውስጥ ከቆየ በኋላ ወጥቶ ኅዳር 27 አሁን በምናየው ቤተ መቅደስ ገብቶ ምርቃቱ ተከናወነ፡፡ የመጀመሪያው የተክሊል አቋቋም መምህር አለቃ ገብረሐና ናቸው፡፡ የዐፄ

ምኒልክ ጸሐፊ ሚኒስቴር ኾነዉ ሲያገለግሉ የነበሩ ደግሞ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረሥላሴ ወልደ አረጋይ ነበሩ። በዐፄ ምኒልክ ትእዛዝ የቤተ ክርስቲያኑ ስም "ደብረ ኃይል" ተባለ። የመጀመሪያው የቤተክርስትያኑ አስተዳዳሪ ጸሓፊ ትእዛዝ ገብረሥላሴ ወልደ አረጋይ ናቸው። በዚያን ወቅት በቤተ ክርስቲያኑ ከ300 በላይ ሊቃውንት እንደነበሩ እና መንፈሳዊ አገልግሎቱም ያማረ እና የተዋበ ነበር። ከ1872 ዓ.ም እስከ 1948 ዓ.ም ድረስ ባሉት ዓመታት እነ አለቃ ገብረሐናን ጨምሮ ከ 300 በላይ ሊቃውንት የነበሩ ሲኾን በቤተክርስቲያኑ ታሪክ ውስጥ ወርቃማው ዘመን ተብሎ ተመዝግቦ ይገኛል። (ዲያቆን ዩሃንስ ወልደጊዮርጊስ 2/2/12 ቃለመጠይቅ)

ሌላው ከቤተክርስቲያኑ ምሥረታ በፊት ቀደምት ጋራ ተያይዞ ከሚነገረዉ ትርክት አንዱ የዐፄ ልብነ ድንግል ኹለት ልጆች ጠብ ጋራ ተያይዞ የሚነገረዉ ትርክት ነው። ዐፄ ልብነ ድንግል ኹለት ልጆች የነበሯቸው ሲኾን ስማቸውም ሚናስ እና ያዕቆብ ይባሉም ነበር። ከዐፄ ልብነ ድንግል ቀጥሎ የነገሠውም ልጃቸዉ ዐፄ ሚናስ ሲኾን ንጉሡም በእንጦጦ ተራራ ቤተ መንግሥት አቋቁመው ለሰባት ዐመታት ይኖሩ ነበር። በአንድ ወቅትም የዐፄ ልብነ ድንግል ልጆች በሃይማኖት ምክንያት እርስ በእርስ ጠብ ተዳረሱ። በዚህ ጊዜ ዐፄ ሚናስ የእንጦጦ ቤተ መንግሥታቸው ትተው ወደ ጎጃም ሸሹ ። ንግሥናውም ወደ ጎንደር ዞሮ፤ ከዛ የዐፄ ፋሲል እና የዐፄ ባካፋ ንግሥና እናያለን። በዚህ ምክንያት ከዐፄ ሚናስ ጀምሮ እስከ ዐፄ ምኒልክ ድረስ የእንጦጦ ተራራ ያለ ምንም ቤተመንሥት ምድረ በዳ ኾነ ቀረ። (ዲያቆን ዮሐንስ ወልደጊዮርጊስ 6/1/2013 ፡ ቃለ መጠይቅ)።

ከዚህ ቀጥሎ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ቀደምት የአመሠራረት ፅንሰ ሐሳብን ከየት መነጨ ብለን ስንጠይቅ ታሪኩ ከዐፄ ልብነ ድንግል፣ ከነዐፄ ሚናስ፣ ከነዐፄ ፋሲል፣ ዐፄ በከፋ እንደዚሁም ዐፄ ቴዎድሮስ በኂላ ከነገሡት የኢትዮጵያ ንጉሥ ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ንግሥና ጋራ ተቆራኝቶ ይገኛል። ዐፄ ሚኒልክ በ1858 ዓ.ም ጥቅምት 27 አንኮበር መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን የሸዋ ንጉሥ ኾነው ተሾሙ። በትረ ሥልጣናቸው ከተቀበሉና ካጠናከሩ በኂላ ድፍን ኢትዮጵያ እየተዘዋወሩ ማሠሥ ጀመሩ። እየተዘዋወሩ ባለ ወቅት ዝዋይ ላይ ሲደርሱ በመልአኩ በቅዱስ ራጉኤል አማካኝነት አንድ ጻድቅ እና የእግዚያብሔር አገልጋይ የኾኑ ባሕታዊ የዐፄ ልብነ ድንግል ክብረ ነገሥት አሳይተው ኢትዮጵያን አንድ አድርገህ የምትገዛ መንግሥትህ ጸንቶ የሚኖረው የዐፄ ዳዊትን ቤተ መንግሥታቸው መሥርተውበት የነበረውን ቦታ ፈልገህ ስትመሠርት ነው ተብሎ ተነገራቸው ። ከዚያ የዐፄ ዳዊትን ቤተ መንግሥት ማፈላለግ ጀመሩ፡

፡ ሲያፈላልጉ ወደ እንጦጦ አቅንተው በዛ ተራራ እንደደረሱ የዐፄ ዳዊትን ቤተ መንግሥት ፍርስራሽ አገኙ፡፡ በዚያ ሰዓት ዐፄ ምኒልክ እጅግ ተደሰቱ፡፡ የቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ከመመሥረትህ በፊት የቅዱስ ራጉኤልን ጽላት ይዘህ ኺድ ተብለው ስለ ነበር በ1870 ዓ.ም እንጦጦ ተራራ ደረሱ፡፡ ከቦታው ደርሰው ቀድሞ ዐፄ ዳዊት የነበሩበት ቤተ መንግሥት እንጦጦ ላይ ታላቅ እልፍኝ ቤት አሠርተው ጥንታዊው የዐፄ ዳዊትን ዋሻ እና ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ ቦታ እስኪያስባርኩ ድረስ የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤልን ታቦተ ሕግ በአሠሩት እልፍኛቸው ውስጥ አሳርፈው እርሳቸው በድንኳን ሰንብተዋል፡፡ (ዲያቆን ዮሐንስ ወልደጊዮርጊስ 6/1/2013 ፡ ቃለመጠይቅ)፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በአራዳ እና ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቤተክህነት ስር የሚገኘው የርዕሰ አድባራት እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል እና ነብዩ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ጥንታዊ የተፈጥሮ ቋጥኝ ፍልፍል ዋሻ ሲኾን በኢትዮጵያ የነገሡት ዐፄ ዳዊት ከተማቸውንና ቤተ መንግሥታቸውን እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል እና ነብዩ ኤልያስ ቤተክርስቲያን መሥርተው ይኖሩ ነበር፡፡

ዐፄ ዳዊት ለጀግንነታቸውና ደግነታቸው የተላኩላቸው እጅ መንሻ ልዩ ገጸ በረከቶች ውስጥ አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ቅዱስ ግማደ መስቀሉ ሲኾን ኹለተኛዉ ደግሞ ንጉሥ ዳዊትን ልዩ የሚያደርጋቸው እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል እና ነብዩ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ በሰሜን ምዕራባዊ የሚገኘው ከቤተ ክርስትያኑ መመሥረት በፊት መቅደስ ፤ቅድስት እና የንጉሡና የንግሥቲቱ ቆሞ ማስቀደሻ ቅኔ ማሕሌት እንዲኖረው ተደርጎ ከተፈጥሮ ቋጥኝ ድንጋይ ተፈልፍሎ ዋሻ እሰሩ ፡፡

ዐፄ ምኒልክ እንጦጦ በከተማነት እንዲመርጡ እና እንዲቆረቁሩ መነሻ የኾናቸዉ ከላይ የተጠቀሰው ታሪካዊ መሠረት ሲኾን ሌላው ደግሞ በመሀል ሀገር የምትገኝ አማካይ ከፍታዋም ለጦር ስትራቴጂ አመቺ ኾና መገኘቷ ነበር፡፡ ከተማዋን ከቆረቆሩ በኋላ የልዑል እግዚአብሔርን ቤተ መቅደስን ለማሳነጽ የነበራቸውን ምኞት ቅዱስ ራጉኤል እንዲያስፈጽምላቸው ከለመኑ በኋላ ዕጨጌ ገብረ ሥላሴን ከታላቁ ከደብረሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አንድነት ገዳም አስመጥተው ቦታውን አስባርከው እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል የቤተክርስቲያን ሕንጻ መሠረት አኑረዋል፡፡ ዋሻውንም ካስባረኩ በኋላ ቤተክርስቲያን ተሠርቶ እስኪመረቅ ድረስ ታቦተ ሕጉን ከዋሻው አስገብተው ሲቀደስበት ቆይቷል፡፡ (የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ታሪክ በአጭሩ ፤በራሪ ወረቀት፤07/08/2006)

ዐፄ ሚኒልክ በእንጦጦ ላይ ከተከሏቸዉ አብተያተ ክርስቲያናት መካከል ቅዱስ ኡራኤል፤ ኤልያስ እና ሌሎችም ነበሩ። የቅዱስ ኤልያስ ቤተክርስቲያን በመፍረሱ በወቅቱ ተከሥቶ በነበረው ረኀብ ካህናቱ በማለቃቸዉ ከቅዱስ ራጉኤል ጋራ እንዲዳበል ተደርጓል።

"ከቤተ ክርስቲያኑ ምርቃት ጋራ ተያይዞ ከሚነገሩ ተረኮች አንዱ በ1876 ዓ.ም ራጉኤል ቤተክርስቲያን ሲመረቅ ከወልቃይት ጠገዴ አካባቢ አንድ ቀንድ ያለው ሰው እራሱን ሸፍኖ መጣ። ዐፄ ምኒልክ ዐይተውት ገንዘብ ለሚሰጥህ ሰው ብቻ ነው የምታሳየው አሉት። ሰውዬው ግን ያቺን ቀንዱን ለየመኳንንቱና መሳፍንቱ እያሳየ ብዙ ገንዘብ ተቀብሎ ወደ ሀገሩ ገባ" (የኔታ ቃለ ጽድቅ 04/01/2013 ቃ.መ)

## 4.2. የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ክብር ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ተረኮች

እንጦጦ ዕድሜ ጠገብ ቤተክርስቲያን ከመኾኑ በተጨማሪ የራጉኤል ቤተክርስቲያን ክብር ከፍ ከፍ ከሚያደርጉ ተረኮች ውስጥ የሚመደበው ቤተክርስቲያኑ ከምሥረታው ጀምሮ እስካሁን ያሉት አገልግሎቶች ሳይዛነፍ ጥንታዊነቱን በጠበቀ መልኩ አስጠብቆ መቀጠሉ ነዉ። ከፍ ያለው መራሒ ጉኒ እንደሚሉት ለምሳሌ በሰዓታት እና በማሕሌት ላይ ያሉ ሥርዐቶች የራሱ ቀለሞች ያላቸው የደመቁ አገልግሎቶች ናቸው።

በሌላ መልኩ ብዙዎች የእምነቱ ተከታዮች እና የቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች እንደሚያምኑት ቦታው ከባድ መለኮታዊ መገለጦች የሚስተዋልበት እና ቦታውን ለመዳፈር በሞከሩ አካላት ላይ ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ ቁጣው የሚገለጥበት እንደኾነ ይነገራል። ለዚህ ማሳያ ይኾናሉ ተብለው ከሚነገሩ ንግሮች ውስጥ አንዱ ዐፄ ኃይለሥላሴ የታቦቱን ወደ መርካቶ መኼድ አስመልክቶ ከተነገሩ ተረኮች ውስጥ አንዱ አንድ ባሕታዊ በ1948 ዓ.ም ታቦቱን ሲያወርዱ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ይህን ታቦት ወደ መርካቶ አታውርደው ካወረድከው አንድ እንቅብ እንባ አለበት ብለው በምስጢር ይነግሯቸዋል። እሳቸውም ማውረድ አልፈለጉም ነበር። ምኒስቴሮቹና እቴጌ ተናግረው አይቀርም ብለው ታቦቱን አወረዱት።

ታቦቱን ወደ መርካቶ ካወረዱት በኋላ በዙፋናቸዉ ላይ በተከታታይ መሰናክሎች ጋራ መጋፈጣቸዉ እንደ አብነት ይጠቀሳል፤ ለምሳሌ፡- የልዑል መኮንን ሞት፣ የእቴጌ መነን ሞት፣ በ1953 የተካኼደዉ መፈንቅለ መንግሥት ይካተታሉ። አንድ "እንቅብ ዐይን" ማለት ሐዘን ማለት ነው ምስጢሩ ብሎ ባሕታዊው ነግሯቸው ነበር ይባላል። ይህም ታቦቱ ባሕታዊ ኾኖ

ሳለ መነካቱና ወደ ከተማ መዛወሩ ቁጣን እንዳስከተለና የተጠቀሱት ችግሮች መከሠታቸውን መዘዝ ነው ብለውም እንደሚያምኑ ይናገራሉ፡፡ (አቶ መኩሪያ ሣህሉ፣ 16/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)፡፡

እዚህ መቅደስ ውስጥ ዋናው መቅደስ ውስጥ ከ2 ኩንታል በላይ ንብ አለ፡፡ የሚገርመው ጽላቶቹን ማጽዳት፣ ማስተካከል፣ ማጠብ ሲያስፈልግ ሲከፋፈት ይወጣል በሩን ኹሉ ይይዛል በንግስ ጊዜ ንቦቹ አብረው ዞረው ነው የሚገቡት ስለዚህ መንካት አይቻልም፡፡ ሁል ጊዜ ለቢሮ ሥራ ስገባ ሦስት ንቦች መጥተው ተሽከርክረው ይወጣሉ፡፡ ይኼ የራሱ መልእክት ነው ተሹሜ የገባሁ ዕለት ጽላቱን እንዲህ አንሥቼ የሥራውን ነገር እንዲባርክልኝ ስነካው ንቦቹ ተሰበሰቡ፡፡ ኧረ አልነካብህም በቃ ብዬ ቁጭ አደረኩት እየበረሩ ገቡ፡፡ ቦታቸው መስኮቱ ላይ ነው፡፡ (የመልአከ ኃይል ቆሞስ አባ ሳሙኤል አስፋው 5/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)፡፡

በአካባቢው የሚኖሩ እማሆይ ዕንደተናገሩት "ንሰሓ ገብቶ በአከባቢው ላይ ሱባዔ ለያዘ ሰው መልስ እንዳለ እንደሚታመን እና ሱባኤውም በንጽሕና እና በቅድስና የሚይዙ ሰዎች በህልማቸው ግቢዉ በብርሃን ተሞልቶ ቅዱሳን ሲጸልዩ እንደሚያዩ ሲናገሩ መስማታቸዉን ገልጸዋል፡፡ ሱባዔም ከያዙ ሰዎች መካከልም አብዛኞቹ የተለያዩ የሕይወት ጥያቄዎቻቸው መልስ ማግኘቱን ይመሰክራሉ፡፡ ይህም በአማኙ ዘንድ የቦታውን ክብር ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እያደረገ መኾኑ ይነገራል፡፡

ነቢዩ ኤሊያስ ባሕታዊ በመኾኑ ቦታው ግርግርን የማይወድ እና ተአምራቱንም በዝምታ በሚስጥር እንደሚያደርግ ለምሳሌ ደጋሹ ዝክርን ዘክሮ ከንቱ ውዳሴን ለማትረፍ በመፈለግ ልታይ ልታይ ካለ ታዳሚ እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ (እማሆይ ዓለም ጸሐይ 7/2/2013 ቃለ መጠይቅ) ፡፡

እንጦጦ ሰው የሚተርፍበት ቦታ ነው ተብሎ ይነገርለታል፤ ተመልሶ ይታደሳል፤ እንደ ድሮው ከተማ ይኾናል፡፡ አሁን ሰው አልባ ነው ለወደፊቱ ግን ድንጋይ ተጥሎ እንኳን የሚወድቅበት ቦታ አይገኝም የሚል ንግር አለ፡፡ ሰው የሚተርፍበት ነው ተብሎ የተነገረው፤ በደርግ ጊዜ ወጣቶች ወደ ውትድርና እንዲሄዱ ይታደኑ ነበር፣ ቦታውን እግዚአብሔር ሸፍኖት በትምህርት ቤቱ የነበሩ ተማሪዎች ሳይነኩ ወደ ውትድርናም ሳይኼዱ ቀሩ፡፡ (ርዕስ ደብር አጋፋሪ ሰሎሞን የ09/02/13 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ) ፡፡



ምስል 2፡ አጥኚዋ ከመርጌታ ርእሰ ደብር አጋፋሪ ሰሎሞን ጋር፣ ቤተክርስቲያን (09/02/2013 ፣ በሳምራዊት)

ቦታውን ግብጻዊው ጳጳስ አቡነ ማቲዎስ በሥርዓተ ክህነት ዳግማዊ ምኒልክ በሥርዓተ መንግሥት በመኾን በዕውቀት እና በጥበብ የተገነቡ በትምህርት በበለጸጉ መምህራንን በመሰብሰብ የስብሐተ እግኢአብሔር መውረድ እንደ ዐባይ ወንዝ ይፈስ እንደነበር በዕድሜ የነበሩት ሊቃውንት ያወሡ ነበር፡፡

እንዲያው የዚያን ጊዜ ማሕሌት በተቀመበት ሰዓታት ይቆማል፡፡ ብዙ አገልጋዮች ብዙ መምህራን ነበሩ፡፡ ስለ ቦታው ክብር በስተምዕራብ በኩል ማሕሌት ይቆማል በሥተምስራቅ በኩል ሰዓታት ይቆማል፡፡ ብዙዎቹን መምህራን ጠይቄ እንደተረዳሁት የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል አይነት ሰዓታት አይቼ አላውቅም ይላሉ፡፡ የተለየ ሰዓታት ነበረው፤ ብዙ ወረብ ነበረው፣ ዝማሬ ነበረው፣ አሁንም ድረስ ከሌሎች አድባራት እንኳን እጅግ በጣም የከበረ ሰዓታት አለ፡፡ (አቶ መኩሪያ ሣህሉ 8/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)

### 4.3. ከራእይ ጋራ ተያይዞ የሚነገሩ ተረኮች

በኦሪት ዘፍጥረት መፅሐፍ የእግዚአብሔር ቃል በራእይ ወደ አብርሃም መጣ (15፡1) ተብሎ እንደተገፈው ራእይ የሚለው ቃል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ባዘጋጀው መዝገበ ቃላት ላይ ህልም በሚለው ቃል በመተካት የሚጠቀምበት ሲሆን፣ እሳቤውንም “ በእንቅልፍ ወይም በተመስጦ ግዜ የሚታይ ህሊናዊ ትእይንት” ህልም (1993፡101) ሲለው ህልምን ደግሞ “በእንቅልፍ ላይ እያሉ የሚታይ ሐሳብ፣ድርጊት ወይም ራእይ” (1993፡7) በማለት ይፈታዋል፡፡

በዐፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ነው። በ16ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ንጉሥ የነበሩት ዐፄ ልብነ ድንግል የግራኝ መሐመድን ጦር ወረራ ለመመከትና የክርስትናን እምነት ለመከላከል ከተዋጉት ነገሥታት አንዱ ነበር። ምንም አንኳን ዐፄ ልብነ ድንግል ከመሀል ሀገር ጀምረው እስከ ሰሜን ኢትዮጵያ በወቅቱ ኃያል ከነበረው የግራኝ ጦር ጋራ በተለያየ ዐውደ ውጊያዎች ላይ የሞት ሽረት ትንቅንቅ ቢያደርጉም ድሉ ባለመሳካቱ ምክንያት ከቦታ ወደቦታ ለመሸሽና ለመሰደድ ተገደው ነበር። በዚያ እጅግ አስቸጋሪ ወቅት ቅዱስ ራጉኤል ለንጉሡ በራዕይ ተገልጾ አንተ በስደት ትሞታለህ፣ ከልጆችህም ውስጥ ገላውዴዎስ ይነግሣል፣ ፊቅጦር ይሞታል ፣ ሚናስ ይማረካል፣ ያዕቆብ ይኖራል በማለት ነገራቸው። በዚህም መሠረት በ1533 ዓ.ም ዐፄ ልብነ ድንግል አርፈው አስከሬናቸው በደብረ ዳሞ ካረፈ በኃላ እርሳቸውን በመተካት በዚያው በደብረ ዳሞ የነገሠው ዐፄ ገላውዴዎስ በተለያዩ ዐውደ ውጊያዎች ከግራኝ ጋር የተካሄደውን ውጊያ በመምራት በመጨረሻም በ በ1535 ዓ.ም ባደረጋቸው ተከታታይ ጦርነቶች ግራኝ በጦርነቱ ውስጥ በመሞቱ የግራኝ ጦር ተሸንፎ በኢትዮጵያ ላይ ለ 15 ዓመታት አንዣቦ የነበረው የመከራ ደመና ሊወገድ ችሏል። ይህንንም ታሪክ መነሻ በማድረግ ዐፄ ምኒልክ በግራኝ ወረራ ወቅት የተቃጠሉትንና የወደሙትን አድባራትና ገዳማት መልሰው ከማቋቋማቸውም በላይ ለሊቀ መልዐኩ ቅዱስ ራጉኤል ውለታ ቅዳሴ ቤቱን እንጦጦ ላይ አሠርተዋል። (ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት ሁለተኛ እትም ታህሳስ፣ 2000፡6)

የቀድሞው የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን አገልጋይ አቶ መኩሪያ ሣህሉ እንደሚሉት ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ራእይ ያዩ ሰዎች እንደሚሉት ቤተክርስቲያኗ ለዐሥራ ኹለት ዓመታት ተዘግታ በነበረበት ሰዓት የተለያዩ አባቶች ለሱባዔ ቦታው ላይ መጥተው ያዩት በተለያየ ሰዓት እና ቀናት የቤተክርስቲያኗ በር እንደተዘጋ ማንም ሳይገባባት በአየር ላይ ተንሳፉ ካህናቱ ሲቀድሱ በራእይ እንደሚያዩ፣ ተዘግቶም በነበረበት ወቅት ማንም ውስጥ ሳይኖር ዕጣን ኹሉ እየጨሰ ሲወጣ እንደሚያዩ ተናግረዋል።

“የተለያዩ አባቶች ታቦቱ እና ንዋያቱ ወደ ቀድሞ ስፍራው እንደሚመለሱ ራእይ እና ንግርት እንዳለ ወደቀድሞ ቦታው መመለሱ የማይቀር መኾኑን እንደሚታመን ይገልጻሉ።

ለዚህም ማሳያ ብለው አቶ መኩሪያ ሣህሉ ከሚጠቅሱት እንቅስቃሴዎች ውስጥ “በደርግ ጊዜ አቶ አበባው ይግዛው የሚባል ሰው  በወቅቱ ታቦቱን ለመመለስ ተሞክሮ ላይ በኹለቱ ቤተ ክርስቲያናት መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ እንደነበር፣ ነገር ግን በጠቅላይ ቤተ ክህነቱ በአቡነ ተክለሃይማኖት አቡነ ዜና ማርቆስ ፈቃድ ፍቅረስላሴ ወግደረስ እና ሰዓሊ አፈወርቅ ተክሌ

ባሉበት ታቦቱ እንዲመለስ ተፈቅዶ ተስማምተዉ ቃለጉባዔ ተይዞ የነበር ቢሆንም በወቅቱ ባለመግባባትና ዕቃ ቤቱን የሚያስተዳድረዉ ሰዉ ባጠፋዉ ጥፋት እረብሻ ተፈጥሮ የሰዉ ሕይወትም ጠፍቶ እንዲሁም ሰዉ ቆስሎ ነገሩም በስምምነት ሳይሆን በዝርፊያ መንገድ ሊወሰድ ነዉ ተብሎ እንደተነገረ እና ጉዳዩ ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ "ከዛም በኋላ በአሁን ስአት ያሉት የመርካቶ እና የእንጦጦ ቤተክርስቲያናት አስተዳደሮች እና ወጣቶች ነዋየ ቅድሳኑን በማስመለስ ዙሪያ እየተነጋገሩ እና ስምምነትም ላይ እየደረሱ መሆናቸዉ የራዕይውን ተአማኙነት የሚያሳዩ እንደሆነ ይታመናል፡፡ (አቶ መኩሪያ ሳህሉ 5/2/2013 ቃለመጠይቅ )፡፡

ከ1960 ጀምሮ ከነበሩት ተማሪዎች መካከል አንዱ እኔ ነኝ በዚያን ጊዜ የሚነገሩ ነገሮች ብዙ ነበሩ እውነት ነው፤ አንድ በዚያን ግዜ የአብነት ተማሪ የነበረ ልጅ አሁንም በአታ ቤተክርስቲያን ነው ያለው፤ ዘወትር ሌሊት ተነስቶ ይጸልይ ነበር እና አንድ ቀን ጸሎት እያደረሰ እያለ፤ በዚያ ሌሊት ጣቶቹ እንደ ወርቅ የሚያበሩ በቦታው አልፎ ሲሄድ አይቼ ደነገጥኩ እንቅልፍ የያዘኝ ነው የመሰለኝ ነው የሚለው እና ያ ምናልባት መልአኩ ቅዱስ ራጉኤል ሊሆን ይችላል፡፡ (መምህር ወልደጊዮርጊስ ገብሬ የ7/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)

ሌላው በህልሜ ቤተክርስቲያኑ ይታደሳል ተብሎ ወጥተን አሁን የፈረሰች አንድ መቃኞ ነገር ነበረች፤ ታቦቱ እዚያ ውስጥ ነበር ወደ ዋሻው መኼጃ ጋራ ማለት ነው፡፡ በቅርብ ጊዜ ነው ያፈረሷት አሁን እዚያ ስንሠራ ነበር እና ያን ቀን ቀዳሽ እኔ ነኝ በህልሜ ያየሁት ልጅ ትልቅ አይደለም፤ ትንሽም አይደለም፤ እኔ ቅዳሴ ልገባ ስዘጋጅ ልጁን ዋናው የምሠራበት ላይ ቁጭ ብሎ እንዴ ታየኝ ምን አመጣው ብዬ አውርጄ ዞር ስል አሁንም ተመልሶ ይመጣል ሶስት ጊዜ አየሁት ይሄ እንግዲህ ለሚያውቀው ሰው እጹብ ድንቅ ነው ህልሙ ሲፈታ ያው ዋናው ቦታ ላይ ስለተቀመጠ ጌታ ነው ልንሰዋ አይደል ስጋ ወደሙን ልናቀብል አይደል የምናዘጋጀው እሱን ነው፡፡ (መምህር ወልደጊዮርጊስ ገብሬ 7/2/2013 ቃለ መጠይቅ)



ምስል 3፡ አጥኚዋ መምህር ወልደጊዮርጊስ ገብሬ ከተባሉ የቀድሞ የአብነት መምህር ጋር፣ በመኖሪያ ቤታቸው (7/2/13 በሳምራዊት)

## 4.4. ከተአምር ጋራ ተያይዘዉ የሚነገሩ ተረኮች

የእንጦጦ ራጉኤል ቤተክርስቲያን በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ በሊቀ መልአኩ ቅዱስ ራጉኤል ስም የተተከለ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ የአዲስ ከተማው ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መነሻና መሠረቱ ይኸው ጥንታዊ ደብር ነው፡፡ የዚህ ታሪካዊ ደብር አመሠራረት የሊቀ መልአኩን ገቢረ ተአምራት መሠረት በማድረግ የተፈጸመ በመኾኑ፤ ከምሥረታው አንሥቶ በየዘመናቱ ዕያሌ አስደናቂ ተአምራት ተከናውነዋል፡፡

የሊቀ መልአኩ የቅዱስ ራጉኤል ገቢረ ተአምራትን ለመግለጽ ቆየት ባሉት ዘመናት የተፈጸሙትንና አሁን በቅርቡ የተከናወኑትን ተአምራት በኹለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ ራጉኤል ሰሚ ታቦት መሆኑ ከቀድሞ ጀምሮ በአባቶችና በእናቶች ሲመሰከርለት ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ ዐፄ ምኒልክ ለራሳቸው ቤተ መንግሥት ሳይኖራቸው የራጉኤልን ቤተ ክርስቲያን እጅግ ከፍ ባለ የሥነ ሕንጻ ጥበብ እንጦጦ ኮረብታ ላይ ያሠሩትም በዚህ ምክንያት እንደ ነበር የደብሩ ታሪክ ይገልጻል፡፡ (የደብረኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት ሁለተኛ እትም ታኅሣሥ 2006፡6)

## ተአምር አንድ

በጣሊያን ወረራ ወቅት ጣሊያኖች ቤተክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ መሠራት የማይገባው አጸያፊ ሥራ እየሠሩ፣ የኢትዮጵያን ባንዲራ አውርደው የራሳቸውን ባንድራ ሰቅለው በሚሣለቁበት ሰዓት በሰማይ ደመና ሳይኖር፣ በምድርም ጉም ሳይሣል፣ በጠራራ ፀሓይ መብረቅ፣ ነጎድጓድ ወርዶ እነሱን በጣም ጎዳቸው። ይህንን ድንቅ ተአምር፣ በራጉኤል ግቢ ውስጥ ስላዩ (ከ1928-1933 ዓ.ም) በኢትዮጵያ ቆይታቸው በየዓመቱ እየመጡ የትንሣኤን በዐል ያከብሩ ነበር ። ወደ አገራቸውም ከተመለሱ በኋላ በአሁኑ ግዜ በደብሩ ሙዚየም የሚገበኙ ነጭ ድባብ ጥላ እና የእነሱን ባንድራ በመሀሉ የቅዱስ ራጉኤል ምስል አሥለው በጣሊያንኛ ለቅዱስ ራጉኤል የተሰጠ የሚል ጽሑፍ ያለው ባንዲራ በስጦታ አበርክተው አሁን ሙዝየም ውስጥ አለ። (ርዕሰ ደብር አጋፋሪ ሰለሞን ጌታነህ 4/2/13 ቃለ መጠይቅ)።

## ተአምር ኹለት

የእንጦጦ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ከተመሠረተ 128 ዓመታት በላይ ዕድሜ ያለው ባለ ታሪክ ደብር እንደመሆኑ ከነገሥታት፣ ከመሣፍንት፣ ከታላላቅ የቤተ መንግሥትና የቤተክህነት ሰዎች የተበረከቱለት የበርካታ ቅርሶች ባለቤት ነው። እነዚህ ቅርሶች በተለይ በውጭ ሀገር ሰዎች ዘንድ በጉጉት የሚታዩና የሚፈለጉ በመሆናቸው ዘራፊዎች የፍቅረ ነዋይ ፍላጎታቸውን ለማርካት እጃቸውን ለዘረፋ የዘረጉባቸው ጊዚያት ጥቂቶች አይደሉም። በተለያዩ ጊዜያት በደብሩ ቅርሶች ላይ ከተፈጸሙት እኩይ ድርጊቶች መካከል አንዱ በርካታ ገቢረ ተዓምራት የተገለጸበት ጸሐፊ ትእዛዝ የጻፉት ድርሣነ ራጉኤል መጽሐፍ ከእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተ ክርስቲያን ወደ መርካቶ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ታቦቱን ሲወስዱ አብረው ወሰዱት። ድርሳነ ራጉኤል የብራና መጽሐፍ በ1970 ዓ.ም ከቤተክርስትያኑ ተሠርቆ ወደ ፈረንሣይ ሀገር ተወስዶ ለሃያ ዓመታት ቆየ። አንድ ፈረንሳያዊ አስጎብኚ ከኢትዮጵያም ሆነ ከሌሎች ሀገራት የሚያመጣቸውን የብራና መጻህፍት ሆነ ሌሎች ቅርሶች ሙዚየም ከፍቶ ህዝቡን ያስጎበኛል። ይህ ድርሳን ከሄደ ጀምሮ ግን ፈርንሳዊው አስፈሪ ህልም ያሰቃየዋል። ከዚያም ይሄ ድርሳን ከየት እንደመጣ ሳላውቀውም (በግዕዝ የተጻፈ ስለሆነ) እያለ ሲያወራ ኢትዮጵያውያን ካህናት መነኮሳት እድል ገጥሟቸው ሲጎበኙ ያን መጽሐፍ ሲያነቡ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረስላሴ ናቸው የጻፉት። የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ድርሳን ነው። ቦታውም ቅዱስ ራጉኤል ይባላል ብለው ነግረውት ወደ እንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ተመለሰ። በሰዎች ፍላጎት እና ድካም ሳይሆን በራሱ ተአምር ሠሪነት በ1993 ዓ.ም ወደ ጥንታዊ መንበረ ክብሩ ተመለሰ። (ደብረ

ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት፤ ታህሳስ 2000፣8-9 እና የዲያቆን ዮሐንስ ወልደጊዮርጊስ 13/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)




**ምስል 4፡ ተአምር የሰራው ድርሳነ ራጉኤል ፣ ሙዝየም ውስጥ ፣ (13/2/2013) በሳምራዊት**

**ተአምር ሦሥት**

ይህ ተዓምረኛ መጽሐፍ ከፈረንሣይ በተመለሰ በስድስተኛው ዓመት እንደገና ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም ይህንን መጽሐፍ ጨምሮ ሌሎች የቤተክርስትያኑ ዋና ዋና ቅርሶች ላይ እጅግ አስደንጋጭና አሳዛኝ የዘረፋ ወንጀል ተፈጽሞ ደብሩ እርቃኑን የቀረበት ጊዜ ነበር፡፡ አያሌ ምእመናንና ምእመናት እንዲሁም ካህናት ሊቀመልዐኩ ቅዱስ ራጉኤልና ቅዱስ ኤልያስ የተለመደ ተዓምራቸውን በማሣየት ዘራፊዎቹን በአስቸኳይ እንዲያጋልጧቸውና የተመዘበረው ቅርስ ፈጥኖ ወደመንበሩ እንዲመለስ ተማጽነዋል፡፡

ስለተሰረቁት ቅርሶች የደብሩ አስተዳዳሪ የነበሩትን መልዐከ ኃይል አባ ገብረ ማርያም ተክለ ሃይማኖት እንደተናገሩት "ዘረፋው መፈፀሙን የታየው ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ ነበረ፣ ወዲያዉኑ በካህናቱ መካከል ከባድ ድንጋጤ በመፈጠሩ ሕዝቡ እንዲሰበሰብ ከቤተክርስትያኑ የአደጋ ደወል ለሩብ ሰዓት ያህል ተደወለ፣ ቀጥሎም ለጉለሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ወንጀሉ ስለመፈፀሙ ሪፖርት ተደረገ፡፡ ቅርሱ ከሀገር እንዳይወጣ በየኬላው ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር

እንዲደረግ አመለከትኩ፤ ከዚህም በተጨማሪ የጠፉት ቅርሶች ከጽላት የማያንሱ ሌቦቹን እርስበርሳቸው በማጣላትና በማጋጨት ገቢረ ተዓምራት ሊያሣዩ ስለሚችሉ ጠፍተው እንደማይቀሩ ከፍተኛ ተስፋ ነበረኝ። ከፖሊስ ኃላፊዎች ጋር ለመነጋገርና ለማስፈጸም ሚያዝያ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ከጠዋት ጀምሮ ፖሊስ ጣቢያ ነበርኩ። ጉዳዩም ስላልተፈጸመልኝ በመጠባበቅ ላይ እንዳለሁ በሰባት ሰዓት ተኩል አከባቢ በያዝኩት ሞባይል ስልክ ተደወለልኝ፤ 'ስሜ እገሌ ይባላል፣ ከቤተክርስትያናችሁ ሰሞኑን ቅርሶች መጥፋታቸውን ሰምቻለሁ፣ እነዚህ ቅርሶች አንድ ቦታ ላይ እንዳለሁ ደርሼበታለሁ' ሲል እኔም በወቅቱ የተሰማኝን ደስታ በቃላት ልገልጸው ባልችልም ራጉኤልና ኤልያስ በዕለተ ቀናቸው ተዓምር ሊያሳዩን ይሆን በሚል ቅዱስ ራጉኤል ወሮታው እንደሚከፍላቸው ነግሬ አመሰገንኩ እና የጠፉት ቅርሶች ኮተቤ አከባቢ ይገኛሉ። የዘረፉትም ሰዎች እነ እገሌ ናቸው ሲሉ የአራት ሰዎች ስም ዝርዝር ገለጹልኝ። በአካል ተገናኝተን ለመነጋገር ተስማምተን ከጠቋሚው ጋር ተገናኘን። መስቀል አሳለምኳቸው እና ቅዱስ ራጉኤልና ኤልያስ ናቸው ያገናኙን፣ ነገ ግንቦት 1 ቀን ቅዱስ ራጉኤል በዓለ ንግሥ መሆኑን ያውቃሉ። ቅዱስ ራጉኤል በእርስዎ ላይ አድሮ ይህንን የደስታ ዜና ያሰማን ስለሆነ እኔም ሳላስበው እርስዎም ሳያስቡት መገናኘታችን የበረከት ስለሆነ ምናልባት የዛሬውን ሌሊት በቅዱስ ራጉኤል በዓለ ንግሥ ላይ ቢገኙልን ብዬ ጠየኳቸው። ቅዱስ ራጉኤልና ኤልያስ በንግሥ ቀናቸው በዚያ ዐውደ ምህረት ላይ እንደቆሙ እንባቸውን መቆጣጠር አቅቷቸው ሲያነቡ ለነበሩት ምእመናንና ምእመናት የተዘረፈውን ቅርስ መገኘት አበሰርኩ። እኔ ከአሁን ቀደም አይቼ በማላውቀው እልልታ ምድረ ግቢው ተናወጠ። እንደገና የደስታ እንባ ፈሰሰ፣ አንገታቸውን ደፍተው የነበሩ ካህናት ዘለሉ፣ ዝማሬው እንደገና ቀጠለ፣ የምድረ ግቢው ትርኢት ሌላ ሆነ።

ምእመናኑ በድርጊቱ እጅግ በጣም ተደነቁ፣ ሥዕለቱ እስከምሽቱ ድረስ ጎረፈ፣ በዚህ ሁኔታ የሰው ሥራ ምክንያት ይሁን እንጂ ቅዱስ ራጉኤልና ኤልያስ በሠሩት ተዓምራት በአስራት ቀኑ ተጠናቀቀ።" (ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት ፣ታህሳስ 2000፣9-13)

### ተአምር አራት

የቅዱስ ራጉኤል ህንፃ ቤተክርስቲያን በሚያስመርቁበት ግዜ ዝናብ መጥቶባቸው ዐፄ ምኒሊክ "ይድረስ ለእመቤቴ ብለህ ፃፍልኝ" ብለው ባሉት መሠረት እና ደብዳቤው ተጽፎ መንበሩ ላይ ካስቀመጡ በኋላ ዝናቡ እንደቆመ እና የምረቃ ስነስርዓታቸው እስኪጨርሱ ለአንድ ሳምንት

አየሩ የተስማማ ሆኖ ከቆየ በኋላ ዝናብ መዝነቡን እንደቀጠለ ይነገርላቸዋል፡፡ (ዲያቆን ዮሐንስ ወልደጊዮርጊስ 13/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)

**ተአምር አምስት**

በ1960 ዓ.ም የአብነት ትምህርት ቤቱ ላይ፣ ተነክቶ የማያውቅ ጽድ፣ ተገንጥሎ ወደቀ ቤቱ ውስጥ አንድ ደካማ እናት እና አንድ ልጅ ተኝተው እያለ ወድቆ በእግዚአብሔር መልዐክ በቅዱስ ራጉኤል ረዳትነት በህይወት ተርፈው ለምስክርነት በቅተዋል፡፡ (መምህር ወልደጊዮርጊስ ገብሬ 4/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ) ፡፡

## 4.5. በፈዉስ መልክ ከተገለጹ ተአምራት ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች

የቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ጸበል ከቤተክርስቲያኑ ትንሽ ራቅ ይላል፡፡ ከመቶ ሺዎች በላይ ተፈዉሰዋል፡፡ ቢሆንም ግን ብዙ ሰዎች መፈወሱን ማሳያ ከሚሆነዉ በጸበል ቦታው እና በቤተክርስቲያኑ የተለያዩ የበረከት ሥራዎች በተፈወሱ አማንያን መሰራቱ እንደማስረጃ መውሰድ ይቻላል፡፡ ጸበሉ በሶስት ቧንባ በትልቅ ታንከር ተደርጎ ተስፋፍቶ እንዲሰራ በጸበሉ ፈዉስ ያገኙ ሰዎች በገንዘብም እና በጉልበት እያገዙ አሁን ያለዉን የጸበል ገጽታ መያዙን ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ብዙ የእምነቱ ተከታዮች ከተለያየ ደዌ መፈወሳቸዉን ምሥክርነት ሠጥተዋል፡፡ ጊቢዉ ዉስጥ ያለችዉ አነስተኛ ጉድጓድ ዉስጥ ባለዉ ዉሀ ተባብሰዉ የተፈወሱ አሉ፡፡

**"አነስተኛ ጉድጓድ"** ተብላ የምትጠራው በቤተክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ የምትገኝ ትንሽ ጉድጓድ ዐፄ ምኒልክ እና እቴጌ ጣይቱ ሲመጡ ይተባበሷት የነበረች ናት ተብሎ ይነገራል፡፡ አንድ እናት ማየት የተሳነው ልጃቸውን ይዘው መጥተው ከዐዘቅት ላይ ጠበል በእጃቸው አፍሰው የልጃቸውን ዐይን ያብሱታል፡፡ የልጃቸው ዐይን በራ እኚህ እናት እልልታውን አቀለጡት፡፡ (አቶ መኩሪያ ሣህሉ የ4/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ) ፡፡



ምስል 5 ፡ በቤተክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ የሚገኝ አነስተኛ ጉድጓድ ፤ (4/2/2013) በሳምራዊት

ከጉድጓዱ በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያኑ በሚገኝ ከአንድ አለት የሚፈልቅ ጠበል ሲሆን ከስድስት የተለያዩ ቦታዎች የሚፈልቅ የቅዱስ ገብርኤል፣ ቅዱስ ኡራኤል፣ ቅዱስ ሩፋኤል፣ ቅዱስ ራጉኤል፣ ቅድስት ክርስቶስ ሳምራ፣ ነብዩ ኤሊያስ ናቸው፡፡ በእነዚህ ጠበል የተፈወሱት የሕመም አይነቶች የሚከተሉት ናቸው፣ ዐይናቸዉ የበራ፣ እጢ ያለባት ሴት መጥታ ተፈውሳ ሄዳለች፣ ከማህጸኗ ደም የሚፈሳት ሴት በአንድ ቀን ተፈውሳ ተመልሳለች፣ ትዕግስት የምትባል ሯጭ እግሯን አሟት መጥታ ስትጠመቅ ሌላ መንፈስ ነበረባት መንፈሱም ወጥቶላት ድና ተመልሳለች፡፡ ሁልጊዜ በአንድ እየመጣች ታነግሳለች፣ አባ ሳሙኤል የሚባሉ አባት ምዕመኑን እያጠመቁ አርብ እለት ጀምሮ እያከፈሉ ቅዳሜ ጠዋት በአፈቸው መስቀል እያደረጉ ጸበል ያጠጧቸውም ያጠምቋቸውም ነበር፡፡ በዚህም በርካታ ሰዎች ተፈውሰዋል፣ አንድ በተደጋጋሚ ነስር የሚያስቸግረው ሰው ከቤተ ክርስቲያኑ የጣራ ውሐ መውረጃ ላይ ከሚወርደው ውሐ ተጠምቆ መፈወሱን ያዩ ሰዎች ተናግረዋል፣ አንዲት ሕፃን ልጅ ልምሾ የኾነ ሕፃን ልጅ ለፍስለታ ጾም ወቅት መጥታ ለአራት ወራት ያህል ጸሎት ተደርጎላት ቆማ መኼድ እንደቻለች የዐይን ምስክሮች ተናግረዋል፣ ይህም ከተአምራቱ ጋራ የተያያዘ ትርክት ነው፣ ከሰበታ ከተማ የመጣች ሕፃን ልጅ ከካንሰር ሕመም ተፈውሳለች፣ ከብሥራተ ገብርኤል አካባቢ የመጣች ሴት ከጉበት በሽታ ድናለች፣ አንድ ተመስገን አጥናፉ የተባለ ወጣት ጠበል በመጠጣት ከኾዱ አረንጓዴ ቅጠል መሰል ነገር እየወጣለት እንደኾነ መስክሯል፣ ከወልቂጤ የመጣ ሰው ከስኳር መፈወሱን መስክሯል፣ ከኩላሊት ሕመምና ከሚጥል በሽታ የተፈወሱ አሉ፣ አንዲት ሴት

ጠበል ጠጥታ ከማሕፀኗ 17 ዕጢ ወጥቶላታል፣ የተለያዩ ሰዎች በተለያየ ጊዜ ከልዩ ልዩ በሽታዎች፤ ከካንሰር፤ ከአጋንንት እስራት የተፈቱ፤ ከኤች አይ ቪ፣ ከስኳር መፈወሳቸውን መስክረዋል ። ( ዲያቆን ሀይሉ ጌታነህ 7/2/2013 ቃለ መጠይቅ )

የእንጦጦ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን አከባቢ የሚኖሩ እማሆይ ስለ ጠበሉ እንደሚከተለው ገልጸዋል። "ጠበሉ ከዚህ በፊትም የነበረ ቢኾንም ግን ለረጅም ጊዜ ተሰውሮ ነበር። በኋላም ኹለት ባሕታዊዎች ራእይ ታይቶናል። የእንጦጦ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ጠበል ብዙ ሰዉ ይፈውሳል። ሒዳችሁ አውጡ ተብለናል ብለው ግቢ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ውስጥ ሲያወሩ ሰምቼ ተከተልኳቸው። ከዚያ ቦታው ጋራ ኼደን ጠበሉን በትንሹ ዐጥረን አገልግሎት ጀመርን" ብለው እማሆይ ይናገራሉ" (እማሆይ ዓለም ፀሐይ 03/02/2013 ቃለ መጠይቅ) ።

ጠበል ቤቱ ላይ የባረኩት አባት መምህር ወልደጊዮርጊስ ገብሬ ሲናገሩ ጠበል እንደሚመነጭ በሕልማቸው ከቁስቋም ወደ ጠበሉ ስመጣ አንድ ነብር የሚመስል አውሬ ዐየሁ፤ እኔ ጋር ሲደርስ ቆመ፤ እንደማስፈራራትም እንደማባበልም እያደረገ መጣ፣ አነጋገርኩት ምን ትፈልጋለህ ብለው ወደ ጸበሉ በአፍንጫው እየጠቆመ አሳየኝ፤ ወደ ጫካው ውስጥ ሲገባ ቆሜ አየሁት የለበሰው ልብስ ከትከሻው እስከ ሆዱ ድረስ የታጠቀው ገመድ ነብር ሰው ሆኖ አየሁት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስለ ጠበል ቦታው ማስጀመር ማሰብ ጀመርኩ። እና ዘላለም ከተባለ ልጅ ጋር ፀበል ቤቱን ማደሳቸውን ይናገራሉ። (መምህር ወልደጊዮርጊስ ገብሬ 4/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)

እልፍ መገርሳ የተባለች ሴት ነበረች ጡቷ ጫፍ ላይ እብጠቱ የጠጠረ ነገር ወጥቶባት ነበር ፀበሉን ስትጠመቅ ከነበረባት አጋንንት መንፈስ ተፈወሰች፤ በ7 ቀኗ ወደ ሀገሯ ሄደች፤ ከትግራይ የመጣ ልጅ ከ HIV በሽታ ድኖ ወደ ሀገሩ ሄደ፣ ዮሀንስ የተባለም ከባድ ጨጓራ ህመምተኛ ነበር በፀበሉ ድኖ እዚሁ አካባቢ ቤት ሠርቶ መኖር ጀምሯል፣ አንድ ሰውዬ ሽባ ሆነው መጥተው ጸበሉን ጠጥተው ተጠምቀው ድነው ቆመው ሄደዋል።" (መምህር ወልደጊዮርጊስ ገብሬ 4/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)



**ምስል 6፡ ጠበል ቤት (4/2/2013) በሳምራዊት**

ጸበል ቤቱ ግቢ ውስጥ ንቦች አሉ፡፡ ከሰኔ እስከ ነሀሴ ማሩ ይቆረጥና ተበጥብጦ ለመፅምናን ይሰጣል፡፡ ብዙ ሰዎች ከህመማቸው ተፈውሰውበታል፡፡



**ምስል 7፡ የንብ ቀፎ (4/2/2013) በሳምራዊት**

በቤተክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ ከሀያ አመታት በላይ የኖሩ ባህታዊ አሰፋ የሚባሉ አባት አሉ፡፡ ለረዥም ግዜ ቤተክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ ጉልላቱን ብቻ እየተመለከቱ ከማንም ሠው ጋር ሳያወሩ፣ ጸሓይም ዝናብም ተቋቁመው በቀን ከ14 ሰዓታት በላይ ቆመው ይጸልዩ ነበር፡፡ ለኹለት ዓመታት እዲህ ከጸለዩ በኃላ ለአንድ አመት ከቤተክርስቲያኑ ተለይተው ቆይተው ነቢዩ ኤልያስ በራእይ ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲቆዩ ነግሮኛል ብለው ስለመጡ አንድ አነስተኛ ክፍል

ተሰጣቸው። እዚህ ክፍል በር ስር ዘወትር ተቀምጠው ለመእመናን ጸሎት ያደርጋሉ፣ ለተፈቀደለት የፈውስ መፍትሔ ይናገራሉ። በርካታ ሰዎች በእኚህ አባት ጸሎት መፈወሳቸውን እየመጡ ይመሠክራሉ። (ዲያቆን ዮሃንስ ወልደጊዮርጊስ 15/01/2013)

## ጥምቀት ስነስርዐት

አጼ ሚኒሊክ ለጥምቀት ባህር ብለው ያሰሩት በአመት አንድ ጊዜ ለጥምቀት በዐል የሚወጣ ከመቶ አመት በላይ እድሜ ያስቆጠረ ድንኳን አለ። እያንዳንዱ ጌጥ በሰው እጅ በመርፌ የተሠራ ሲሆን ቴክኖሎጂ በሌለበት በዚያን ወቅት የተሰራ ድንቅ ጥበብ ነው። የጥምቀት በዓል የሚከበረው ጌታ የሰው ልጅን የእዳ ደብዳቤ ለመደምሰስ በባህረ ዮርዲያኖስ በዮሀነስ እጅ የተጠመቀበት ነው። በየአመቱ ድህነትን ፈውስን ያገኙበታል። የበረከት በዐል ነው የጸጋ በዐል ነው። (በትረ ትጉሀን ቀሲስ ክንፈ ሚኪኤል ጥላሁን ፣ 11 /5/ 2013 ፣ ቃለ መጠይቅ)

ድንኳኑ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ተጠበው የሰሩት ነው። አጼ ሚኒሊክ አድዋ ሲዘምቱ የማርያምና የጊዮርጊስን ታቦት ይዘው ነው የወረዱት። ለዛ ማስቀደሻ አሰርተው አድዋ ድረስ የወሰዱት ድንኳን ነው። አሰራሩ በዲዛይን የተሰራ ሆኖ የእንቁላል ቅርጽ አለው። ከመጀመሪያው ጀምሮ ለታቦቱ የተዘጋጀ ነው። ሥእላቶቹ የኃይማኖት ተምሳሌት የሚያመለክት መስቀል፣ የሰለሞን ኮከብ ተምሣሌት የሆነ ኮከብ ፣ የተፈጥሮን የሚያሣይ ፀሐይ፣ድንኳኑ ላይ የሚታየው ክብ ቅርጽ የዓለም ቅርጽ ተምሣሌት ነው፣ ሐረግ፣ አበባ ተሥለውበታል። በቅርስነት ተጠብቆ የተቀመጠ ታላቅ ኃብት ነው። (መምህር ሀይለ ስላሴ ወልደሚካኤል 11/05/2013 ቃለ መጠይቅ)

እንጨት፡ የድንኳኑ እንጨት በጠፈር የተጠፈረ ሶስት ዋልታ፣ በሶስት ቋሚ ተሰኪ ቅርጽ፣ ጫፉ ድቡልቡል ተጠርቦ የተሰራ ነው።







ምስል 8፡ የታቦት ማደርያ ድንኳን የድንኳኑ ውስጣዊ ክፍል የድንኳን መወጠሪያ
(11/05/2013) በሳምራዊት

### 4.6. የታቦቱ አመጣጥ እና ከእንጦጦ ወደ መርካቶ ቤተክርስቲያን መሸኘት

በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ውስጥ 11 ጥንታዊ ፅላቶች አሉ። ፓትሪያርክ ተክለሃይማኖት፣ ዐፄ ምኒልክ፣ ዐፄ ዮሃንስ ያመጧቸው ሶስት የቅዱስ ራጉኤል ታቦታት ነበሩ። ሌላ ዐፄ ምኒልክ ከእየሩሳሌም በስጦታ መልክ ይዘውት የመጡት ስእለ ማርያም እንደመስኮት ተከፋች የሆነችውን ምስል አለች። (አቶ መኩሪያ ሳህሉ 7/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ) ።

በ1948 ዓ.ም በወቅቱ ንጉስ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ትዕዛዝ መሰረት እንጦጦ ራጉኤል ቤተክርስቲያን የነበረው ታቦት ወደ መርካቶ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ተዘዋወረ። ይህም ለእንጦጦ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ታሪካዊ ጉዞ መነሻ ምክንያት የተፈጠረዉ በ 1927 ዓ.ም ኢትዮጵያ በጣሊያን ወረራ ውስጥ መዉደቅን ተከትሎ ነዉ።

ታቦቱ ከእንጦጦ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ወደ መርካቶዉ ቤተክርስቲያን ሊዛወር የቻለበት ዋናዉ ምክንያት እቴጌ መነን ወደ ስደት በሚሄዱበት ጊዜ በደህና ከተመለስኩ፣ የቅዱስ ራጉኤልን ቤተክርስቲያን ሊያሰሩ ተስለው ነበር። ይህንም ስለት ደብዳቤ ጽፈው በፖስታ አሽገው በወኪላቸው ለቄስ ገበዝ ዘውዱ ደብዳቤውን ልከው *"መንበሩ ውስጥ አስቀምጡት፣ ማንም እንዳያየው ስመጣ እንደነበረ እንዳገኘው"* አሉዋቸዉ። ደብዳቤውም የጣልያን ወረራ እስኪያልፍ ድረስ እዚያ መንበሩ ውስጥ ተቀመጠ። በ 1934 ዓ.ም እቴጌ መነን ከተመለሱ በኋላ ደብዳቤውን እንዳስቀመጡት ስላገኙት እና የተሳሉትን ስለት ለመፈጸም የእንጦጦ ቅዱስ

ራጌኤልን ካህናትና የአከባቢውን ህዝብ ሰብስበው ያለውን ህንፃ አፍርሰው ሌላ ለመስራት ማሰባቸውን ገለጹ። ነገር ግን ካህናቱና ሕዝቡ፣ ያለውን ሕንፃ ከሚያፈርሱ ይልቅ አድሰው የምኒልክን ስም ቢያስጠሩ ይሻላል የሚል ሐሳብ አቅርበውላቸው ነበር። እቴጌ መነን የሥራ ሚኒስቴር ባለሙያዎችን ወደ ሥፍራው በመላክ ሁኔታው እንዲጠና አደረጉ። ከመሐንዲሶቹም የቀረበው ጥናት ያለውን ማደስ እንጂ ነባሩን ማፍረስ አይገባም አሏቸው። የሁኔታውን አዝማሚያ የተመለከቱት እቴጌይቱ ግን *"በራጉኤል ግቢ ውስጥ ሌላ ቤተክርስቲያን በራጉኤል ስም ልሥራ?"* ብለው ሐሳብ ሲያቀርቡ በዚህም ተቃውሞ ገጠማቸው።

ከዚህም ይህንኑ ቤተክርስቲያን ለማሠራት ተገቢ የሆነ ቦታ በማፈላለግ እንዳሉ የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ልጅ ጋር ውይይት ሲያደርጉ፤ እዚህ አባቴ እልፍኝ ላይ አንድ ቤተክርስቲያን ለማሠራት እፈልጋለሁ በማለት ለእቴጌ መነን ነገሯቸው። እቴጌ መነንም "ይህ ከሆነ ለእኔ ስጭኝና የቅዱስ ራጉኤልን ቤተ ክርስቲያን ልሥራበት" ብለው ይጠይቋቸዋል። እርሳቸውም "በደስታ ሰጥቼሻለሁ" ብለው እንደሰጧቸው ይነገራል። (የእንጦጦ የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ሁለተኛ ዕትም፡ታህሳስ 2000 ዓ.ም፡ ገፅ 23)

በኃላም የመርካቶዉ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ዛሬ በገበያ ማዕከልነቱ በሚታወቀው ቀድመ አፅመ ርስትነቱ የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በሆነው መርካቶ አነስተኛ ቦታ ገዝተው በ1945 ዓ.ም ግንቦት 1 ቀን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለስላሴ በተገኙበት /በእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ/ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ጸሎተ ቡራኬ ቦታው ተባርኮና በግርማዊነታቸው መሠረት ተጥሎ የቤተክርስቲያኑ ሥራ ተጀመረ። ግንባታውም በተጀመረ በሶስተኛው ዓመት መስከረም 1 ቀን 1948 ዓ.ም ተጠናቆ ግርማዊ ጃንሆይ በተገኙበት /በእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ/ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ጸሎተ ቡራኬ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ። በዚያን ግዜ ቤተክርስቲያኑ ለማነጽ የወጣው አጠቃላይ ወጪ ብር 300,000 (ሶስት መቶ ሺህ ብር) መሆኑ ተገልጧል። (የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ህንፃ ምርቃት መፅሔት፡ ህዳር 2008 ዓ.ም፡ ገፅ 21-22)

ለእቴጌ መነን ትልቁ ችግር የነበረው የእንጦጦ ራጉኤልን ካህናት ማሳመን ነበር። ለዚህም ትልቁን ሚና የተጫወቱት አቡነ ባስልዮስ ናቸው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በልዩ ልዩ የመንግሥት መስሪያቤቶች ያሉትን የእንጦጦ ተወላጆችን አስቀድመው ካሳመኑ በኋላ የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤልን ካህናት ስብሰባ ጠሩ። "የቅዱስ ራጉኤል ታቦትና ንዋያተ ቅድሳት አዲስ አበባ እንዲመጣ ምክንያቱ በእንጦጦ ታቦቱ እና ንዋያተ ቅድሳት መቀመጣቸው፣ ለዝርፊያ

እንደሚያጋልጣቸው ሁለቱም አድባራት በአንድ አስተዳደረው እንዲመሙሩ፤ ለማስቻል ነው፡፡ ይህን ትእዛዝ መቀበል አለባችሁ ብለው አስጠነቀቁ ከብዙ ሙግት እና ክርክር በኋላ የሚከተለውን ነገር ወይም ማስጠንቀቂያ በመፍራት ካህናቱ ተስማሙ፡፡

የመርካቶ ዳግሚት ደብረኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን መሠረት ግንቦት 1 ቀን 1946 ዓ.ም አኖሩ፡፡ ንጉሠ ነገስቱ ጠዋት እንጦጦ ራጉኤል ካስቀደሱ እና ስርዓተ ክብሩ ካበቃ በኋላ ካህናቱም ጭምር መርካቶ ወረዱ፡፡ በአቡነ ባስልዮስ ፀሎትና ቡራኬ በኋላ ንጉሡ የመሰረት ድንጋይ አኖሩ፡፡

ከመስከረም 1 ቀን 1948 ዓ.ም በዋዜማው ታቦቱ በካህናቱ እና ህዝቡ ታጅቦ ወረደ፡፡ በሁኔታው ግራ የገባቸው የአከባቢው ተወላጆች፣ ሽማግሌዎች እና እናቶች በእንባ እየተራጩ የውሎ ለቅሶ አስመሰሉት፡፡ እንደውም አንዳንድ ሰዎች “ምኒልክ ዛሬ ገና ሞተ ሐውልቱም ፈረሰ” በማለት የሚናገሩ ሰዎችም ነበሩ፡፡

ከመስከረም 1 ቀን 1948 ዓ.ም ጀምሮ የአዲስ አበባ መርካቶ ቅዱስ ራጉኤል አለቃ፣ ሁለቱንም አድባራት እንዲያስተዳድሩ ተወስኖ ነበር፡፡ ነገር ግን ደብሩ እየቀዘቀዘ በመምጣቱ የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ሲያገለግሉ የነበሩበትን በወር ተራ ስለነበር አገልግሎቱ ሊዘልቅ አልቻለም፡፡ የሁለቱም አገልግሎት ተቋረጠ፡፡ ቤተክርስቲያኑም ተመልካችና አስተዋሽ በማጣቱ ለዘጠኝ ዓመታት ተዘጋ፡፡

ከዚህ በኋላ የዚህ ደብር ተወላጅ የሆኑት አቶ መዝራዕተ አብ ሠርጤ የታዕካ ነገሥት ባእታ ለማርያም ገዳም አስተዳዳሪ ስለነበሩ ቦታው ምድረበዳ እንዳይሆን በማሰብ ለዘውድ ምክርቤት ባቀረቡት ሪፖርት መሠረት 30 ተማሪዎችና አምስት መምህራን ተፈቅዶ የአብነት ትምህርት ይካሄድ ጀመር፡፡ ደቀ መዛሙርቱም ሆነ መምህራኑ ቤተክርስቲያኑን እንዲያገለግሉ ተደረገ፡፡ ከዚያም በኋላ እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ በመንግሥት ለውጥ ምክንያት ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራኑ ተበተኑ፡፡ ቤተክርስቲያኑም ተመልሶ ተዘጋ፡፡

ያን የመሰለ ታላቅ ደብር በርካታ ሊቃውንትን ያፈራ ተዘግቶ አገልግሎቱ ተቋርጦ ምድረበዳ የከብቶች መዋያ ተመልካች ያጣ ሆኖ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ በአከባቢው የሚኖሩ ምእመናን ልጆቻቸውን ክርስትና የሚያስነሱበት፣ ቅዳሴ የሚያስቀድሱበት ቦታ አጥተው እንጦጦ ቤተክርስቲያን ነበር የሚሄዱት፡፡

በ1967 ዓ.ም አቶ መዝራዕተ አብ ሰርጤ ከዚህ ዓለም በድንገት በሞት በመለየታቸው ቤተክርስቲያኑ ተመልካች አጣ። በድጋሚ ለጥቂት አመታት ተዘጋ። ይህን ቤተክርስቲያን እንዲከፈት ያደረጉት በዚያው ደብር ተወላጅ የነበሩት አቶ ጌታቸው ተክለስላሴ ናቸው። አቶ ጌታቸው የአከባቢውን ተወላጆች እና በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር አምስት ሰሞነኞች በመቅጠር ቤተክርስቲያኑ ተከፍቶ እንዲገለገል አድርገዋል። በኋላም በወቅቱ የነበሩት ፓትሪያርክ አቡነ ተክለሃይማኖት ታህሳስ 1 ቀን እንዲገኙ ተጋብዘው መጥተው ቦታውንም አይተው በጣም አዝነው የልማት ኮሚቴ፣ የሰበካ ጉባኤ እንዲቋቋም መመሪያ ሰጡ። በተሰጠው መመሪያ መሰረት የሰበከ ጉባኤ እና የልማት ኮሚቴ እንዲቋቋም ተደረገ። ከዛም ከተለያዩ በጎ አድራጊዎች ገንዘብ ማሰባሰቡ ቀጠለ። የልማት ኮሚቴው በልመና ባገኘው ገንዘብ ከባህል ሚኒስቴር ጋር ለመመካከር የእድሳት ሥራ ውል በመግባት ተጀመረ። ኮሚቴውም ሊወጣው ባለመቻሉ ጉዳዩ ለመንግሥት አካል ቀርቦ በስራው አምነውበት ተረክበው አደሱት።

በአጠቃላይ ሲታይ ታቦቱ ከእንጦጦ ወደ አዲስ ከተማ መውረዱ እንጦጦ ቤተክርስቲያን ለችግር ተጋልጧል። ቤተክርስቲያኑን የሚረዱት ሰዎች ቀሩ፣ ከመንግሥትም ከቤተክህነትም ተመልካች ያጣ በችግር ላይ የሚገኝ ቤተክርስቲያን ሆኖ ነበር። (የእንጦጦ የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ሁለተኛ ዕትም፡ታህሳስ 2000 ዓ.ም፡ ገፅ 23-24)

ለዚህም ምክንያት ነዉ ተብሎ የሚጠቀሰዉ በወቅቱ የነበሩት የእንጦጦ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ኃላፊዎች ጉዳዩን በሚገባ ጊዜ ሰጥተዉ ስላልተከታተሉት በንጉሱ ቃል መሰረት ጉዳዩን በቀጣይነት ማስፈጸም አልቻለም። ይህም ሊሆን የቻለዉ የእንጦጦ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ተዛዉረዉ ወደ መርካቶዉ ቤተክርስቲያን የሄዱት አገልጋዮች ብዙዎቹ የተለያየ የመንግስት ሥልጣን ስለያዙ እና ለጉዳዩ ትኩረት ማድረግ ስላልቻሉ ነበር። ለምሳሌ እነ ሊቀ ገብረክርስቶስ በኃላ አፈ-ንጉስ ገብረክርስቶስ (የፍተሐቤር ህግ አዉጪ የነበሩ)፤ አፈ-ንጉስ ኪዳኔ እንደሻዉ፤ አፈ-ንጉስ ኪዳኔ መልከፀዴቅ፤ አፈ-ንጉስ ገብረሀና ቅጣዉ እና ሊቀ ጳጳስ አፈ-ንጉስ ሳሕሉ ወልደመድህን (ፊታውራሪ) የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ይገኙበታል። በተጨማሪም የቀሩትም ጥቂት ካህናትም ዘመናዊ ኑሮ ለመኖር ፍላጎት ስለነበራቸዉ ወደ ከተማ በመዛወራቸዉ ለእንጦጦዉ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን መጎሳቆል ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሆኑ ይጠቁማሉ።

በአሁን ሰዓት በህይወት ያሉት በዛን ዘመን ታቦቱ ሲሸኝ የአይን እማኝ የነበሩ እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል፡- *የተወሰኑ ካህናት አስቀድመዉ የመንግስት ስራ ስለገቡ እንጦጦ የቀሩት ካህናት*

ፈቅደዉ እና በፍላጎታቸዉ  እየዘመሩ የአካባቢዉ ሰዉ ግን እያለቀሰ ታቦቱን ወደ መርካቶ ራጉኤል ተሸኝቷል።

ይህን ተከትሎ ቤተክርስቲያኑ ከ1948-60 ዓ.ም አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር በመዘጋቱ የአካባቢዉ ነዋሪዎች ወልደዉ ክርስትና ለማስነሳት፤ ቅዳሴ የሚያስቀድሱበት ቦታ አጥተው እንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ነበር የሚሄዱት። በቤተክህነቱም ዘንድ ትኩረት በማጣቱ ከ1948 -1992 ዓ.ም ድረስ ለ44 ዓመታት አስተዳዳሪ ሳይሾምለት ቆይቷል። ሌላዉ ክስተት ከአገልጋዮቹ መዛወር በተጨማሪ ታቦቱን  ከእንጦጦ ወደ መርካቶ ራጉኤል ሲሸኝ አብሮ የእንጦጦ የቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን መገልገያ ቁሳቁሶች በብዛት  ወደ መርካቶ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን መወሰዳቸዉን በደብሩ በተለያየ ሃላፊነት ያገለገሉት ካህን ይናገራሉ ይህም ለአገልግሎቱ መቀዛቀዝ ጉልህ ሚና ተጫዉቷል። በኃላም ይህን ተከትሎ የአብነት ትምህርት ቤቱ ለመዘጋት በቃ። (የእንጦጦ የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ሁለተኛ ዕትም፡ ታህሳስ 2000 ዓ.ም፡ ገፅ 23-24)

## 4.7. የነገሥታቱ እና የተለያዩ መንግሥታት ድርሻ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ

ከዚህ ቀደም ለማብራራት እንደተሞከረዉ ዳግማዊ ዐፄ ምኒሊክ የሊቀ መልአኩን መቅደስ ለሰባት ዓመት ያክል ደክመው የዛሬውን ገፅታ እንዲይዝ ያደረጉ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ባለዉለታ ናቸዉ። በወቅቱ የንጉሡ አላማ ቤተክርስቲያኑን ከማነጽ በተጨማሪ ቦታውን የሊቃውንት ማፍለቅያ ማድረግም እንደነበር ታሪኩን በቅርበት የሚያዉቁ ይናገራሉ። ዐፄ ሚኒሊክ እና እቴጌ ጣይቱ ቤተክርስቲያኑን ከመመስረት ባሻገር አብረዉ በማገልገል  እና ጉልት/ርስት  በመስጠት  ትልቅ  አስተዋጾ  አበርክተዋል።  የእንጦጦው  ቤተ  መንግስት ከቤተክርስቲያኑ ስድስት ሜትር ርቀት ላይ ነዉ የተመሰረተዉ። ነገስታቱም እዛዉ ጊቢ ውስጥ ይኖሩ ነበር፤ እንጦጦ ቤተ መንግስት እስከቆዩበት ጊዜ ድረስ የቤተክርስቲያኑ አገልጋዮች የሚመገቡት እዛዉ ቤተመንግስት ዉስጥ ገብተዉ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል። በዚህም ምክንያት ደጀ ሰላም በደብሩ አልተሰራለትም። ንጉሱ የቅዱስ ራጉኤልን እና ካህናቱን የእኔ ብለው እንደ ራሳቸዉ ካህናት ሲቆጥሩ ንግስቲቱ ደግሞ እንጦጦ ማርያምንና ካህናት “የኔ” ይሉ ነበር።ይህ ምን ያክል ቤተክርስቲያኑ እና ነገስታቱ ቅርብ ትስስር እንደነበራቸዉ ያስረዳል።

ቤተክርስቲያኑ ርዕሰ አድባራት ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል በመባል በአዲስ አበባ ከተመሰረቱት ቀዳሚዉ ቤተክርስቲያን እንደሆነ እና ‹‹ኃይል›› የሚለዉ ቃል ንጉሱን እንደሚወክል፤

የቤተክርስያኑ አስተዳዳሪም ማዕረግ “መለዓከ ኃይል” እንዲባል መደንገጉን እና ለእቴጌ ጣይቱ ሲባል እንጦጦ ማርያም መመስረትዋን ስለዚህም ደብሩም ርዕሰ አድባራት እንጦጦ መንበረ ፀሀይ ማርያም መባሉን እና የቤተክርስያኑ አስተዳዳሪም ማዕረግ “መለዓከ ፀሀይ” እንዲባል መደንገጉን በታሪክ ያስረዳል፡፡

ሌላዉ የዐፄ ሚኒልክ እና የደብሩን ጥብቅ ቁርኝት ከሚያስረዱት ሁነቶች አንዱ ንጉሱ ወደ ጦር ሜዳ ሲሄዱ ጸሎተ ማርያም እዚህ ቤተክርስቲያን አስደርሰው ፤የጊዮርጊስን ታቦት ከዚህ ይዘው ሄደው ሲጨርሱ ጠላቱን ድል አድርገው ከተመለሱ በኋላ አዲስ ያስተከሉት የጊዮርጊስ ታቦትንም ከዚህ ቤተክርስቲያን ይዘውት ወጡ፡፡ በተጨማሪም እንጦጦ ማርያምም እና ሩፋኤልም በርካታ ታቦቶች ከዚህ ነው የወጡት፡፡ ብዙ ጽላቶች ተሸክሞ አሁንም ከ18ኛ ክፍለ ዘመን በፊት የነበሩ 12ኛ ዘመን ያስቆጠሩ በርካታ ቅርሶችን ተሸክሞ የያዘ ታላቅ ደብር ነው ፡፡ ( አቶ መኩሪያ ሳህሉ፡ 4/2/2013 ዓ.ም፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

## የዐፄ ኃይለስላሴ እና የቅዱስ ራጉኤል ካህናት ግንኙነት

ሊቀ ጠበብት ሳህሉ ወልደመድህን በወቅቱ የቤተክርስቲያኑ አገልጋይ የነበሩ ሲመሰክሩ እንዲህ በማለት እንደነገሯቸዉ ልጃቸዉ አቶ መኩሪያ ሳህሉ ያስታዉሳሉ

> *“በኢዩቤልዩ ቤተመንግስት የእንጦጦ ራጉኤል ካህናት ለበዓል ተጋብዘዉ ሲሄዱ ከሁሉም ሰዉ ቅድሚያ ተሰቷቸዉ ይስተናገዱ እንደነበር እና ከዐፄኃይለስላሴ ጋር በአንድ ማዕድ እንዲመገቡ ታስቦ የአሳ ምግብ ተዘጋጅቶ (ምክንያቱም ዐፄ ኃይለስላሴ አሳ እንጂ ስጋ አይመገቡም) ከንጉሱ ጋር አብረዋቸዉ ይመገቡ እንደነበር ንጉሱ ይህን ከሌላ ቤተክርስቲያን ወደ ቤተመንግስት ከሚሄዱ ካህናት ጋር ሲያደርጉ እንደማይታዩ አያደርጉትም ነበር፡፡” (አቶ መኩሪያ ሳህሉ፡ 4/2/2013፣ ቃለመጠይቅ)*

## በደርግ ዘመነ መንግስት

ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም ስልጣን ሲይዝ ዐፄ ኃይለስላሴ ይጠቀሙበት የነበረዉን ልብሰ ተክህኖ ፤ የመያር መስቀል ከነቀፀላዉ እና አምስቱን የሉካን ልብስ ጠቅልሎ በክብር በብርጋዴር ጀነራል ፍሬሰንበት እጅ ለቅዱስ ራጉኤል ስጡ ብሎ በማዘዙ ለቤተክርስቲያኑ ገቢ ሆኗል፡፡ ይህም ድርጊታቸዉ በወቅቱ በቤተክርስቲያኑ አገልጋዮች በነበሩ በምእመእናን ዘንድ ምስጋናን

አስችሯቸዋል፡፡ በዘመኑ አንዳንድ ከፍተኛ የደርግ ባለስልጣናት ለምሳሌ በጠቅላይ ሚኒስትር ፍቅረ ስላሴ ወግ ደረስ ትዛዝ፣ አዲስ ተድላ እና ሜትር አርቲስት ሰአሊ ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ እንዲሁም ብርሀኑ ባየ በጀቱ እንዲፈቀድ፣ እንዲታደስ እና መቶኛ ዓመት በዓሉ ሲከበር ፕሬዝዳንት መንግስቱ ሀይለማርያም አዲስ አበባ አልነበሩም እነሱ ተገኝተው ቤተክርስቲያኑን ጎብኝተው ጥሩ ይዞታ እንዲይዝ በመንግስት ወጪ አሰሩት፡፡ (አቶ መኩሪያ ሳህሉ፡ 4/2/2013 ፣*ቃለመጠይቅ*)

**የታዋቂ ሰዎች ጉብኝት**

በቤተክርስቲያኑ የቅኔ መምህር የነበሩት የሊቀጠበብት አለቃ ድንቄ ልጅ የአሜሪካ አምባሳደር የነበረዉ ብርሀኑ ድንቄ ብዙ ተአምራት ይታይበት የነበረ ቦታ እንደነበር እና ስለ ማህሌቱ ክብር ለመግለጽ *‹‹ዐፄ ኃይለስላሴ ከመንገሳቸዉ በፊት እዛ ቦታ ይመጡ ነበር ነገር ግን ከማህሌቱ ክብር የተነሳ መጋረጃውን ገልጠዉ አይተው ለመግባት ፈርተዉ ተመልሰዉ ዞረዉ በቅድስቱ በኩል ይገቡ ነበር፡፡››* የአይን እማኙ አቶ መኩሪያ እንደሚሉት ከዚህ በፊትም አሁንም ያሉ የሀገሪቱ ጳጳሳቶች ስለ ትህትና ብለዉ ተደብቀዉ እና ከህዝቡ እራሳቸዉን ሰዉረዉ ጸሎት አድርሰዉ ይሄዳሉ፡፡ ከነዚህም ዉስጥ የሚጠቀሱት ለረጅም ጊዜ ይመጡ የነበሩት አቡነ ገሪማ እና ፣ እስከ 1988 ዓ.ም ድረስ አሁን በህይወት ያሉት አቡነ ሳሙኤል፤ አቡነ ኤልሳ፤ አቡነ አብርሀም፤አቡነ መርሀክርስቶስ እየመጡ ይቀድሳሉ ማህሌት ያድሩ እንዲሁም በየበዐሉ ይመጡም እንደነበር ለጥናት አቅራቢዋ ተናግረዋል፡፡ ከውጭ ሀገር የአርመን እና የግሪክ ጳጳሶች ኢትዮጵያ ሲመጡ እዚች ቤተክርስቲያን ይመጡ እንደነበር እና የግሪኩ ጳጳስ ከአቡነ ጳውሎስ ጋራ መጥተው ይቀድሱ እንደነበርም ገልጸዋል፡፡ ይቀድሱበት የነበረውም ቅዱሳን ነዋያት ጻሕሉ፤ ጽዋው፤ ዕርፈ መስቀሉ ከእነ ማጎደሯ በከፋይ ጨርቅ እንደተያዘች ሙዚየም ተቀምጠዋል፡፡ በተለያየ ጊዜም የተለያዩ ሀገራት ባለ ሥልጣናት መጥተው የዐፄ ምኒልክን ቤተ መንግሥት እና ቤተ ክርስቲያኑን ጎብኝተዋል ፡፡ (አቶ መኩሪያ ሣህሉ የ4/2/2013 *ቃለመጠይቅ*)፡፡

## 4.8. የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ያፈሯቸዉ ሰዎች

የዐፄ ምኒልክ ዓላማ ቤተ ክርስቲያኑን ከማነጽ በተጨማሪ ቦታውን የሊቃውንት ማፍለቂያ ማድረግ ነበር፡፡ ይህም ዓላማቸው የሀገር ባለውለታ ታላላቅ ሰዎችን በማፍራት ፍሬ አሳይቷል፡ የደብረ ኃይል፤ ቅዱስ ራጉኤልን ስናነሳ ደግሞ በዛው ደብር ፊደል ቆጥረው፣ ቅኔ ተቀኝተው፣

ምሥጢር አመስጥረው፣ ትርጓሜ ተምረው አንቱ የተባሉ ስመጥር ሊቃውንት ያፈራ ደብር መሆኑ አይዘነጋም። ከእነዚሁ ሊቃውንት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

**አቶ ብርሃኑ ድንቄ፡** አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ የታወቁ የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ሊቅ የአለቃ ድንቄ ልጅ ናቸው። የቤተ ክህነትን ትምህርት በሚገባ አጠናቀው ቤተክስቲያኑን ሲያገለግሉም ቆይተዋል። በዘመናዊ ትምህርት እውቀትም የተካኑ ሰዉ ነበሩ፤ በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በጽሕፈት ምኒስቴር ዋና ዳይሬክተር በፖስታ፣ ቴሌግራፍ፣ ቴሌፎን ሚኒስቴር፣የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ ከዚያም የአሜሪካ አማባሳደር ሆነዉ አገልግለዋል።

**ደጃዝማች ታከለ ወልዴ፡-** የእንጦጦ ራጉኤል አገልጋይ የነበሩ ናቸዉ። የሚያውቁዋቸው ሲናገሩም ቅኔ ማሕሌት ሲቆሙ ክንፍ አዉጥተዉ የሚበሩ ይመስሉ ነበር ይላሉ። በመንግሥት አገልግሎት የአዲስ አበባ ከንቲባ፣ የአገር ግዛት ሚኒስትር እና የሸዋ ጠቅላይ ገዥ ነበሩ።

**ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ፤ አካለ ወርቅ ሀብተ ወልድ እና መኮንን ሀብተ ወልድ፡-** የመጀመሪያው የቅዲስ ራጉኤል ደብተራ ሀብተ ወልድ ልጆች ናቸዉ። የአንድ ቤተክርስቲያን ትልቅነት ለማወቅ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ያሉትን የደብተራዎች ብዛት ማየቱ በቂ መልስ ይሆናል። በአጤ ምኒልክ ዘመን በአንድ ወቅት በቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ሥድሥት ደብተራዎች ነበሩ ይህ ማለት ምን ያህል ትልቅ ቤተክርስቲያን እንደ ነበር ነዉ። ‹‹ደብተራ›› ማለት በዉስጡ የከበረ ነገሮች የያዘ ሊቅ ነዉ።

**ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፡** ሀገራቸውን በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ያገለገሉ በኋላም በዐፄ ኃይለስላሴ ዘመን የሀገሪትዋ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሹመዋል።

**መኮንን ሃብተወልድ** ፡- በድጓ፤በጾመ ድጓ፤ የታወቁ ሊቅ ነበሩ። ዘመናዊ ትምህርትም በመቅሰም በመንግስት መሥሪያ ቤት የገንዘብ ሚኒስትር፤የአገር ግዛት ሚኒስትር በመሆን በዐፄ ኃይለስላሴ ዘመን አገልግለዋል። እነዚህ ወንድማማቾች ከደጃች ታከለ ጋራ ዘመዳሞች የነበሩ፣ ዐጼ ምኒሊክ በታመሙ ጊዜ ለጸሎት ከሸዋ የመጡ እና በድቁና ያገለገሉ መሆናቸው ይነገራል።

**ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደስላሴ ፡** ታላቅ ምሁር ፤ዲፕሎማት፤ “የአማርኛ ስነ ጽሑፍ አባት” ነበሩ። ትጉህና ታታሪ እንደነበሩ የሚነገርላቸዉ እኚህ ሰዉ በእንጦጦ ራጉኤል ትምህርታቸዉን ሲከታተሉ በድቁና ያገለግሉ ነበር። በ1914 ዓ.ም ብላታ ተብለዉ የፍርድ ቤት ዋና ዳኛ ሆኑ።

በ1919 ዓ.ም የልዑል አልጋ ወራሽ ልጅ አማካሪ ሆኑ፡፡ ሊቁ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ ያልተሠማሩበት የሙያ ዘርፍ የለም፡፡ ከሃይማኖት አስተማሪነት በ 1920 ዓ.ም እስከ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ሀገራቸውን በቅንነት አገልግለዋል፡፡ በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ በርካታ መጽሐፍትም በመጻፍ የመጀመሪያውን ሥፍራ የያዙ ደራሲ ናቸው፡፡ ዐፄ ምንሊክ ወዳጄ ልቤ የሚሉዋቸው፤ እስከ ዐፄ ኃይለ ስላሴ ዘመን አገልግለዋል፡፡

**ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ፡-**

የመጀመሪያው የጽህፈት ሚኒስትር ጸሀፊ ትእዛዝ ገ/ስላሴ ወልደ አረጋይ የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ደግሞ የመጀመሪያው አስተዳደር፤ በዚያን ዘመን የተጻፉትን መጽሀፍቶች በሙሉ የጻፉ እንዲሁም የዐፄ ምኒልክ የመጀመርያ ጸሐፊ ትእዛዝ ነበሩ፡፡ (ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት ሁለተኛ እትም ታህሣሥ 2000፡ 28-30)




**ምስል 9፡ የጸሐፊ ትእዛዝ ገብረስላሴ እና የልጃቸው እማሆይ ሐመልማል ገብረስላሴ መቃብር (05/02/ 2013) በሳምራዊት**

**ቀኛዝማች ተስፋ ገብረስላሴ፡** በኢትዮጵያ ውስጥ አርአያ የሚያሰኛቸው በርካታ ተግባራትን ከከናውኑ ስመጥር ታላላቅ ሰዎች ተርታ የሚመደቡ አባት ናቸው፡፡ ቀኛዝማች ተስፋ ገብረሥላሴ “ድንቁርና ይጥፋ ዕውቀት ይስፋ ይህ ነው የኢትዮጵያ ተስፋ” የሚለውን ኃይለ ቃል በማራመድ በኢትዮጵያ ውስጥ በዘመናዊ ማተሚያ ፊደልን በማተም በስፋት ሕፃናት

እንዲማሩባቸው ያደረጉ የመጀመሪያው የፊደል ሐዋርያ ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ቤተክርስቲያንን ሊቃውንት ድካም ወደ ዘመናዊ የህትመት ሥራ በማሸጋገር የፊደል ገበታዎችንና የንባብ መልመጃዎች በዘመናዊ ማተሚያ በማዘጋጀት ልዩ ልዩ የጸሎትና የግብረ ገብነት መጽሐፍትን በብዛት በማተም ፈር ቀዳጅ ሚና የተጫወቱት ደግሞ ቀኛዝማች ተስፋ ገብረሥላሴ ናቸው፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ የፊደል ስም ጎልቶ መወሳቱ የማይቀር ነው፡፡ የሃይማኖትና የግብረ ገብነት መጽሐፍትን በማተምና በማሠራጨት ግንባር ቀደም ታዋቂነትን አትርፈዋል፡፡ ዛሬም እንደ አንጋፋ ልጆቻቸው የሚቆጠረው የማተሚያ ድረጅታቸውና ልጆቻቸውን ይህንኑ ፈለግ በመከተል የኅብረተሰባችንን የዕውቀት ጥማት ለማርካትና መንፈሳዊ ሕይወትን እያተሙ ማሠራጨታቸውን ቀጥለዋል፡፡

ቀኛዝማች ተስፋ ላለፈው፣ ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ በበጎ አርአያነቱ መጠቀስ የሚገባው በኢትዮጵያ ዘመናዊ ዕውቀት እጅግ ውስን በነበረበት ከአንድ መቶ ዓመታ በፊት ገና በልጅነታቸው ራዕይ ሰንቀው በመነሳት በጥረትና በግረት ትልቅ ሰው መባል መብቃታቸው ነው፡፡ ምንም አይነት ዘመናዊ የዕውቀት ጭላንጭል ካልነበረበት ከገጠሪቱ ኢትዮጵያ ተነስተው ከተማ በመግባት ራሳቸውን በራሳቸው በማስተማርና ማናቸውንም ሥራ ባለመናቅ የሥነ ጽሑፍ ሰውና የዘመናዊ የህትመት ቴክኖሎጂ ባለቤት ለመሆን መብቃታቸው በጥረትና በአርቆ አስተዋይነት የማይናድ ተራራ እንደሌለ ያሳያል፡፡

ህይወታቸውን በሙሉ የዕውቀትን ሻማ ሲያበሩ የኖሩ ታላቅ ሰው አስከሬን በኑዛዚያቸው መሠረት በሊቀ ብርሃናት ቅዱስ ራጉኤል ደጅ አረፈ፡፡ በመቃብራቸውም ላይ በታሪክ መዘክርነት የተስፋ ገብረ ሥላሴ መጻሕፍት ቤት ወመዘክረ ተሠርቶ ይገኛል፡፡ (የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሄት ሁለተኛ እትም፡፡ ታህሳስ 2000፣ 26-27)




**ምስል 10፡ የቀኛዝማች ተስፋ ገብረስላሴ መቃብር ላይ የተሰራ ወመዘክር (05/02/ 2013) በሳምራዊት**

***መቃብር*** የዳግማዊ ዐፄ ሚኒልክ ልጃቸው ደጃዝማች ወንድወሰን (ማሞ) በቤተክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ ነው የተቀበሩት።

***መቃብር*** ሌላው መቃብር በቅርብ ጊዜ የፕሬዝዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ባለቤታቸው ከማርያም አካባቢ ቀብሬ መፈጸም ያለበት በራጉኤል ቤተክርስቲያን ነው ብለው ተናዘው የመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅሰው ለቤተሰቦቻቸው ሰጥተው በማረፋቸው ነሀሴ 11፣ 2009 ዓ.ም ቀን ጳጳሳት ታዋቂ ሰዎች ባሉበት በዚህ ቦታ አርፈዋል። (ቃለ መጠይቅ ዮሀንስ ወልደጊዮርጊስ 8/02/2013)

# ምዕራፍ አምስት

## 5. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን፣ ሙዚየም የተሰበሰቡ እና ወደ መርካቶ ቅዱስ ራጉኤል የተዛወሩ ቁሳዊ ባህሎች ትንተና

### 5.1. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎች

#### 5.1.1. የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ህንጻ አሰራር

ሕንፃው የተሰራው ከለስላሳ ድንጋይ፣ በኖራ በአሸዋና ለማጣበቂያነት እንዲያገለግል የተቀቀለ የእንስሳት ቆዳ እንዲሁም እንቁላል በመጠቀም ነው። በተለይ ደግሞ ጉልላቱ የተሰራው በስንዴና በእንቁላል ነው። ይህም የበለጠ ጥንካሬ እንዲሰጠው ታስቦ ነው። ቤተክርስትያኑ በእንጦጦ ተራራማና ደጋማ አከባቢ ይገኛል። ስለአሰራሩ ፀሓፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ እንዲህ ብለዋል።

> *‹‹የቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ሲሰራ ድንጋዩ ለኖራው እንዲስማማ አራት ማዕዘን እየሆነ የተጠረበ ንጉሡም እራሳቸዉ እየጠረቡ እንጨቱ በሰረገላ ከመናገሻ እየመጣ ቅኔ ማህሌቱም፣ ቅድስቱም፣ መቅደሱም ስምንት ስምንት ማዕዘን ሆኖ በኖራ ተሰራ። ከዚህም ቀደም እንደዚህ ያለ ማለፊያ ሥራ አልተሰራም፣ አላየነም። እቴጌ ጣይቱም ተገኝተው ያሰሩ ነበር። ከመናገሻ አራት ማዕዘን እንጨት በሰረገላ እየመጣ ድንጋዩም በመንኮራኮር እየተመላለሰ ንጉሡም እየተመላለሱ ሥራውን እያሳዩ ለአናጢዎች ሹም አዛዥ ወልደጊዮርጊስ ሰጥተው ያሰሩ ጀመረ”። (ጸሓፊ ትእዛዝ ገብረሥላሴ 2008፡ 125)*

የቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ሕንፃ ባለ አንድ ፎቅ ሲሆን ሥራው በ 1877 ዓ.ም ተጀምሮ ከስድስት ዓመታት በኂላ እንደተጠናቀቀ ይነገራል። የሕንፃው ሥራ ሲጠናቀቅም ለስድስት ዓመት ያህል በዋሻው ውስጥ ተቀምጦ የነበረውን ጽላት ወደ ሕንፃ ቤተክርስትያኑን አስገብተውታል።የሕንፃውን የላይኛው ክፍል ለሐይማኖታዊ ሥርዓት ማስኬጃ የሚውል ሲሆን፣ ምድር ቤቱ መጋዘን ሆኖ ያገለግል ነበር። ጣራው፣ ማገሩ እና ወራጁ ከጽድ እንጨት በጣውላ የተሰራ ነው። ይህ እንጨት ከመናገሻ ማርያም ቱባ ከተባለ ተራራ የመጣ ሲሆን ከፈረንሳይ በተላከ ማሽን እየተዘጋጀ እና እየተላገ የተሠራ፤ እንጨቱም ይጓጓዝ የነበረዉ ከመናገሻ አስራ

ሁለት ሰዎች ሆነዉ ተሸክመው ለሶስት ቀን ያህል እንጦጦ ድረስ በማጓጓዝ ነበር። በዚህ ግዜ በየመንገዱ የግብር ቤት ተሰርቶ እንጨቱን የተሸከሙ ሰዎች እያረፉ ምግብ እየተመገቡ ይጓዙ ነበር። በጊዜዉ ከሚመገቡባቸዉ ቦታዎች አንደኛው ፀደንያ ማርያም ግቢ ሲሆን በዚያ አርፈው ምግብ በልተው የደከሙት እንደገና በርትተው ጉዞአቸውን ይቀጥሉ ነበር። ከዚያ ቀጥሎ ከፍተሻ ከፍ ብሎ ስጋ ሜዳ ከተባለ ቦታ ፍሪዳ ድረስ እስከመታረድ ደርሶ ምግብ በሚገባ በልተው መጠጥ ጠጥተው ጉዞ ይቀጥሉ ነበር። በተጨማሪም በየዛፉ ላይ የማር ቀሰም ተቀምጦ ሰራተኞቹ እሱን እየተመገቡ ይሰሩ ነበር። የጣራው ክዳን ከግብፅ የመጣ ሲሆን የእየሩሳሌም ድንጋይ ተብሎ ይጠራል።

በግንባታዉ ላይም ከሀገር ውስጥ ታዋቂ ግንበኞች ከአንኮበርና ከጎንደር እንዲመጡ አድርገዋል እንዲሁም ከዉጭ ሰዎች አንኮበር ከነበሩበት ጊዜ ከሚኒልክ ቤተመንግስት ተለይቶ የማያዉቀዉን የህንድ ተወላጅ ሀጂ ካዋስ ምርጥ ባለሙያ በመሆኑ በዚህ የህንፃ ስራ ውስጥ ግንባር ቀደም ተሳታፊ አድርገዉታል። በ1877 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ሶስት የስዊዝ ጥበበኞች በዚሁ ቤተክርስቲያን የግንባታ ስራ ዉስጥ በማሳተፍ የአዉሮፓን የህንፃ ጥበብ ግንባታ አካፍለዋል። የእድሳቱን ሁኔታ ስንመለከት ለሁለተኛ ግዜ ከፈረንሳይ በመጣ ቆርቆሮ መሰል ጣርያው ተቀይሯል። ለሶስተኛ ጊዜ እቴጌ መነን አድሰውታል። ከዚያ ዘመን በኃላ በ1979 ዓ.ም በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አማካኝነት ቆርቆሮው ተቀይሮለታል። (ዲያቆን ዮሃንስ ወልደጊዮርጊስ፡ 09/02/2013)

ከአዲስ አበባ መስተዳድር ቱሪዝም ቢሮ ያገኘሁት መረጃ እንደሚያትተው ከሆነም ለቤተክርስትያኑ ግንባታ የሚሆን ድንጋይ፣ የጥድ እንጨቶች በሠረገላ እያቀረቡ ቅኔ ማኅሌቱ፣ ቅድስቱና መቅደሱም ስምንት ማዕዘን ሆኖ የተሠራ ሕንጻ ነው። የቤተክርስቲያኑ ክፍሎች በአጠቃላይ አራት የመስታወት መስኮቶች እና ሃያ ዘጠኝ የእንጨት መስኮቶች እንዲሁም አራት መግቢያ በሮች ያሉት ሲሆን እነዚህም የሴቶች በር ፥ የካህናት መግቢያ በር ፥ ሁለት የወንዶች መግቢያ በሮች ሲኖሩት ነገር ግን አንደኛዉ በር ታቦት ብቻ የሚገባበት እና ሚወጣበት በሮች ናቸዉ። ስለአሠራሩ ኪነሕንጻዊ ጥበብና አስደናቂ ግንባታ የአውሮፓ ዲፕሎማቶችና ተመራማሪዎች የሰጡትን ምስክርነት እንዲህ ገልጸውታል።

*"ግሌችን የተባለው ተጓዥ በ1890 ዓ.ም በምኒልክ ግብዣ በራጉኤል ንግስ ላይ መገኘቱን ገልጾ በዓሉ እጅግ በጣም ደማቅና ማራኪ ትዝታው ምንግዜም የማይጠፋ እንደነበር ጽፏል፡፡"*

*"ፓውል ኮተን የተባለው ሌላዉ ተጓዥ ደግሞ በአቢሲኒያ ምድር እንዲህ ዓይነት ቤተክርስቲያን አልታየም ቁመቱና ግዝፈቱ አራት ፎቅ ያክላል" በማለት ምስክርነቱን ሰቷል። (የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሄት፣ ሁለተኛ እትም፣ ታህሣሥ 2000፣7)*

የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ህንፃ ስራ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በሀገሪቱ ዉስጥ እንዲለመዱ ፈር ቀዳጅ መሆኑንም አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ቀድሞ በኢትዮጵያ ተለምዶ የነበረዉ የቤተክርስቲያን አሰራር ክብ ሲሆን የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን አሰራር ግን ስምንት መዐዘን ሆኖ ፎቅ ተደርጎ የተሰራ ነዉ፡፡

ቤተ ክርስቲያኑ አናት ላይ የሰጎን እንቁላል ይገኛል፡፡ የሰጎን እንቁላሏን ከጣለች በኋላ ከአይኗ እንደማትለየው እየሱስ ክርስቶስም አይኑን ከቤተክርስቲያን አይለይም የሚል አምሳያ አለው፡፡ ቤተክርስቲያኑ ስምንት ማእዘን እንዲኖረው ተደርጎ የተሠራ ሲኾን የኖኅ መርከብ ተምሳሌት ይዟል፡፡

ይህንንም በወቅቱ የደብሩ አስተዳዳሪ የነበሩት እና የዐፄ ምኒልክ ልዮ ጸሐፊና የመጀመሪያው የጽሕፈት ምኒስቴር የነበሩት ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ ይህንኑ በማረጋገጥ ከዚህ ቀደም እንዲሁ ያለ ማለፊያ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ አላየንም ሲሉ አድናቆታቸዉን ገልጸዋል፡፡

ዐፄ ምኒልክ በዚሁ ቤተክርስቲያን ሥራ ውስጥ ኢትዮጵያውያን ሙያ እንዲቀስሙ ከማስቻላቸውም ባሻገር የተለያዩ ኅብረተሰብ ክፍሎችን በማደራጀት በቤተ ክርስቲያኑ የግንባታ ሥራ እንዲሳተፉ አድርገዋል፡፡

በአጠቃላይ የቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ አዳዲስ ቴክኖሎጂ የታየበት፤ በርካታ ባለሙያዎች የተሳተፉበት በብዙህ ሺሕ የሚቆጠር ሕዝብ አዳዲስ ቴክኖሎጂ የታየበት በርካታ የዐፄ ምኒልክ የመጀመሪያ ትልቁ ሥራቸው በአግባቡ ተጠናቆ በ1877 ዓ.ም መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ ከነበረበት ከዐፄ ዳዊት ፍልፍል ዋሻ ወደ አዲሱ ሕንጻ ቤተ መቅደስ

አስገብተው ቅዳሴ ቤቱን አክበረዋል፡፡ (በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጉለሌ ክፍለከተማ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት፣ በራሪ ወረቀት፣ ሰኔ 2008)



**ምስል 11፡ የቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ሕንፃ ቤተክርስቲያን (09/02/ 2013) በሳምራዊት**

### 5.1.2. የቤተክርስቲያኑ ውስጣዊ ገጽታ

የቤተ ክርስቲያኑ ውስጣዊ ገጽታ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን መቅደስ፣ ቅደስት እና ቅኔ ማህሌት ይባላሉ፡፡ መቅደስ ማለት ታቦቱ ያለበት፣ ስጋ ወደሙ የሚፈተትበት፣ ቅዳሴው ስርአት የሚከናወንበት ቤተ መቅደስ ይባላል፡፡ ቅድስት ማለት ደግሞ ምእመናን ገብተው የሚያስቀድሱበት ሴቱ በሴት ወንዱ በወንድ በኩል ሆኖ አስቀድሶ መጨረሻ ላይ የክርስቶስን ቅዱስ ቁርባን የሚያገኙበት ወይም የሚቀበልበት ቦታ ቅድስት ተብሎ ይጠራል፡፡ የእነዚህ የሦሥቱ ምሣሌ የአብ የወልድ መንፈስ ቅዱስ ምሣሌ ነው፡፡ አብ ማለት ቤተ መቅደስ አባት ማለት ነው፡፡ ወልድ ማለት ብፁእ እየሱስ ክርስቶስ ስጋዬን ያልበላ ደሜን ያልጠጣ የዘላለም ህይወት የለውም ያለው ወልድ እየሱስ ክርስቶስ ነው ስጋ የሚገኝበት ክፍል ወልድ ይባላል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ቅኔ ማህሌቱ አጠቃላይ ማለት ነው፡፡ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ይጠራል ቤተ መቅደስ ቅድስት እና ቅኔ ማህሌት ይባላሉ፡፡ (ዲያቆን ዮሃንስ ወልደጊዮርጊስ 06/02/2013 ቃለመጠይቅ)

በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ሥዕላቶች አሉ፡፡ እነዚህ ታሪካዊ ሥዕላት ከተሣሉ ከ135 ዓመት በላይ ያስቆጠሩ ናቸው፡፡ ሥዕላቱን ዐፄ ምኒልክ በኢትዮጵያውያን ሠዓሊዎች ነው ያሠሩት፡፡ ዐፄ ምኒልክ ሥዕላቱን ከማሠራታቸው በፊት በ1876 ዓ.ም ላይ ሠዓሊዎች ከፖርቹጋል በማስመጣት አጠቃላይ ሥዕላቱን አሥለው ሰቀሉ፡፡ ከዚያ ሥዕሎቹ ተስለው እንዳበቁ ዐፄ ሚኒልክ እንዲጎበኙ ሲደረግ በሰዓቱ በቤተ መቅደሱ ግድግዳ ላይ ተሰቅለው ንጉሡ

በሚመለከቱበት ጊዜ እጅግ በጣም አዘኑ፡፡ ምክንያቱም የተመለከቱአቸው ሥዕሎች በአጠቃላይ የፊት ገጽታቸው የፈረንጅ መልክን ብቻ የያዙ በመሆኑ እርሳቸውንም ሚሥኒቸው እንደ ፈረንጅ ነጭ አድርገው ስለሣሏቸውና ስላልተደሰቱ እና የሀገሪቱን የሥዕል አሳሳል ዘይቤን ያልተከተለ በመሆኑ በ1877 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ መቅደሱ ግድግዳ ላይ አስወርደው ወዲያውኑ ሹማሙንቱንና መኳንንቱን ሰብስበው "ይህን የመሰለ ቤተ ክርስቲያን ሠርተን የተሣሉት ሥዕሎች ኢትዮጵያዊ ቀለም የሌላቸው፣ እኛን ብቻ ሳይሆን የወደፊቱን ትውልድ ጭምር የሚያሳዝን ስለሆነ አሁን አሉ የተባሉትን የሀገሪቱ ሠዓሊዎች ከሀገራችን ፈልጋችሁ አምጡና ሥዕሎቹ በአስቸኳይ እንዲጀመሩ" በማለት ትእዛዝ አስተላልፈው አለቃ ዘዮሐንስ ዘማኅደረ ማርያም፤ አለቃ ኤልያስ ገ/እግዚአብሔር፤ አለቃ ሉቃስ እና አለቃ መዝሙር ዘዳዊትን በማስመጣት አሁን የሚታየውን ሥዕል በድንቅ ጥበብ አሥለው በቤተ መቅደሱ ግድግዳ ላይ አኖሩ፡፡

በአብዛኛውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምትታወቅበት የግድግዳ ላይ ሥዕል የእንጦጦ ራጉኤል ውበት ነው፡፡ ሥዕሎቹ አቡጀዲ ጨርቅ ላይ ተሥለው በግድግዳው ላይ የተለጠፉ ናቸው፡፡የቤተ ክርስቲያኑ ጣሪያ በሚያስደንቅ ጥበብ የተሠራ ኾኖ የክርስቶስን ከልደት እስከ ትንሣኤ ያለውን የቤዛነትንና የማዳን ሥራውን ግሩም በኾነ ኢትዮጵያዊ አሣሣል ጥበብ የሚገልጽ ነው፣ ሌሎችም መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ በግድግዳዎች ላይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የተጠበቡባቸውና የተራቀቁባቸው የተለያዩ የቅዱሳን መላእክትና የሰማዕታት ሥዕሎች ይታያሉ፡፡

በዐፄ ሚኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያኑ የሚገኙ የተሣሉ የቅዱሳን ሥዕላት እና ቁሳቁሶች የሐዋርያት ምስል በዐፄ ምኒልክ ትእዛዝ በአለቃ ዮሐንስ የተሣለ ነው:: ይህ ሰው ከዚህ ሥዕል በተጨማሪ ሙሉ ሥዕሎችን በአለቅነት እየተቆጣጠሩ ያሣሉ ናቸዉ፡፡ የኢየሱስን ልደት የሚያሳይ ምስል፣ከመስቀል እስከ ስቅለቱ ያለው እና ከመስቀል አውርደው ወደ አዲስ መቃብር ሲወስዱት ያለዉን ገዞ የሚያሳይ፣ የማርያምን ስደት የሚያሳይ ምስል፣ የማርያምን እረፍት እና ለቶማስ ተገልፃ መገነዣዋ ስትሰጠው የሚያሳዩ ምስሎች፣ ዕለተ ምጽአትን የሚያሳይ ምስል፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ተአምራት የሚያሳዩ ምስሎች፣ የሆሳዕናን ቀን እና የዕለተ ኃሙስን የሚያሳዩ ምስሎች፣ የ318ቱ ሊቃውንት የመሩትን ሥዕሎች ስለ ኃይማኖት መከፋፈልን የሚያሳይ የጉባኤ ኒቂያን የሚያሳዩ ምስሎች፣ የዲያቢሎስ መልኩ አስፈሪነቱን የሚገልጽ ምስል (ዲያቆን ኃይሉ ጌታነህ 10/02/2013 ቃለ መጠይቅ)

**መልአኩ ቅዱስ ራጉኤል**

መጋቤ ብርሃናት ቅዱስ ራጉኤል እግዚአብሔርንና የሰውን ልጆች ለማገልገል የተመደበበትን ተልእኮ ብርሃናትን መመገብና ማስተናገድ፤ ፀሐይንና ጨረቃን ከዋክብትንም በተመደበላቸው ሰዓት ሳይዛነፉ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ በክፉዎች መናፍስትም ላይ ሥልጣን አለው፤ ዲያብሎስን የሚበቀለው አጋንንትንም የሚበቀላቸው ከከበሩ መላእክት አንዱ ራጉኤል ነው፤ (ሔኖ 6፡39-42) ። ይህም በመኾኑ ቅዱስ ራጉኤል መጋቤ ብርሃናት፣ ሰዳዴ አጋንንት ይባላል፤ በክፉ መንፈስ ተይዘው የሚሠቃዩትን፣ አጋንንትም ይዘው የሚያሠቃዩአቸውን ሰዎች ለመርዳትና ለመፈወስ ኃይል አርያማዊ የተሰጠው መልአክ ነው (*የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት 1991፡6 ዓ.ም*)።



**ምስል 12፡ ጥንታዊ ቅዱስ ራጉኤል ምስል (09/02/2013) በሳምራዊት**

ከ1877 ዓ.ም ህዳር 25 ቀን ታቦተ ህጉ ከነበረበት ከዋሻው ወጥቶ ወደ ቤተክርስቲያኑ ገባ። ከስእላቶቹ ጋር ተያይዞ ከሚነገር ተረክ መካከል አንዱ ስእላቶቹ ላይ ዐፄ ሚኒልክም መሬት ላይ ሆነው ሲቀበሉ ቅዱስ ራጉኤል በትረ መንግስቱን ከመሬት ከፍ ከሰማይ ዝቅ ብሎ ሲሰጣቸው ነው ያዩት ህልም ለሰዓሊው ነግረውት ሰዓሊው በዛ መልክ ስሏቸዋል። ከዚያም በኋላ እንጦጦ በዐፄ ምኒልክ እንደገና ስትቀረቀር ንጉሡ በሕልማቸው መልአኩ ራጉኤል በትረ መስቀል ሲሰጣቸው በማየታቸው ቤተክርስቲያን በመላኩ በቅዱስ ራጉኤል ስም ለማሠራት

ይቆርጣሉ። እንዲሁም በስተቀኝ በኩል ጸሀፊ ትእዛዝ ገብረስላሴ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ ጊዜ የፅህፈት ሚኒስተር ተስለዋል። (ዲያቆን ኃይሉ ጌታነህ 10/02/2013 ቃለመጠይቅ)



**ምስል13፡ ቅዱስ ራጉኤል ለዐፄ ምኒልክ በትረ መንግሥት ሲሰጥ የሚያሳይ ምስል (09/02/2013) በሳምራዊት**

ሌላው ተረክ የቤተክርስቲያኑ በሮቹ ላይ ደግሞ ለዐፄ ልብነ ድንግል ቅዱስ ራጉኤል በራእይ እየተገለጠ ብዙ ማስታወሻ ይነግራቸው ነበር ከግራኝ አህመድ ጋር የት ቦታ ላይ ጦርነት እንደሚገጥማቸው ግዛታቸው የት የት ቦታ እንደሆነ ቤተ መንግስታቸው የት ቦታ እንደሚሰሩ ከሳቸው አልፎ ሚኒልክ የተባለ ንጉስ በዚህ በ1819 ክፍለ ዘመን 1870 ዓ.ም በዚህ በእንጦጦ አካባቢ ላይ እንደሚመጣ እና ቤተ መንግስት በዚህ ቦታ ላይ እንደሚመሰርት ሁሉ ለዐፄ ልብነ ድንግል ቅዱስ ራጉኤል በህልም በራእይ ነግሯቸው እንደነበረ ሁሉ በር ላይ በስእል ተስሎ ተሰቅሎአል። (ዲያቆን ኃይሉ ጌታነህ 10/02/2013 ቃለመጠይቅ)

**የነቢዩ ኤልያስ እና የነቢዩ ኤልሳዕ**

ነቢዩ ኤልያስ ፍጡር እንደመሆኑ ተርቦ እና ደክሞት ሳለ እሱ ቁራዎች ከሰማይ ህብስት እያመጡ ሲመግቡት ነው የሚያሳየው። እሱ የነበረበት ቦታ ደግሞ ከጀርባው ውሃ ይፈሳል አለት ነገር ይታያል ያ እልም ያለ በረሃ ውስጥ እንዳለ ያመለክታል።
ነብዩ ኤልያስ ኤልሳእን “ካንተ ከመለየቴ በፊት ምን ትፈልጋለህ” ሲለው “በረከትህ እጥፍ ድርብ ሆኖ ይደርብኝ” ብሎ ለመነው። “ከባድ ነገር ለመንከኝ ” ። ኤልሳእ እና ኤልያስ እያወሩ ሲሄዱ

በመካከላቸው የእሳት ፈረሶች ገብተው ከፈሏቸው ይላል፡፡ ኤልሳእም “መምህር ሆይ ”እያለ ወደ ሰማይ አንጋጦ በሚጮህበት ሰዓት ኤልያስም መጎናጸፍያው ለሁለት ከፍሎ አንዱን ለራሱ፣ ሁለተኛውን ለኤልሳእ ላከለት፡፡ ኤልሳእም መጎናጸፍያውን ይዞ ሄዶ የኤልያስ አምላክ ሆይ እያለ ባህሩን ሲደበድብ ባህረ ዮርዳኖስ ለሁለት ተከፈለና ተሻገረ ይላል፡፡ (ዲያቆን ዮሃንስ ወልደጊዮርጊስ 09/02/2013 ቃለመጠይቅ)



**ምስል 14፡ የነቢዩ ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ሲያርግ እና ነቢዩ ኤልሳእ ምስል (09/02/2013) በሳምራዊት**

**ኮርኒስ** የተሠራበት ሽክላ እና ጣውላ በመጠቀም ነበር የተሠራበት



**ምስል 15፡ ኮርኒስ (09/02/2013) በሳምራዊት**

**መሰላል**፡ ከ140 ዓመት በላይ ያስቆጠረ ለሕንጻ መሥሪያነት ያገለገለ መሰላል ቤተ ክርስቲያኑ ሲሰራ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ አሁንም በቤተክርስቲያኑ ውስጥ አለ፡፡ በሕንፃው ውስጥ ከወለሉ እስከ ጣሪያው ድረስ ሙሉ የቤቱ ቁመት አላቸው፡፡ ከቁመታቸውም የተነሳ ከቤተክርስትያኑ ውስጥ ሳያቋርጡ መውጣት አይቻልም፡፡ መሰላሎቹ ለጥገና ተብለው እንደተሰሩ

ይታመናል። አገልግሎቱም ስአሊዎቹ ስእላቶቹ በየቦታው የሚሰቀሉት የነበረው በመሰላሉ ነው። አሰራሩም አጠቃላይ ከፅድ ወጥ እንጨት የተሰራ እና ምንም ቅጥልጥል የለውም። እዚሁ ቅድስት ውስጥ ተገጣጥሞ የተሰራ ነው። አጠቃላይ ከ15 ሜትር በላይ ርዝመት ያላቸው መሰላሎች ናቸው። እስከ አሁን ድረስ ቅርስ ሆኖ በመንብኘት ላይ ይገኛል። (ዲያቆን ኃይሉ ጌታነህ 10/02/2013 ቃለመጠይቅ)





**ምስል 16፡ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የሚገኙት መሰላሎች (10/02/2013) በሳምራዊት**

**በዐፄ ዳዊት የተፈለፈለው ዋሻ**

እንጦጦ በዐሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን የንጉሥ ዳዊት ከተማ እንደነበረችና ንጉስ ዳዊት ከወጥ ድንጋይ አስፈልፍለው ያሳነጹት የሰባት መቶ ዓመት ዕድሜ ባለጸጋ የዋሻ ቤተ ክርስቲያን በራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ አለ። ዋሻው ምንም የመጎዳትና የመጎሳቆል ምልክት ሳያሳይ ከነ ሙሉ ግርማ ሞገሱ በእንጦጦ ራጉኤል ሕንጻ ቤተክርስቲያን ጎን በቀኝ በኩል ይገኛል።

ዐፄ ዳዊት የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ አባት ናቸው። ከ1375-1380 ባለው ዓመተ ምሕረት ውስጥ ቤተ መንግሥታቸውን በዚህ በእንጦጦ ላይ ሠርተው ሲኖሩ በዚያን ሰዓት ያስፈለፈሉት ዋሻ ነው። ይህን ዋሻ ካስፈለፈሉ በኋላ ለግምዣ ቤት ነው እሳቸው በዋናነት የተጠቀሙት። ከቤተ መንግሥታቸው ውስጥ ያሉትን ወርቆቻቸውን፣ ብሮቻቸውንና ውድ የኾኑ የዕንቁ ቁሳቁሶቻቸውን በሙሉ እዚህ ዋሻ ውስጥ ነበር የሚያስቀምጡት። ዐፄ ዳዊት ከሀገራቸው ውጭ

በሚኼዱበት ሰዓት ከቤተ መንግሥታቸው ያሉትን ዕቃዎች ጠላት እንዳይሰርቅባቸው የተለያየ ችግር እንዳይደርስበት በዚህ ዋሻ ውስጥ እያስቀመጡ ይኼዱ እንደነበር በታሪክ ተመዝግቧል። ከዚያ በመቀጠል ከዐፄ ዳዊት እስከ ዐፄ ምኒልክ ድረስ የ 500 ዓመት ልዩነት አለ። በዚያ መካከል ግን እንደዚሁ የተለያዩ መናንያንና ባሕታውያን ይኖሩበት እንደነበር ይነገራል።

ከ1870-1877 ዓ.ም ሥርዓተ ቅዳሴው በዚህ ዋሻ ውስጥ ይከናወን ነበር። ምኒልክም በዚህ ዋሻ ውስጥ ሥርዓተ ቅዳሴ ይሳተፉ ነበር። በዚህ በኹለተኛው በር ቅድስት ተብሎ በሚጠራው ክፍል ውስጥ በመጋረጃ በተለየ ቦታ የእሳቸው ዙፋን ተቀምጦ ይገኛል። በቤተ መቅደስ ያለው በር ተዘግቶ በቅድስት ያለውን በር በመጋረጃ ይዘጋና እሳቸው መካከል ላይ ኾነው ሥርዓተ ቅዳሴ ይሳተፉሉ።

በዋሻው በስተግራ በኩል ያለው የንጉሡ ተከታዮች እና እቴጌይቱ ሲያስቀድሱ በዋሻው በስተቀኝ በኩል ያለው ደግሞ በመጋረጃ ተጋርዶ እስከ መንበሩ ድረስ ያለውን ቦታ እንደ ቤተ መቅደስ ይገለገሉበት ነበር። መሀል ላይ ያለው ክፍል ቅኔ ማሕሌት ነው። ዐፄ ምኒልክ ብዙ ካህናት ነበሯቸው። በዘመኑ ቅኔ ማሕሌት ከዚያ አነስ ያለ ክፍል ስለኾነ ምእመኑ በውጪ የሚያስቀድስበት ሰፊ ዳስ የተሠራ ሲኾን ከቅኔ ማሕሌቱ ተያያዥነት ባለው መልኩ ተሠርቶ አገልግሎት ይሰጥ ነበር። (ዲያቆን ኃይሉ ጌታነህ 10/02/2013 ቃለ መጠይቅ)

ዋሻው ከአንድ ወጥ ከሆነ ድንጋይ የተፈለፈለ ሲኾን በሰው እጅ እንደተሠራ ይነገራል። ውስጡንም ዐፄ ዳዊት ሲያስፈለፍሉ ሦስት ክፍሎች እንዲኖረው አድርገው አሠርተውታል። እሳቸው ግምጃ ቤት ቢያደርጉትም ከእኔ በኋላ የሚመጣ ትውልድ ታቦት ይኖረዋል፤ ቤተ መቅደስም ያደርገዋል የሚል ምኞትና እምነት ስለነበራቸው ራእያቸው ተሳክቶ ዐፄ ምኒልክ ለሰባት ዓመታት ያክል እንደ ቤተ መቅደስ ተገልግለውበታል። ቤተ መቅደስ ቅድስት እና ቅኔ ማሕሌት ኾኖ ሲያገለግል የነበረው ዋሻ በወቅቱ መብራት ስላልነበረ ጧፍ የበራበት እና ዕጣን የጨሰበት ጥላሸት በጣራው ላይ ይታያል። በእንጦጦ አከባቢ የሚገኝ ድንጋይ ‹በሐ› ድንጋይ ይባላል። በጣም ለስላሳ እና ቀዝቃዛ ሲኾን ማታ ላይ ግን ሙቀት የመፍጠር ባሕርይ አለው። በጥንቃቄ ካልተያዘ ግን ዝናብ ወይም ውኃ የሚያገኘው ከኾነ በቀላሉ ሊናድ የሚችል እና ወደ አፈርነት ወይም ወደ ጭቃ የሚቀየር ነው። ከኻያ ዓመታት በፊት በአርማታ ተጠግኖ አጠቃላይ የሚፈሰው ውሐ ቆሞ በክረምትም ኾነ በማንኛውም ጊዜ ለጎብኚዎች ከዓመት ዓመት ክፍት ኾኖ ይገኛል። ይህ ዋሻ ከታሪካዊነቱ ከመጎብኘቱ በተጨማሪ የክርስትና ቤት ኾኖ

አገልግሏል እስከአሁንም ድረስ እያገለገለ ነው፡፡(ዲያቆን ዮሐንስ ወልደጊዮርጊስ 9/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)፡፡





**ምስል 17 ፡ የዋሻው ውጫዊ ገጽታ ምስል 18፡ ውስጣዊ ገጽታ (09/02/2013) በሳምራዊት ከዋሻው ጋር ተያይዞ የሚነገር ተረክ**

ዐፄ ዳዊት ከግብፅ የጳጳሳት የክርስቲያን መሞት መልእክት ደረሳቸው እና ክተት ሠራዊት አሉ፡፡ በሱዳን- ካርቱም ሠራዊቱ ከከተተ በኋላ 'የፀብ መጀመርያው ውሃ ነው ይላሉ' እና የአባይን ውሃ ገደቡት በያዙት ነገር በዱላም በድንጋይም ሁሉ አቅጣጫ በማስቀየር የአባይን ውሃ ገድቤዋለሁ ከመጣህ ና ብለው ሲናስርን ወይም ሲናር በሚባል ቦታ ውግያ መሸጉ፡፡ ከዛ በኋላ የግብፅ መንግሥት ቀጥታ መዋጋት ሳይሆን ከግብፅ ክርስቲያኖች ጋራ መስማማት ነው የጀመሩት፡፡ ተስምምትን ተፋቅረን እንኑር ይህንን የመጣብኝን የኢትዮጵያ አንጋፋ መንግሥት ብቻ የሚመለስበትን ነገር አስተካክሉልን፣ አገራችን አይውረር እኛ እንስማማ በማለት ተስማምተው፤ የኢትዮጵያ መንግሥት እባክህ ይቅር በል የሚል አምሃ (ስጦታ) ልኮ በግመል ወርቁ ብሩ ተጭኖ መጣለት "ተስማምተናል እና እባክህ ተመለስ" ከሚል መልእክት ጋር፡፡ ዐፄ ዳዊትም እኔ በእናንተ በክርስቲያን ወገኖቼ እና በእግዚአብሔር ቀንቼ ነው እንጂ የእናንተን የግብፅ ወርቅ ላግበሰብስ እና ልጭን አልመጣሁም እንኳን እናንተ ተስማማችሁልኝ የክርስቲያኖች ነፃነት ነው የምፈልገው በሚል ወርቅና ብሩ መልሰው መልእክት ላኩ፡፡ ይልቁንም በእናንተ አገር የምታመልኩበት መገለጫ የሚሆን ኩፌቶ፣ አክሊለ ሱክ እና ግማደ መስቀል አለ እና ከሱ አንደኛውን ብትልኩልኝ ብሎ ደብዳቤ ፃፈላቸው፡፡ ከዚህም በኋላ ንጉሡ ተመካክረው እንደውም በክርስቲያን አገር ኢትየጵያ የእየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀል ቢኖር ለእኛ ትልቅ ጥቅም አለው የክርስቲያን ቦታ ነው ብለው ወሰኑ እና ዐፄ ዳዊት ድጋሚ ተጠርተው ሄዱ፡፡ እዛው ግማደ መስቀሉን ለመቀበል እንደሄዱ በቅሎ ረግጧቸው ወድቀው አረፉ፡፡ ከዛም ልጃቸው ዘርአያብቆብ የጌታ ግማደ መስቀል በአንድ በቅሎ፤ አስከሬናቸው በሌላ

በቅሎ በኬንያ በኩል ነው ይዞ የመጣው ይባላል ። አሁን ወሎ ክፍለሃገር በምትገኘው ግሸን ማርያም ደብረከርቤ ይገኛል። ከግማደ መስቀሉ ጋራ ሉቃስ የሳለው የእመቤታችን ምስል፣ የእመቤታችን ተአምር መጥተዋል። ዐፄ ዳዊት በደምብ የሚታወቁት የእየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀል ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ በማስመጣት ነው። ዐፄ ዳዊት በግብፅ ሀገር የክርስቲያኖች መገፋት ሲሰሙ መጀመርያ ያደረጉት ከመኳንንቶች ጋር ተወያይተው ሱባኤ ገቡ ከዛም እመቤታችን ማርያም ተገልፃላቸው ሂድ ድል ታደርጋለህ ተብለው ነው የዘመቱት።" (ርእሰ ደብር አጋፋሪ ሰለሞን 10/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)



ምስል 19፡ አጥኚዋ ከርእሰ ደብር አጋፋሪ ሰለሞን ጌታነህ ጋር (ቤተ ክርስቲያን 10/02/2013) በሳምራዊት

***ሥዕለ ማርያምና መንበር፡-*** *መንበሩ በዐፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት የነበረ ሳይሆን ቤተመቅደስ ስለሆነ ከዛ በኂላ የተቀመጠ ነው። ከመንበሩ በላይ ያለችው ስእል በዐፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት የነበረች ጥንታዊ ስእል ከ133 ዓመት በላይ እድሜ ያስቆጠረች ናት።በዚህ ዋሻ ውስጥ ዐፄ ምኒልክ ከቅዱስ ራጉኤል ታቦት ጋር ይዘዋት የመጡ የድንግል ማርያም ስእል ይገኛል እና ምእመናን የልባቸውን ፍላጎት በወረቀት ፅፈው የስቀምጡባታል፤ ፀሎት ሰሚ እንደሆነች ብዙዎች ይመሰክራሉ። ከስእሉ አከባቢ አፈር ይዛ የሄደች አንድ መካን ሴት መውለድዋን መጥታ ምስክርነት የሰጠችበት ግዜ አለ። በዋሻው ውስጥ የአይን ማረፍያ በሆነችው በስእለ ማርያም በቁርጥራጭ ወረቀቶች ተከባ ትታያለች። እነዚህ ወረቀቶች በዚህ ስፍራ መጥተው የተሳለሙ እና የልቦናቸው መሻት ፅፈው ተስለው ያስቀመጧቸው መልእክቶች ናቸው። (ርእሰ ደብር አጋፋሪ ሰለሞን ጌታነህ 10/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)*





**ምስል 20፡ ስእለ ማርያምና መንበር (10/02/2013) በሳምራዊት**

**ከቤተክርስቲያኑ በስተሰሜን ምዕራብ ያለ ዋሻ**

በቤተክርስቲያኑ ሰሜን ምእራብ አቅጣጫ ጋር ሌላ ጥናታዊና ታሪካዊ ዋሻ አለ። ከዋሻው በስተቀኝ በኩል የሚገኘው በወቅቱ ለቤተልሄምነት አገልግሎት ይሰጥ የነበረ አነስተኛ ዋሻ ነው። የዋሻው ግድግዳ ውሀን ያዣል። ዐፄ ዳዊት ያስፈለፈሉት ዋሻ ሲሆን ዐፄ ሚኒልክ ከመጡ በኋላ ትልቁን ዋሻ ቤተ መቅደስ ሲያደርጉ ይኼኛውን ትንሹን ዋሻ ደግሞ ጊዜያዊ እንደ ቤተልሄምነት ይገለገሉበት ነበረ። ወደ ውስጥ የተወሰነ ይገባል። ብዙ ርቀት የለውም በአጠቃላይ ከአንድ ወጥ ድንጋይ በመጥረቢያ የተሰራ ነው። ውሀ አለው፤ ይህ ክረምት ላይ ነው የሚከሰተው ከውስጡም ይመነጫል። ከህዳር በኋላ ይደርቃሉ ሰው እንደልብ ወደ ውስጥ ይገባል። ምእመናን ሲመጡ እንደ ጠበል ይጠቀሙበታል። ለመጠጣት ባይኾንና እጃቸውን ፊታቸውን ይደባብሱበታል (ዲያቆን ዮሐንስ ወልደጊዮርጊስ የ09/02/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)።



**ምስል 21፡ ከቤተክርስቲያኑ በስተሰሜን ምዕራብ ያለ ዋሻ (09/02/2013) በሳምራዊት**

**የመልአከ ኃይል ተድላ ወልደ ጻድቅ ዋሻ**

እንጦጦ በከፍታው እንደሚታወቀው ሁሉ በዚህ አካባቢ በጫካ ውስጥ በጣሊያን ወረራ ጊዜ ከጠላቶች ለመሸሸግ የሰራቸው በርካታ ዋሻዎች ይገኛሉ፡፡ በግምት 20 ሜትር እንኳ የማይሞላው ካብ ስር የቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ የነበሩ መልአከ ሀይል ተድላ ውልደጻዲቅ በ1927 ዓ.ም ያስፈለፈሉት ወጥ ቦታው ዳገታማ የሆነ ጠባብ በር እና መስኮትም ያለው አነስተኛ ዋሻ ከቤተክርስቲያኑ ግቢ ውጪ የሚገኝ ዋሻ አስፈለፈሉ፡፡ ይህ ዋሻ በ1928 ዓ.ም ላይ ጣሊያን ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ሀገር ቤት ይገባል ሲባል ቀደም ብለው ጣሊያኖች በተለያየ በኤሊኮፍተር በጆት እንዲያጠቋቸው ነው የሰሩት፡፡ ጣሊያን እንደመጣ መጀመሪያ እዚ ነው የመጣው የሚኒልክ ቤተ መንግስት እዚህ ስለነበረ ቤተ መንግስታቸውን አቃጥሎባቸዋል፡፡ የራሱን ካምፕ ሰርቶ እዚህ ይኖር ነበረ፤ በዛን ሰዓት እዚህ ዋሻ ውስጥ ተሸሽገውበት ነበር፣ ውስጡ ሰፋ ያለ ነው፡፡ በመካከል ደግሞ ብዙ አባቶች ባህታዊያን እዚህ ይኖሩ ነበረ በሩ ላይ መቀመጫ አለ ፊቱ ወደ ምስራቅ ስለሆነ ጠዋት ፀሐይ ይሞቁበት እና ፀሎት መፅሀፍ ያነቡበት ነበር፡፡ ካብ አለ ካቡ እንደአጥር ሆኖ ያገለግላል፡፡ ( ዲያቆን ዮሀንስ ወልዴ የ09/02/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)



ምስል 22፡ የመላእክ ኃይል ተድላ ወልደ ፃዲቅ ዋሻ (09/02/2013) በሳምራዊት

## የአብነት ትምህርት

በ1960 ዓ.ም በአታ ለማርያም ገዳም የዐፄ ምኒልክ የሞት መታሰቢያቸው፣ እንጦጦ ራጉኤል የሕያውነት መታሰቢያቸው እንደኾነ ታሪክ በመጥቀስ በተደረገው ስምምነት መሠረት የበአታ ለማርያም ገዳም ፈለገ ብርሃን የተሰኘ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በእንጦጦ ራጉኤል ቅጥር ግቢ በማቋቋም መምህራንና ተማሪዎች ከትምህርታቸው በተጓዳኝ ቤተ ክርስቲያኑን እንዲያገለግሉ በመደረጉ ለ12 ዓመታት ተቋርጦ የቆየው ቤተ ክርስቲያኑ መደበኛ አገልግሎት እንዲያገኝ ተደረገ፡፡ ይህ ውጤት ሊገኝ የቻለው ታሪክና ቅርስ በመጥፋቱ ይህም ታላቅ የዐፄ ምኒልክ ሕያውነታቸው የሚታሰብበት የአምልኮት ቦታ በመዘጋቱ ከፍተኛ ቁጭት ባደረባቸው እንደእነ አቶ መዝራዕተ አብ ሠርጡ ከታዕካ ነገሥት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና ከአካባቢው ምእመናን ጋራ በመነጋገር የዐፄ ምኒልክ መታሰቢያ ቦታ ስለኾነ የአብነት ትምህርት ቤቱ 1960 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ በዚያ ሰዓት የቅኔ፣ የድጓ፣ የአቋቋም፣ የሐዲስ ኪዳን መምህር እነዚህ አራት ጉባኤ ተተከሉ፡፡ ሊቃውንቱ ከዚህ እየፈለቁ ግማሾቹ ወደ ከተማ ሲኼዱ በጣም ትልቅ ታሪክ ተሠርቶበት ብዙ ሊቃውንታት አፍርቶ እንደገና የመጀመሪያው ውድቀት ተወግዶ በእነዚህ ሊቃውንት ከ1960 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ በእነዚህ ሊቃውንት ቅዳሴውም ኹሉ በበለጠ ኹኔታ አገልግሎት ሲሰጥ ቆየ፡፡

አሁን ላይ በታሪክ ቦታነቱም የሕንጻው አመሠራረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ታታሪነት፣ ዐዋቂነትና ክሂሎት መግለጫ ኾኖ በግልፅ ይታያል፡፡ ስለኾነም ታሪክነቱን በቤተክርስቲያኑ ስም እየገለጽን ከ1960 ዓ.ም አንሥቶ እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ከቤተ ጉባኤ በሚፈልቁ ሊቃውንት በአግባቡ ሲገለገል ቆይቶ በ1994 ዓ.ም በትምህርት ቤቱ እና በአንዳንድ ግለሰብ መካከል በተፈጠረው የግጭት መንሥኤ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው በመበተናቸውና በጆቱም በመታጠፉ የተነሣ የጉባኤው መፍረስ ይበልጥ ቤተ ክርስቲያኑን ከዳጥ ወደ ማጥ አስገብቶታል፡፡ ይኹን እንጂ ቤተ ክርስቲያኑ በአንጻራዊው የአገልግሎቱ ዘርፍና የልማት እንቅስቃሴው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ አሁን ካለበት ዘመን ላይ ደርሷል፡፡

የመጨረሻው ክስተት በ1993 ዓ.ም ተመልሶ ተዘጋ፡፡ እዛው በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት ተአከለ ነገስት ተመልሰው ትምህርት ቤቱን ወደ ባእታ ወስደውታል፡፡ እስከ አሁን ብዙ ጥረት ተደርጓል፡፡ አልተሳካም ካልሆነ እንኳን ወይ እራሱን ችሎ ትምህርት ቤት መኖር አለበት በማለት ብዙ ታግለዋል ጥረቱ አልተቆረጠም፡፡ አሁንም መምህራኑ ግን በተቋም ደረጃ አልተቋቋሙም፡፡ የቤተክርስቲያኑ ትልቁ ክስተቶች የሚባሉት እነዚህ ናቸው፡፡ (የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሄት ሁለተኛ እትም፡፡ ታህሳስ 2000፣ 29-30)



**ምስል 23፡ የአብነት ትምህርት ቤት (09/02/2013) በሳምራዊት**

**የተለያዩ በግቢው ውስጥ የሚገኙ አፀዶች** ዐፄ ሚኒሊክ በዘመነ መንግስታቸው እዚህ ቤተክርስቲያን ሲቆረቆር ለቤተክርስቲያኑ ሞገስ እንዲሆን ይህንን ዛፍ ተክለዋል፡፡ ዛፎቹን ቤተ ክርስቲያን ናት በየዘመኑ ያሸጋገረችው፡፡ ለምሳሌ እዚህ ታላላቅ ግራሮች አሉ የግራር ዛፍ በቤተክርስቲያን እንዲተከል የሚፈለግበት ግራር እሾካማ ስለሆነ ማንኛውም አውሬ ሊመጣ አይችልም፡፡ ወፎች ደግሞ አውሬ እንዳያጠቃቸው እሾካማው ላይ ነው ጎጇቸውን የሚሰሩት ጠዋትም ተነስተው የቤተ ክርስቲያን ዝማሬያቸውን ሲያቀርቡ ለቤተ ክርስቲያን ሞገስ ነው፡፡ ይህ እድሜ ጠገብ ግራርና የጥድ ዛፍ ዐፄ ሚኒልክ በዘመናቸው የተከሉት ሲኾን የመጀመሪያው የጽህፈት ሚኒስትር ጸሀፊ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ ወልደ አረጋይ እና የንጉሰ ነገስቱ ባለቤት እቴጌ ጣይቱ በመታሰቢያነት  በዘመናቸው ሁሉ እድሜ ያስቆጠረ ዛፍ ተክለዋል፡፡ ብላቴን ህሩይ ወልደስላሴ ለመታሰቢያነት የተከሉት ዛፍ አለ፡፡ አለቃ ገብረሀና  ሁል ጊዜ በቀልድ ነው የሚነሱት በምሳሌያዊ ንግግራቸው ነው የሚነሱት እና እሳቸው በመታሰቢያነት የተከሉት ዛፍ አለ፡፡ ትልቁ ዛፍ ንፋስ በቅርቡ ገንጥሎብን ነው ንጉሰ ነገስቱ ዐፄ ሚኒልክ በነበሩበት ዘመን ኢትዮጵያን በሀይማኖት ሲያስተዳድሩ የነበሩት ግብጻዊ አቡነ ማቲዎስ ናቸው የተከሉት፡፡ ይሄንን ታሪካዊ ነገሩን ለመጠበቅ ብለን ዙሪያውን አስጊጠነዋል በእንክብካቤ ለመያዝ ብለን ነው፡፡

እዚህ ቤተ ክርስቲያን ላይ በተለየ መልኩ ዛፍን በመትከል ታሪካዊ አሻራ የተቀመጠበት ነው፡፡ ለትውልድ የሚተላለፉ ዕድሜ ጠገብ ዛፎች አሉ (የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደሪ የመልአከ ኃይል ቆሞስ አባ ሳሙኤል አስፋው የ9/2/2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅና ምልከታ)፡፡



**ምስል 24፡ በቤተክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ የሚገኙ ዛፎች (09/02/2013) በሳምራዊት**

**የዝክር ቤት፡-** ወ/ሮ ዘውዲቱ መሸሻ ይባላሉ፤ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ቤት አሠርተዋል፡፡ የቤቱ አገልግሎትም ለፍስለታ ጾም ጊዜ ሱባኤ መያዣ፣ ለዝክር፣ ለማህበር ምግብ መመገቢያ ነው፡፡ የቤቱ አቀማመጥም ከስር ፉካ ነው፡፡ በዚህ ፉካ ውስጥም ሟች ቤተሰቦቻቸው ተቀብረውበታል፡፡ በመኖሪያ ቤታቸው 40 ወላጅ አልባ ህጻናት አሳዳጊ ናቸው፡፡ ከ35 ዓመት በላይ ቤተክርስቲያኑ ላይ ሰዓታት ከካህናት ጋር ይቆሙ ነበር፡፡ ከቅዳሴ በኋላ ካህናቶቹን ምግብ ያበላሉ፡፡



**ምስል 25፡ ዝክር ቤት እና ፉካ (09/02/2013) በሳምራዊት**

## 5.2. በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን በሙዚየም ውስጥ የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎች

የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ሙዚየም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ካፈራቻቸው ታሪካዊ ቦታና ቁሳዊ ባህሎች ወደሚገኙበት ከመዲናችን ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት በስተሰሜን በኩል በደን ተከባ የምትገኘው ጥንታዊቷ የዐፄ ዳዊትና የዐፄ ምኒልክ መናገሻ ከተማና ቤተመንግስት የነበረው እንጦጦ ላይ የሚገኘውን ታሪካዊ ሙዚየም አለ፡፡ ይህ ሙዚየም የተሰራው የሀገሪቷን ታሪክ ለመጠበቅና ለትውልድ ለማስተላለፍ ሲሆን በ1872 ዓ.ም

ተሰራ። አገልግሎት የጀመረው በ 2006 ዓ.ም ነው። ከዛ በፊት ግን በምድር ቤቱ ውስጥ የተለያየ ጊዜ ተቀምጠው ነበር። (ቀዳማዊ ትዕይንቱ ለዳግማዊ ምኒሊክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ርዕሰ አድባራት እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን) ግቢ ውስጥ ለትውልድና ለሀገር የሚጠቅም ታላቅ የቅርስ ሙዚየም ይገኛል። እዚህ ሙዚየም ውስጥ የቤተክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት እና የተለያዩ ነገስታት ለቤተክርስቲያን በስጦታ ያበረከቱት ብርቅና ድንቅዬ እቃዎች ይገኛሉ። ወደ ሙዚየሙ ለሚመጡ ጎብኚዎች የትራንስፖርት አገልግሎት አመቺ እንዲሆን በፊት የነበረው ገረጋንቲ መንገድ በአስፋልት ንጣፍ ቤተ ክርስቲያኑ በር ድረስ ተሰርቷል። ሙዚየም ውስጥ በርካታ ጥንታዊ ቅርሶችን ያካተተ ሲሆን ቤተክርስቲያኗ ካሏት ቅርሶች በከፊል በዚህ ስፍራ ይገኛሉ። ከዚህ ቦታ አብዛኞቹ ቅርሶች ወደ መርካቶ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ሄደዋል። እንጦጦ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት ቅርሶች ከነክብራቸው እንደተጠበቁ ይገኛሉ፤ አሁን ላይ በቅርስነት የተቀመጡ ናቸው፤ አገልግሎት አይሰጡም። በየ6 ወሩ በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ የቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን እና የባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች እገዛ ያደርጋሉ። ይኸውም በእንጦጦ ሙዚየም ውስጥ እና በአካባቢው ከሚገኙ ቅርሶች ከብዙ በጥቂቱ እነዚህ ናቸው። አሁን ወደ ሚዝየሙ የተዘዋወሩ ለቤተ ክርስቲያኗ የተበረከቱ ንዋየ ቅድሳት፣ አልባሳት፣ መገልገያዎች፣ የጦር መሣሪያዎች፣ የብራና መጻሕፍትና የመሳሰሉት ይገኛሉ። አልባሳት፣ ዋንጫዎች፣ መስቀሎች፣ ካባዎች፣ ከበሮዎች፣ ባንዲራዎች፣ የጠጅና የጠላ መጥመቂያ ጋኖች፣ በጣልያን ወረራ ጊዜ የተገኙና የተማረኩ ከ1888 ዓ.ም ጥንታዊ የወጨፎ መሣሪያዎችም፣ በርካታ የብራና ቅዱሳን መጻሕፍት፣ ከወርቅ፣ ከነሐስ፣ ከብር የተገኙ ጥንታዊ ቅዱስ ቁርባን የሚሰጥባቸው ጽዋዎች፣ ከነሐስ የተዘጋጁ ሻማ ማብሪያዎች፣ ከቀንድ እና ከዕንጨት የተሠሩ ጠላ እና ጠጅ መጠጫ ዋንጫዎች እና ሌሎች በርካታ ንዋያተ ቅድሳት እና ቅርሶች በደብሩ ሙዝየም ውስጥ ይገኛሉ። ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ቅርሶች ለጎብኚዎች በሚመች መልኩ የተቀመጡ ሲሆን ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ሰዎች በቤተክርስቲያኑ አስጎብኚዎች በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ገለጻ ይደረጋል። የመጎብኛ ሰዓቱም ከሰኞ እስከ እሁድ የሕዝብ በዓላትን ጨምሮ ለጎብኚዎች ክፍት ነው። ሰዓቶቹም ዘወትር ከጠዋቱ 3:00 እስከ 7:00 ሰዓት ከሰዓት በኋላ ከ8:30-11:30 ክፍት ነው። በአሁኑም ሰዓት በጥንት ይዘቱ እየተጎበኘ ይገኛል። ወደዚህ ታሪካዊ ሙዚየም ለመጎብኘት የተለያዩ ሰዎች ወደዚህ ጥንታዊ ከተማ ቦታ በመምጣት ታሪክን በማወቅ ላይ ይገኛሉ። በዚህ ሙዚየም ውስጥ ያልተካተቱ ብርቅና ድንቅ የሆኑ ቅርሶችን ለሕዝብ እይታ

ሳይበቁ የመርካቶ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገኛሉ፡፡ (ዲያቆን ኃይሉ ጌታነህ 10/02/2013 ቃለመጠይቅ)

**ሙዝየም፡-** በደብሩ ውስጥ አንድ አነስ ያለ ሙዚየም የሚገኝ ሲኾን በሙዚየሙ ውስጥ ያሉ አጠቃላይ ቅርሶች የዐፄ ምኒልክ ቅርሶች ናቸው፡፡ ዐፄ ምኒልክ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ከጨረሱ በኋላ ሙዝየሙን ለግምጃ ቤትነት ይጠቀሙበት ነበር፡፡ አሁን ቤቷ አነስ ስለምትል ያሉትም ቅርሶች የተወሰኑ ናቸው፡፡ ሙዙየሙ ከቤተክርስቲያኑ ጋራ የተሠራ ቤት ነው፡፡ የቆርቆሮና የሞራሌ ዕድሳት ተደርጎለታል፡፡ ጣውላዎቹ ጥንታውያን ናቸው፡፡ እያፈሰሰ ሲያስቸግር ሞራሌው በ2010 ዓ.ም ታድሷል፡፡ ጣውላው ጠንካራ ነው ከዚህ በፊት የነበሩት አገልግሎት ደጀ ሰላም ጠበል ጻድቅ የሚቀምሱበት፣ ሰው ሲሞት አስክሬን የሚያርፍበት ነበር፡፡ ሙዝየም ከመኾኑ በፊት ዐፄ ምኒልክ ግምጃ ቤት አድርገው ይጠቀሙበት ነበር፡፡ እንዲሁም አንዳንዴ ፍርድ ይሰጡበት እንደነበር የሚነገር ሲኾን በአሁኑ ወቅት በሙዝየሙ ውስጥ ከዚህ በታች በዝርዝር የተቀመጡ የተለያዩ ቅርሶች ይገኛሉ፡፡



**ምስል 26፡ በቤተክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ የሚገኝ ሙዚየም (09/02/2013) በሳምራዊት**

## የኢትዮጵያ ፓትሪያሪኮች

መጀመርያ ያሉት ግብጻዊው ጳጳስ አቡነ ማቲዮስ በዐፄ ምኒልክ ዘመን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ኾነው ብዙ ጊዜ የቆዩ እና ከንጉሡ ጋራ በዚህ ቦታ ብዙ ሥራ የሠሩ ቤተ ክርስቲያኑ ሲመረቅም ብዙ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ግብጻዊ ጳጳስ ናቸው። እዚህ እንጦጦ ላይ የአቡነ ማቴዎስ ግቢ እየተባለ በስማቸው የሚጠራ ቦታም አላቸው። ከኹለተኛው ጀምሮ የኢትዮጵያ

ፓትርያሪኮች በየዘመናቸው የተሾሙ ሲኾኑ በዐፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት አቡነ ባስልዮስ፣ አቡነ ቴዎፍሎስ፣ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ አቡነ መርቆሬዎስ፣ አቡነ ጳውሎስ እና አቡነ ማቴዎስ ናቸው። (ዲያቆን ዮሐንስ ወልደጊዮርጊስ 10/02/2013 ቃለ መጠይቅ)

**አልባሳት፡-** ጥንታዊ የካህናት ልብሶቹ ታቦቱ በዋሻው በነበረበት ጊዜ ጀምሮ ካህናት በቅዳሴ ጊዜ ይለብሷቸው የነበሩ ጥንታዊ የክህነት ልብሶች ናቸው ። የተለያዩ የምኒስትሮች፣ የአጋፋሪዎች፣ የካህናትና የዲያቆናት፣ የቤተ መንግሥት ሠራተኞች ይለብሱት የነበረ ለምድ፣ ሱሪዎች፣ ጥንታዊ እና የቤተ መቅደስ አልባሳተ ክህነት ይገኛሉ። በዐፄ ምኒልክ ጊዜ ይለብሱ የነበሩ አልባሳት ናቸው።



**ምስል 27፡ የካህናት፣ የዲያቆናት፣ ሚኒስቲሮች፣ አጋፋሪዎችና የቤተመንግስት ሰራተኞች አልባሳት (10/02/2013) በሳምራዊት**

**ካባ፡-** የዐፄ ምኒልክ የክብር ካባዎች መጋቢት 27 ቀን 1858 ዓ.ም ላይ የአንኮበር የሸዋ ንጉሥ ተብለው በነገሡበት ጊዜ ለብሰውት ነበር፡፡ ዐፄ ምኒልክ ለቤተ ክርስቲያኑ ያበረከቱት ካባ አለ፡፡ ካባው የእጅ ስራ ጥበብ ያለው ሲኾን በብር የተጌጠ ዙሪያው ከከፋይ ጨርቅ የተሠራ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከ154 ዓ.ም በላይ ዕድሜ ያስቆጠረ ሲኾን ሙሉ በሙሉ ከነሐስ የተሠራ ነው፡፡



**ምስል 28፡ የዐፄ ምኒልክ ካባ (10/02/2013) በሳምራዊት**

**መስቀል፡-** ከዐፄ ምኒልክ የተሰጠ ንጹሕ የብር መስቀል፣ የማርያም ልጇን ዐቅፋ ያለ ንጹሕ የብር መስቀል፣ ከንጹህ ነሐስ የተሠራች የክርስትና ማንሻ የነበረች መስቀል፣ ለነጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ 1900 ዓ.ም ላይ በስጦታ ያበረከቱት መስቀል፣ የዕንጨት የእጅ መስቀል፣ አክሡም መስቀል፣ ጎንደር መስቀል፣ ላሊበላ መስቀል ተብለው የሚጠሩ ከ140 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው መስቀሎች አሉ፡፡



**ምስል 29፡ የተለያዩ ከእንጨት፣ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሐስ የተሰሩ ጥንታዊ መስቀሎች(10/02/2013) በሳምራዊት**

**ማሕተም፡-** በወቅቱ ቄሰ ገበዙ/የኀላፊው የሚገለገሉበት የነበረ ማኅተም አለ፡፡



**ምስል 30፡ ማሕተም (10/02/2013) በሳምራዊት**

**መጥረቢያ፡-** አምስት አይነት አገልግሎት ትሰጣለች ሚስማር ትመታለች፣ ትነቀላለች፣ ትጠርባለች፣ ቅርፅ ታወጣለች ክዳኗ ሲከፈት ሚስማሮች ትይዛለች፡፡ ክብደት አላት ከብር የተሰራች ናት፡፡ ቤተክርስቲያኑ ሲሰራ አገልግሎት ትሰጥ ነበር፡፡ ንጹህ ናት፡፡ ከጀርመን አገር በስጦታ የተሰጠች እንደ መፍጫ፣ መጥረብያ እና እንደመዶሻ ይጠቀሙባት የነበረች በጣም አነስተኛ መሳርያ ነበረች፡፡



**ምስል 31፡ መጥረቢያ (10/02/2013) በሳምራዊት**

**ፅዋ፡-** የእየሱስ ክርስቶስ ደም በቅዳሴ ጊዜ መስዋእት ሆኖ የሚቀርብበርት ነው፡፡ ዮሀንስ እየሱስን የሚያጠምቅበት ምስል አለ ከውስጡ ያለው ጌጦቹ ሀረጎቹ ብርና ትልቁ ዋናው ምሰሶው ነሀስ ነው፡፡

ሰሀኑ ጎድጓዳው እና ሰፊ ነው መቀመጫው 4ቱ ወንጌላውያን አሉ፡፡ እየሱስ ሲጠመቅ፣ ሲሰቀል በዚህኛው ደግሞ ወደ መቃብር ሲወርድ የሚያሳዩ ጌጦች አሉ፡፡ የእየሱስን ገብረ ገድላት ያሳያሉ

ከዐፄ ሚኒልክ ለቤተክርስቲያኑ የተሰጠ ነው ማንኪያ 1 እርፈ መስቀል ይባላል። ሌሎቹ የቅርብ ጊዜ ናቸው አገልግሎታቸው ተመሳሳይ ነው።

የተሰራዉ ከወርቅ ፤ከብር እና ከነሀስ የተሰራ ነዉ ። ታቦቱ ዋሻ ውስጥ ከነበረበት ግዜ ጀምሮ የነበሩ ከ 140 ዓመት ዕድሜ በላይ አስቆጥረዋል። የሚያገለግለውም ስጋ ወደሙን ለማቁረቢያ ነዉ። ሀረግ እና የወይን የስንዴ ስእል አለው የሚፈታታ ነው እሱ ጽዋ የብር ነው። የመድኀኒአለም የማርያም 4ቱ ወንጌላውያን በጉብታ ከግርጌው የተሰራ ጽዋ አለ እሱ 4 ጉብታ እና ከላይ ያሉት ስእሎች ሰባቱ ወርቅ ናቸው።



**ምስል 32፡ ፅዋዎች (10/02/2013) በሳምራዊት**

**መፃሕፍቶች፡-** የብራና መጽሀፍት 9 ናቸው። መዝሙረ ዳዊት፣ ከቅዱስ ያሬድ ድርሰት መካከል አንድ የድጓ መጽሀፍ፣ ፆመ ድጓ፣ ዝማሬ መስዋዕት፣ ገድለ ማርቆስ፣ 4ቱ ወንጌላውያን፣ መልክአ የሀዋርያት የጳውሎስ፣ በመንፈቅ በመንፈቅ ተከፋፍሎ የታተመ መፅሐፍ ስንክሳር፣ አንደኛው ከመስከረም 1 እስከ የካቲት 30፣ ኹለተኛው ከመጋቢት 1 እስከ ጳጉሜ 5 ድረስ የሚነበብ፣ ዘወትር ከቅዳሴ በኂላ ስለ ቅዱሳን ጻድቃን ሰማእታት ስራቸው እና ተጋድሏቸውን የሚናገር ቅዱስ መጽሀፍ፣ የእያንዳንዱ የየእለታቱን ታሪክ መዝግቦ የያዘ ነው፣ በግእዝ ቋንቋዎች የተጻፉና ከፍየል ቆዳ የተሰሩ ናቸው። ቀለሞቹ እየተንጠባጠበ ነው የተሰራው። ወደ ኂላ ስንመለከት ከ150 ዓመት በፊት ቅርሶቹ የተሰሩት የቆዳ፣ የቀለም፣ የጨርቅ፣ የጣውላ፣ ፋብሪካ ባልነበረበት ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቀለም በጥብጣ፣ ብራና ፍቃ፣ መጽሀፍት ጽፋ ነበር። መጻህፍቶቹ አቡጀዲ ሰፍታ ትሸፍን ነበር። ጣውላ ፋብሪካ ባልኖረበት ጊዜ መስቀሎቹን ልዩ ልዩ የቤተክርስቲያን ቅርሶቹ በእጃቸው ጠርበው ይሰሩ ነበር። ወረቀቶቹ

ጥንካሬያቸው ልዩ ነው። ተአምረ ማርያም፣ ድርሳነ ሚካኤል ወገብርኤል፣ ዝማሬ ወምስአት ማለት መጽሀፍ ቅዱስ ያሬድ ድርስቶች መካከል አንደኛዋ ናት በቅዳሴ ጊዜ በቅኔ ማህሌት አገልግሎት ወቅት የሚሰጥ ነው። ዳዊት፤ 44ቱ ወንጌል፣ መፅሐፈ ሀዲስ ሃሰልስቱ (መልዕክተ ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ እና ይሁዳ) ድርሳነ ራጉኤል (ተሰርቆ ለ22 ዓመታት ያህል በፈረንሳይ ሀገር ቆይቶ የተለያየ ግብረ ተአምራትን በማድረግ ወደ ሀገር ቤት የተመለሰ)፣ ግብረ ሕማማት የእየሱስ ክርስቶስ ሕማም በሚታወስበት የህማማት ሰሞን ከሰኞ እስከ ቅዳሜ የሚነበብ ቅዱስ መጽሐፍ ነው።

ከላይ ከተዘረዘሩት ዉስጥ አብዛኛዎቹ በዐፄ ሚኒልክ ጊዜ የነበሩ ሲሆን በሙሉ የብራና መጽሀፍት ናቸው። ሁሉም ለቤተክርስቲያን አገልግሎት በዝማሬም በቅዳሴም ሲገለገሉባቸው የነበሩ ቅዱሳን መጻሕፍት ናቸው። የተወሰኑ ቅዱሳን መፃህፍት በዐፄ ኃይለሥላሴ ዘመን በ1925 ዓ.ም ማተሚያ ማሽን እስከመጣ ድረስ በእጅ የተፃፉ ናቸዉ።



**ምስል 33፡ መጻሕፍት (10/02/2013) በሳምራዊት**

**ባንዲራ (ሰንደቅ አላማ)** ፡- በ1933 ዓ.ም በአማርኛ እና በጣልያንኛ ቋንቋዎች የተፃፈ አንድ ባንዲራ ከጣልያን ሀገር የተሰጠ መደቡ አረንጓዴ የሆነ የቅዱስ ራጉኤል ምስል አሁን ሙዚየም ውስጥ እና ነጭ ድባብ ጥላ አለ ለክብር የሰጡት ነው። ሁለቱም በሙዝየም ውስጥ ይገኛሉ።






**ምስል 34፡ ባንዲራ (ሰንደቅ አላማ) እና ነጭ ድባብ (10/02/2013) በሳምራዊት**

**የቆዳ ሳጥን ፡** ሳጥኑ በቤተመንግሥት እንደ ካዝና ሆኖ የወርቅ፣ የብር ማከማቻ የነበረ ትልቅ ከአንድ ወጥ የበሬ ቆዳ የተሰራ ሻንጣ በሶስት ቁልፎች ይቆለፍ የነበረ ሲሆን ከቦታ ቦታ ሲሄዱ በቀላሉ ይዘውት ይጓዙ ነበር፡፡



**ምስል 35፡ የቆዳ ሳጥን (10/02/2013) በሳምራዊት**

**የእቴጌ ጣይቱ አልጋ፣** የጠፈር ጥንታዊ አልጋ አለ፡፡



**ምስል 36፡ የእቴጌ ጣይቱ አልጋ (10/02/2013) በሳምራዊት**

***መጠጫዎች፡-*** ከቀንድ፣ ከእንጨት እና ከቀርከሃ የተሰሩ በርካታ የጠጅና ጠላ መጠጫ ዋንጫዎች አሉ፡፡ ንጉሱ ግብር ሲያስገቡ የሚጠጡባቸው 18 የሚሆኑ መጠጫዎች አሉ፡፡



**ምስል 37፡ ከቀንድ ከቀርክሀ የተሰሩ የጠጅ እና የጠላ መጠጫዎች (10/02/2013) በሳምራዊት**

**ከበሮ፡-** በ1880 ዓ.ም በስጦታ ከዐፄ ሚኒልክ የተሰጠ፤ ከብር፣ ከቆዳና ከእንጨት የተሰራ ከበሮ ነው፡፡ "ከአፉ ሰፋ ከስሩ ጠበብ ያለ ቅርጽ ያለውና አፍና ስሩ ላይ የሚወጠር እንዲሁም በእጅ ሲመቱት ድምፅ የሚሰጥ የማህሌት መሳሪያ ነው፡፡" /የአማርኛ መዝገበ ቃላት 1993፣375/፡፡

"የከበሮ ትእምርታዊ ትርጓሜ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን ሰፊና ጠባብ አፍ እንዲኖረው ተደርጎ የተሰራ የሰፊው አፍ ትርጓሜ በሁሉም ሥፍራ ያለውንና የሚኖረውን እግዚያብሔር፤ ጠባቡ አፍ ደሞ እግዚያብሔር ወልድ በጠባብ ደረት በአጭር ቁመት መወሰኑን እንዲሁም የከበሮው ሁለቱ አፎች የተያያዙበት ጨርቅ ወይም ጠፈር አይሁድ እየሱስ ክርስቶስን

በገረፉበት ወቅት የታየውን አጥንቱን፣ ማንገቻው ደግሞ በአንገቱ ገመድ አስረው ያንገላቱትን እንግልት ያሳያል፡፡”




**ምስል 38፡ ከበሮ (10/02/2013) በሳምራዊት**

**ጥላ፡-** ጥላዎቹ ጥንታዊነታቸውን የጠበቁ ሲሆኑ ጫፍና ጫፍ ላይ ያለው ጌጥ አሰራር የተለየ ነው፡፡ የእቴጌ ጣይቱ ጥላ የሚባሉት ጥላዎች እሳቸው ሲመጡ የሚዘረጋላቸው ነው፡፡ የዐፄ ሚኒልክ ጥላም ላይ የቤተክርስቲያኑ ዲዛይን፣ 5 ኮከቦች፣ ከላይ የንጉሱ ዘውድ፣ የድል ሀውልቶች፣ ሀረጎች አሉት፡፡ ከሀር ነው የተሰሩ፣ በወርቅ የተለበጡ ጌጠኛ ጥላዎች ናቸው፡፡ የንግሥት ዘውዲቱ የአክብሮት ጥላዎችም ይገኛሉ፡፡



**ምስል 39 ፡ ጥላዎች (10/02/2013) በሳምራዊት**

**ጋኖች**፡- ከ1879 ዓ.ም ጀምሮ የነበሩ፣ ከሸክላ የተሰሩ ናቸው፡፡ አገልግሎቱም መስከረም አንድ እና ታህሳስ አንድ የቅዱስ ራጉኤልና የኤልያስን ዝክር በአል አስመልክቶ ጠጅ ይጠመቅበት ነበር፡፡



**ምስል 40፡ ጋኖች** (10/02/2013) **በሳምራዊት**

**የፊት መስተዋት፡** ከእንግሊዝ ሀገር ከንግስት ቪክቶሪያ ለአጼ ሚኒሊክ በ1875 ዓ.ም የተሠጠ የፊት መስተዋት ሆኖ አጼ ሚኒሊክ በቤተ መንግስታቸው ውስጥ ካባቸውን፣ ልብሳቸውን፣ ዘውዳቸውን፣ ሲለብሱ ይመለከቱበት የነበረ፤ መደቡ ወርቅ ቅብ የሆነ የፊት መስታወት ነው፡፡



**ምስል 41፡ የፊት መስተዋት** (10/02/2013) **በሳምራዊት**

**አገልግል** በብር የተለበጠ ውስጡ አክርማ የሆነ ከቆዳ የተለጎመ ነው፡፡ አገልግሎቱ የጣይቱ የመዋቢያ የጌጣ ጌጥ እቃዎች ማስቀመጫ ነበር፡፡ አሰራሩ የመኳንንት አሰራር ነው ከነ ክብሩ የተቀመጠ ነው፡፡



**ምስል 42፡ አገልግል (10/02/2013) በሳምራዊት**

**ድባብ፡** ምኒሊክ በ1877 ዓ.ም ላይ የቅዱስ ራጉኤልን ቤተክርስቲያን ሲያስመርቁ ታቦቱ ብቻ እንዲጠለልበት የተሰራ ድባብ፤ በሁለት ከፋ ጨርቅ ላይ ዙርያውን ከጨርቅ፣ ከብር እና ከነሐስ የተሰራ ድባብ አለ፡፡



**ምስል 43፡ የቅዱስ ራጉኤል ታቦት ድባብ (10/02/2013) በሳምራዊት**

**ለምዶች**፡ በእጅ የተሰራ ነው ጫፍ ላይ ንጹህ ብሮች አሉ፡፡ የንጉሱ አማካሪ ጋሽ አሻግሬ ቃል አቀባዩ አፈ ንጉስ ወደ ቤተ መንግስት ሲገቡ እና ታቦታት ሲወጡ የሚለብሱት ለምድ የክብር ልብስ ነው፡፡ ታቦት ሲወጣ ከውስጥ ቀሚስ ለብሰው ከላይ የሚደርቡት ካባ አለ 5 የሚሆኑ ጌጦች ያሉት ደግሞ ላንቃ ይባላል፡፡ ታቦት የሚሸከሙት ሁለት ናቸው እነሱ የሚለብሱት ልብስ የእጅ ስራ ነው፡፡ የጸሀፊ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ ወልደ አረጋይ የቤተክርስቲያኑ አስተዳደር ስለነበሩ ይለብሱት የነበረ ለምድ፤ በቤተመንግሥት በእጅ የተጠለፈ የፈረሰኞች ለምድ፣ በእጅ የተጠለፈ በቤተመንግሥቱ መኳንንት እና ሚኒስትሮች ሱሪዎችም አሉ፡፡



ምስል 44፡ የመኳንንት ለምዶች (10/02/2013) በሳምራዊት

**ኩስኩስት (የእጅ መታጠቢያ ጆግና ሰሀን)** ከነሀስ የተሰራ፣ በቅዳሴ ሰዓት ካህናት ለቅዱስ ቁርባን ሲዘጋጁ የሚታጠቡበት የእጅ መታጠቢያ አለ፡፡



ምስል 45፡ ኩስኩስት የእጅ መታጠቢያ ጆግ እና ሰሀን/ (10/02/2013) በሳምራዊት

**የሻማ ማብሪያዎች፡-** በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ፣የተለያዩ አይነት የሻማ ማብሪያዎች



ምስል 46፡ ሻማ ማብሪያዎች(10/02/2013) በሳምራዊት

**የጦር መሳሪያዎች**፡ ኢትዮጵያውያን በ1888 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት ወቅት ከጣሊያን አስማርከው ያመጡት መሳሪያዎች ናቸው፡፡

***መቋሚያ፡-*** ከላይ ጭንቅላታቸው ከእንስሳት ቀንድ፣ ከታች በእንጨት ለቤተ ክርስቲያኑ መገልገያ የተሰሩ ጥንታዊያን መቋምያዎች ናቸው፡፡ ነጭ መቋምያው ከዝሆን ጥርስ የተሰራ ሲሆን በግዜው ዐፄ ሚኒሊክ በዚህ ቦታ ከ300 በላይ ካህናት መዘምራን እና ዲያቆናት እንደነበሯዋቸው የሚነገር ሲሆን አጠቃላይም ከ300 በላይ ከቀንድና ከዝሆን ጥርስ የተሰሩ መቋምያዎች ይገኛሉ፡፡ የቅኔ ማህሌቱ አገልግሎትም ዙርያውን እንደነበረ ይነገራል፡፡

**ዘውድ፡** ከነሐስ የተሰራ ሲሆን ዐፄ ምኒሊክ ሁለት ዘውድ ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱም ሁለት ዘውዶች ነበሯቸው፡፡ ከ1875 ዓ.ም ጀመሮ የተለያዩ ታሪካዊ በዓላት ላይ ያደርጉት እንደነበር ይነገራል፡፡

**ገበጣ፡** ገበጣዎቹ በቤተመንሥት ሲጫወቱበት የነበረ፣ ይህም በሁለተኛው ጦርነት በ1933 ዓ.ም ከጣልያኖች የተማረከ ነው፡፡

***መጋረጃ፡*** በ 1878 ዓ.ም ዐፄ ምኒሊክ ቤተክርስትያኑን ሲያስመርቁ ከሀገር ውስጥም ከሀገር ውጭም የተለያዩ ታላላቅ ሰዎችን ጋብዘው ነበር፡፡ ከነዚህም ውስጥ የጅማው ንጉስ አባ ጅፋር አንዱ የክብር እንግዳ ሲሆኑ ንጉሱ በበቅሎአቸው ጭነውት የመጡት በጣም ትልቅ፣ ቤተክርስትያኑን ስምንት መአዘን ዙርያውን የሚያለብስ ትልቅ መጋረጃ ነበር ይዘው የመጡት፡፡ በግዜው የቤተክርስትያኑ በሮች እና መስኮቶች መጋረጃውን ለብሰው ነበር፡፡

***መቁረብት***፡ ለቅባ ቅዱስ ማቅረቢያ ይገለገሉበት ነበር፡፡ ***ቀጸላ***፡ ማለት ታቦታት ሲወጡ የሚለብሱት ነው፡፡ ***ቃጭሎች*** ከቤተልሄም ወደ መቅደስ ታቦት ሲወጣ ለተለያዩ አገልግሎት ይውል ነበር፡፡ **ቅብአ ሜሮን፡-**ቅብአ ቅዱሱን ለክርስትና እና የታመመ ሰው ሲኖር በዚህ ይቀባ ነበር፡፡***የዕጣን ማስቀመጫ፡-*** ከብር የተሠሩ፣ ለዕጣኑ ክብር ሲባል በከበረ ዕቃ ይቀመጣል፡፡ **ጽናጽል፡-** ከነሐስና ከብር የተሠሩ ናቸው፡፡ ጥሩምባ፣ ጦር፣ ጅራፍ፣ በምድር ቤቱ ውስጥ በተለያየ ግዜ ለቤተክርስትያኗ የተበረከቱ ንዋየ ቅዱሳት፣ የጦር መሣሪያዎች፣ የብራና መጽሐፍትና የመሳሰሉ/ት የተለያዩ ቅርሶች ይገኛሉ፡፡

(ዲያቆን ዮሃንስ ወልደጊዮርጊስ 09/02/2013፣ ርእሰ ደብር አጋፋሪ ሰለሞን ጌታነህ 10/02/2013፣ ዲያቆን ኃይሉ ጌታነህ፡ 10/2/2013 ቃለ መጠይቅ)፡፡ (በሳምራዊት 10/02/2013)

## 5.3. ከእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ወደ መርካቶ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን የተዘዋወሩ ቁሳዊ ባህሎች

በመርካቶ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ ለመፈጸም የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳዊ ባህሎች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

**ወንጌል**፡ 4ቱ ወንጌል ይባላል፡፡ "ወንጌል ዘወርቅ ይባላል" በወርቅ የተለበጠ ነው፡፡ ክዳኑ በወርቅ የተሠራ ነው፡፡ በክብረ በዐላት ቀን፣ በቅዳሴ ሰዓት የሚነበብ የነበረ ሲሆን አሁን ግን ሌሎች የታተሙ ወንጌሎች ስላሉ እነሱ ናቸው የሚነበቡት፣ በቅርስነት ተቀምጧል፡፡ ከብራና ነው የተሠራው፡፡ መስከረም 1 ቀን የራጉኤል በዐል ሲነግሥ ወንጌሉ ይወጣ እና ይነበባል፡፡ አንድምታ ትርጓሜ ያለው ነው፤ ኹሉም ወንጌል ቃል አንድ ነው፤ ከብራና የተሠራ ነው፡፡ ሌላው ወንጌሎቹ በውስጣቸው ሥዕላት አሏቸው፡፡ ጥልስም አለው፣ መጽኀፍን ለማክበር የሚሠራ በቀለማት ከብር ተውቦ ይሠራል፡፡



**ምስል 47፡ ወንጌል (03/02/2013) በሳምራዊት**

**ዳዊት**፡- የዐፄ ምኒልክ አባት ሀይለመለኮት የሚደገሙበት ዳዊት አለ፡፡ ዳዊቱ ውስጥ በተጨማሪ ያሉት ቅዳሴ፣ ኪዳን፣ ትምህርተ ህቡአት፣ መልከአ መልኮች፣ በየአይነቱ መልክአ ማርያም፣ መልክአ ኢየሱስ፣ ውዳሴ ማርያም፣ አንቀጸ ብርሃን ያሉት ሲሆን የተጻፈው በብእር ነው፡፡ ወረቀቱ ብራና ነው ወፍራምና ጠንካራ ነው አይቀደድም፡፡ የድሮ አባቶች ሀይማኖታዊ መጽሀፍትን እያነበቡ እየደገሙ ነበረ ሀገሪቷን የሚያስተዳድሩት፡፡ ተአምረ ማርያም 400 ተአምር በውስጡ ያለው ነው፡፡ መቅድም አለው ከብራና ነው የተሰራው ቤተክርስቲያን ጠዋት

ይነበባል በውስጡም የተለያዩ ቅዱሳን ስእሎች አሉት። በውስጡ ያሉት ስእላቶች የሚገለልጹት የማርያም ስደትን፣ ቅዱስ ገብርኤል ሲያበስራት፣ ፋኑኤል ለማርያም ምግብ ይዞላት ሲመጣ፣ የጊዮርጊስ፣ የማርያም የተለያዩ ስእላቶች አሉት። ስእላቶቹ ከተለያዩ እጽዋቶች በተለያዩ ቀለማት እየበጠበጡ ነው የሚስሉት ከፍየል ቆዳ ነው የተሰራው በውስጡ 296 ገጾች አሉት። ትልቅ መጽሀፍም ነው።

***ታሪክ ነገሥት፡-*** የነገሥታት ታሪክን የያዘ መጽሐፍ ነው። ከብራና የተጻፈ ነው ቀለሙ ከተለያየ ዕፅዋት ነው የሚሠራው፤ ከፍየል ቆዳ ነው የሚሠራው፣ ኹሉም መጽሐፎች የተጻፉት በግዕዝ ነው፣ የብራና መጽሐፎች ናቸው፣ አብዛኛውን መጽሐፍ የጻፉት ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ናቸው። መጽሐፎቹን ሲጽፉ፣ ለምሳሌ የመስከረምን ጽፈው ሲጨርሱ የጥቅምትን ከመጻፋቸው በፊት አባቶቹ በየምዕራፍ ሲከፋፍሉ የሚጠቀሙት በጠልስም አድርገው የተለያዩ ቅዱሳን ሥዕላት ይሥላሉ እና ወደ ጥቅምት ጽሑፍ የሚቀጥሉት።

**መልክአ ማርያም፡-** በብራና የተሠራ አለ፤ በረጅሙ በፍየል ቆዳ የተሰራ በቀለማት በጠልስም እየተነከረ የተሠራ ነው። በወቅቱ ማተሚያ ቤት ስላልነበረ ነው በዚህ መልኩ ይጻፍ የነበረው መልከኣዎቹ ከአንዱ ወጥ የኾነ የፍየል ቆዳ ይሠሩ ነበር። **ስንክሳር፡-** ከመስከረም፣ የካቲት፣ ከመጋቢት እስከ ጳጉሜ ይነበባል። በጣም ትልቅ ስለኾነ በኹለት መጻሕፍት ተከፍሎ ነው የተጻፈው ጠዋት፣ ጠዋት ይነበባል። የተሠራው ከፍየል ቆዳ ነው። **ጾመ ድጓ**፡ የዜማ መጀመሪያ ማለት ነው ዜማ ሲማሩ መጀመሪያ ይህን ነው የሚማሩት። የሚቆመው ደግሞ በጾመ ኹዳዴ ጊዜ ነው። ዜማው የሚዜመው በነዚህ ምልክት ነው። ትንንሾቹ የዜማ ምልክት ናቸው። መጽሐፉ ላይ ያለው በግዕዝ የተጻፈ ነው፤ የብራና መጽሐፍ ነው። **ሃይማኖተ አበው**፡ የሚል መጽሐፍ አለ። የቅዱሳን አባቶችን ሃይማኖታቸውን የሚናገር መጽሐፍ ነው። የእግዚአብሔርን ዋስትና የመሰከሩበት ነው። **ፍትሐ ነገሥት፡-** የነገሥታት ፍርድ የሚፈርዱበት የነበረ ነው። **መጽሐፈ መቃብያን፡-** የመፅሀፍ ቅዱስ ስሞችን ስያሜ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው። **መጽሐፈ ቄዳር**፡-አንድ ሰው ኀጢአት ሠርቶ ንስሐ ከገባ በኋላ ኀጢአቱን እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው የሚነበብ መጽሐፍ ነው። **መጽሐፈ ተክሊል**፡-ኹለት ሰዎች ሲጋቡ የሚነበብ ነው። **መጽሀፈ ቀንዲል**፡-አንድ ሰው ሲታመም የሚነበብለት መጽሐፍ ነው። ከዚያም ጥምቀት ይጠመቃል። **መጽሐፈ ነገሥት፡-** የነገሥታት መጽሐፍ ለግዕዝ ነው የተጻፈው። **ውዳሴ አምላክ**፡ የአምላክ ምስጋና የሚነበብበት ነው። **ግብረ ሐዋርያት**፡ ስለ ሐዋርያት ሥራ የሚያወራ ነው።

**መጽሐፈ ግንዘት፡** ሰው ሲሞት የሚነበብ መጽሐፍ ነው፡፡ **መጽሐፈ ጨዋታ፡-** አለቃ ዘነብ የሚባሉ ሊቅ ናቸው የጻፉት፡፡



**ምስል 48፡ ለሥርዓተ አምልኮ የሚያገለግሉ የተለያዩ የብራና መጻሕፍት (03/02/2013) በሳምራዊት**

በአጠቃላይ እጅግ ብዙ የተለያዩ መጻሕፍት በዚህ ቦታ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ በጥቂቱ ድርሳነ ሚካኤል፣ መጽሐፈ ኤርምያስ፣ መጽሐፈ ኦሪት፣ መዝሙረ ዳዊት፣ የቅዳሴ መጽሐፍ፤ አርጋኖን፤ ወንጌል፣ ድጓ፣ ትንቢተ ኢሳይያስ የሚገኙ ሲሆን ሁሉም ከፍየል ቆዳ የተሠሩ የብራና መጻሕፍት ናቸው፡፡

**ማኅደሮች፡-** የእያንዳንዱ የዳዊት፣ የወንጌል፣ ስንክሳር፣ ድጓ ወዘተ የመጻሕፍት ኹሉ መያዣ ነው እንዳይበላሽ ይጠቅማል፤ የሚሠራው ከቆዳ ነው፡፡



**ምስል 49፡ ማኅደሮች (03/02/2013) በሳምራዊት**

**ገበታ፡-** መጽሐፎቹን መሸፈኛ ከጣውላ የተሠራ ነው፡፡



**ምስል 50፡ ገበታ (03/02/2013) በሳምራዊት**

**ማኅተም፡-**ዐፄ ምኒልክ ይገለገሉበት የነበረ ማኅተም ከነ መርገጫው አለ፡፡






**ምስል 51፡ ማኅተም እና መርገጫ (03/02/2013) በሳምራዊት**

**ዘውዶች፡** የዐፄ ምኒልክ፣ የእቴጌ ጣይቱ፣ የንግሥት ዘውዲቱ፣ የኃይለ ሥላሴ በበዐላት ግዜ የክብር ዘውዶች አድርገው መድረክ ላይ ይወጡ ነበር፡፡



**ምስል 52፡ ዘውዶች (03/02/2013) በሳምራዊት**

**የተለያዩ መስቀሎች፡-** ከብር፣ ከነሐስ፣ ከወርቅ ከእብነ በረድ የተሠሩ ትላልቅ ከታቦቱ ጋር የሚወጡ እና የእጅ  መስቀሎች አሉ፡፡





**ምስል 53፡ የተለያዩ መሥቀሎች (03/02/2013) በሳምራዊት**

**ፅዋ፡-** የቅዱስ ቁርባን ማቅረቢያ ከወርቅ የተሰራ ነው፡፡ **ሰሀን**፡ አገልግሎቱ ስጋ ወደሙ ማቅረቢያ ሲሆን ከነሀስ የተሰራ ነው፡፡





**ምስል 54፡ ፅዋ (03/02/2013)** **ምስል 55፡ ሰሀን (03/02/2013) በሳምራዊት**

**አልባሳት**፡- የካህናትና የዲያቆናት ከወርቅ፣ ከብር ከነሐስ የተሰሩ ልብሶች አሉ፡፡ ለቅዳሴ እና ታቦት ሲወጣ ለክብረ በዓላት ይለብሷቸው ነበር፡፡ የዐፄ ሚኒልክ እና የእቴጌ ጣይቱ አልባሳትም እና የታቦቱን መሸፈኛ መጎናጸፊያም አለ፡፡




**ምስል 56፡ አልባሳት (03/02/2013) በሳምራዊት**

**መሶበ ወርቅ** እቴጌ ጣይቱ የሰሩት መሶበ ወርቅ አለ፡፡ ከሰበዝ ከስንደዶ የተሰራ ሲሆን የጌጣ ጌጦቻቸው ማስቀመጫ ነው፡፡



**ምስል 57፡ መሶበ ወርቅ (03/02/2013) በሳምራዊት**

ጋሻ፡- በጦርነት ወቅት የሚይዙት ነበረ፡፡




**ምስል 58፡ ጋሻዎች (03/02/2013) በሳምራዊት**

**አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ጥላ፡** መጋቢ ብርሃን ቅዱስ ራጉኤል የበትርህን ሀይል ለአንተ እልክልሀለሁ የሚል ጽሁፍ ያለው ትልቅ ጥላ ያለ ሲሆን፣ ታቦት ሲወጣ ለጥምቀት በዓል ተዘርግቶ ከታቦቱ በፊት ይዘውት ይወጣሉ፡፡

**ጥላዎች፡-** የተለያዩ ጥላዎች  ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሐስ እና ከሐር ጨርቅ የተሰሩ ሲሆን መያዣው ብረት ነው፡፡ አገልግሎታቸው ለበአላት ጊዜ ታቦት ይጠለልባቸዋል፡፡





**ምስል 59፡ ጥላዎች (03/02/2013) በሳምራዊት**

**ወንበር፡-** አለቃ ተድላ የሚቀመጡበት ከእንጨት የተሰራ ሶፋ የሚመስል ምቹ ወንበር ነው፡፡



**ምስል 60፡ ወንበር (03/02/2013) በሳምራዊት**

**መሶብ፡-**ትንሽ መሶብ ከበሶ የተሰራ ጭኮ የሚይዙበት ወደ ክፍለ ሀገር ሲሄዱ ለምግብነት የሚገለገሉበት ነው፡፡



**ምስል 61፡ መሶብ (03/02/2013) በሳምራዊት**

**የብር አትኖስ፡-** አገልግሎቱ የተለያዩ መጽሀፍት ማንበቢያ አለ ከላይ ጨርቅ ይለብሳል፡፡

**የወርቅ ቅብ ከበሮ፡** የቅኔ ማህሌት ጊዜ የሚወጣ ነው፡፡ የወርቅ ከበሮ ከስር በብረት ከላይ ከሸራ የተሰራ ነው ማስቀመጫ አለው፡፡



**ምስል 62፡ የብር አትኖስ እና የወርቅ ቅብ ከበሮ (03/02/2013) በሳምራዊት**

**የብር ቅብ ከበሮ፡-** የቅኔ ማህሌት ጊዜ የሚወጣ ነው፡፡ የብር ከበሮ ከስር በብረት ከላይ ከሸራ የተሰራ ነው ማስቀመጫ አለው፡፡



**ምስል 63፡ የብር ቅብ ከበሮ(03/02/2013) በሳምራዊት**

**የእጅ ማስታጠቢያ፡** እና ውሃ ማቅረቢያ፣ **ፅና፡-** ማለት የእጣን ማጠኛዎች ናቸው፡፡ **ፅናጽል፡** የወርቅ ቅብ ፅናጽል አለ፡፡ **የአለቃው መቋሚያ** የቀድሞው የደብሩ አስተዳዳሪ አለቃ ተድላ ወልደ ጻዲቅ ቅኔ ማህሌት ሲቆሙ የሚይዙት ከላይ በወርቅ ከታችኛው በእንጨት የተሰራ ነው፡ (አባ ባዬ ሲሻው፡ 03/02/2013 ቃለ መጠይቅ) (ፎቶ በሳምራዊት 03/02/2013)

በብዛት ከእንጦጦው ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ጥንታዊ ቁሶች ወደ መርካቶዉ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን የተወሰዱት ቅርሶች አግባብ ባለዉ መንገድ ለትውልዱ በማስተዋወቅ ታሪክን የማስተላለፍ ነገር ትኩረት አልተሰጠውም አብዛኛው ለጎብኚዎች ክፍት ሳይሆኑ ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም በ1993 ዓ.ም ከመርካቶ ተሰርቆ ወደ ፈረንሳይ ሄዶ ወደ እንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል የተመለሰ ‹‹ድርሳነ ራጉዔል ዘ-ሃገረ እንጦጦ›› በሚል የተፃፈ የብራና ድርሳን አለ፡፡

ከእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወደ መርካቶ ቅዱስ ራጉኤል የተዘዋወሩ ቁሳዊ ባህሎች የሚገኙበት ሙዚየም በአሁኑ ሰዓት በተደራጀ ሁኔታ እየተንቀሳቀሰ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ታሪክ እንዳይነገር ሆኗል፡፡

**የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወ ኤልያስ ቤተክርስቲያን አሁን ላይ**

የቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ህንፃ ቤተክርስቲያን ያሰሩት የዐፄ ምኒልክ መሞት ተያይዞ ወደ ቤተክርስቲያኑ ለአምልኮት የሚመላለስ መእመን መቀነስ፣ የቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ተጨማሪ ህንፃ ቤተክርስቲያን በመርካቶ መገንባቱ፣ የቤተክርስቲያኑ አገልግሎት በአንድ ወቅት ተቋርጦ የአብነት ትምህርት ቤቱ መዘጋቱ፣ በቅርቡ የተከሰቱ ከቤተክርስቲያኑ ርስት ወሰን ጋር የተያያዙ ችግሮች፣ ታሪክን በትክክል የማስተላለፍ ግድፈቶች እና በፅሑፍ መዝግቦ የማስቀረት ችግሮች፤ ለዚህም አንዱ ምክንያት በቤተክርስቲያኑ ስር ተመዝግበዉ የሚገኙ ቅርሶች ብዙዎቹ ወደ መርካቶ ራጉኤል መወሰዳቸዉ፣ የተወሰኑት ቅርሶች ደግሞ በግዚያዊ ሙዚየም መቆለፍ እና የመሳሰሉት ምክንያቶች ቤተክርስቲያኑ ዳግም በፍጥነት እንዳያንሰራራ አድርጎታል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## 6. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ

### 6.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሣው በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን ተረኮች እና ቁሣዊ ባህሎች ለቤተክርስቲያኑና ለቤተክርስቲያን ህይወት የሚኖራቸውን ፋይዳ መመርመርን ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ የጽሁፍ መረጃዎችን ማንበብ ቃለ መጠይቅን እና ምልከታን በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

መረጃዎቹን በጽሁፍ ማስታወሻ፣ በቪዲዮ ካሜራ፣ በፎቶ ግራፍ እና በመቅረጸ ድምፅ አማካይነት ተቀርጸዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችንም ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በጥናቱ ተዛማጅነት ያላቸው ጥናቶቹ ከስነ ፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተሰሩ ናቸው፡፡ በእነዚህም ጥናቶች የታዩ ደካማና ጠንካራ ጎኖች ተለይተዋል፡፡ ጥናቱ በቤተክርስቲያኑ ላይ የሚተረኩ ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ መረጃዎቹን መሰረት በማድረግ ከተሰጡት ትንታኔዎች በመነሳት የቤተክርስቲያኑን አመሰራረት በማን እና እንዴት እንደተመሰረተ የሚገልጹ ናቸው፡፡

ዐፄ ምኒልክ በዝዋይ ሀይቅ ውስጥ በነበሩ መነኩሴ በተነገራቸው ራዕይ መሰረት ወደ ዐፄ ዳዊት ዋሻ በመምጣት ቤተክርስቲያኑን መመስረታቸው የሚተርከው ተረክ አንዱ ነው፡፡ ተረኮቹንም ቤተክርስቲያኗ ጥንት የነበሯት ተረኮች ምእመናኑ በቤተክርስቲያኗ ያላቸው አመለካከት የተደረገላቸው ተአምራት፣ የቤተክርስቲያኑን ጥንታዊነት፣ የቦታውን ክብር ከፍ ከፍ የሚያደርጉ የስፍራውን ሉዓላዊነት የሚያስጠብቁ የቤተክርስቲያኑን ቅርስ የሚዘክሩ ከራእይ፣ ከተዓምር በፈውስ መልክ ንግር፣ትንቢት ጋር ተያይዞ የሚነገሩ ተረኮች በሚሉ ርዕሶች ተተንትኗል፡፡

በጥናቱ የቤተክርስቲያኑ ጠባቂ ነብር እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ይህም አማኒያኑን እና የአካባቢው ነዋሪዎች ለቤተክርስቲያኑ ክብር እንዲሰጡ፣ ንብረት እንዲጠብቁ፣ ለሕጉ እንዲታዘዙ የማድረግ ተግባር አለው፡፡ በክርስትና ህይወት የማነጽና የማጠናከር በዋሻውና በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ ያሉትን ቁሶች እና በሚነገሩት ተረኮች አማካኝነት በቤተክርስቲያኑ አስተምሮ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሳይሸራረፍ ተጠብቆ እንዲቆይ የሚያደርግ ተግባራት አላቸው፡፡

እንዲሁም ስለ ቤተክርስቲያኑ የተፃፈ መዝገብ ባይገኝም ተረኮች ስለ ቤተክርስቲያኑ ይዘው ለማቆየት በማብቃቱ፣ ተረኮቹ ለአንድ ማህበረሰብ መልሶ መቋቋም ወይም ምስረታ ያላቸውን ፋይዳ የሚያሳይ ነው። የአመሰራረት ተረኮቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያለው ተያያዥነት እንዳለው በማሳወቅና የስፍራውን ቅድስና በማጉላት በኩል ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው። እነዚህ ቁሶች መታየታቸው እና ተረኮቹ መተረካቸው ለአማኒያኑም ሆነ ምዕመኑ የቦታውን ቅድስና ተገንዝበው የቤተክርስቲያኑን ህግ፣ ሥርዓትና ክብር እንዲኖራቸው ያደርጋሉ።

ከዚህም በተጨማሪ የአካባቢው ነዋሪዎች እድገታቸው በቤተክርስቲያኑ መግነንና በታቦቱ መገለጥ ላይ መስርተው ታዛዥ እንዲሆኑ የማድረግ ፋይዳ ይኖረዋል። በፈውስ መልክ ከቀረቡት ተረኮች ውስጥ ያሉት ከተለያየ ስፍራ የመጡ እና በተለያየ መንገድ ከተለያዩ በሽታዎች የተፈወሱ ናቸው። እነዚህ ተረኮች መተረካቸው በምዕመናኑና በቤተክርስቲያኑ ላይ ያላቸው እምነት እንዲያጸኑ ያደርጋል። በተጨማሪም ተረኮቹ የተለያዩ የሃይማኖት ተከታዮች መካከል ያለውን ማኅበራዊ ትስስር ያስቀጥላሉ። የተፈወሱትም ሰዎች የገዳሙን ህግና ስርዓት አክብረው ይኖራሉ።

በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚተረኩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት የተገኘው ግኝት አማንያኑን በእምነቱ ለማጽናት፤ የአከባቢው ነዋሪዎች የአከባቢያቸውን እድገት ከቤተክርስቲያኑ ጋር በማያያዝ የቤተክርስቲያኑ ጠባቂ እንደሆኑ ለማድረግ፣ የእምነቱ ተከታዮች ሆኑ ሌሎች ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያኑ እንዲመጡ ለማድረግ፣ ማህበረሰቡ የቤተክርስቲያን ህግና ስርዓት እንዲጠብቁ ለማድረግ፣ የመንግሥት አካላት ቤተክርስቲያኑ የሚያስፈልገው ነገር ተባባሪ ለማድረግ ወዘተ ፋይዳ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል።

የሚጠናው ማህበረሰብ በተረኮቹ እና በቁሳዊ ባህሎች አማካኝነት ኬት መጥነቱን፣ ማንነቱን፣ እምነቱን፣ ባህሉን እና አስተሳሰቡን እንደሚገልጽ ከጥናቱ ማወቅ ይቻላል። በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ የሚነገሩ ትርክቶች እና ቁሳዊ ባህሎች በአጠቃላይ የጥበብ መገለጫ፣ የዘመን መንፈስ መፈተሻ፣ ማህበረሰቡን በእመነታቸው ለማፅናት፣ ታሪካዊነቱን ለመዘከር፣ የአከባቢያቸውን እድገት እንዲሁም የእምነቱ ተከታዮች ሆኑ ሌሎች ታዋቂ እና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያኑ እንዲመጡ በማድረግ ህግና ሥርዓቱ እንዲጠብቁ የማገዝ ፋይዳ አላቸው።

ኃይማኖታዊ ተረኮች ማጥናት የማህበረሰቡን ሥነልቦናዊ እና ማህበረሰባዊ አኗኗር ማንነት ለመረዳት ያስችላል።

በወቅቱ በመንፈሳዊ ጥበብ በኩል የተለያዩ ቅዱሳን መፃሕፍት፣ ነዋያተ ቅድሳት ነበሩ፡፡ በመንፈሳዊ ጥበብ በኩል ዘመናዊ መተየብያ ማሽን ባልነበረበት ወቅት በእጃቸው ብራና ፍቀው የጻፏቸው ቅዱሳን መጻሕፍትን ፣ ነዋያተ ቅድሳት መሰረት ያደረጉ የእደጥበብ እና ሥነጥበብ ሥራዎችን በመስራት ድንቅ የሚባሉ ኃይማኖታዊ ቁሳዊ ባህሎች ባለቤት መሆናቸውን፣

በአጠቃላይ እንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወኤልያስ ቤተክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች የእምነቱ ተከታዮች በእምነታቸው እንዲጸኑና እንዲጠነክሩ የማድረግ የአካባቢው ማህበረሰብ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እና የሌሎች እምነት ተከታዮች፣ የቤተክርስቲያኑ ጠባቂ፣ ተቆርቋሪ፣ ደጋፊ እንዲሆኑ የማድረግ ፋይዳ አላቸው፡፡ ቤተክርስቲያኑ አሁን ላይ ለሚከወነው የልማት እና የማስፋፋት ስራም የተቃና ይሆን ዘንድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

## 6.2. የይሁንታ ሀሳቦች

ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ ለማቅረብ የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡ የቤተክርስቲያኑን ንብረት ቁሳቁስ ለመንከባከብና ለጎብኚዎች ለማሳየት እንዲመች ቁሶቹ በሙዚየም ውስጥ መቀመጣቸው ይበል የሚያስብል ነው፡፡ ይሁን እንጂ መርካቶ ቅዱስ ራጉኤል ያለው ሙዚየሙ አገልግሎት እየሰጠ አይደለም፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ የቤተክርስቲያኑን ታሪክ ለማወቅ ለሚፈልጉ አካላት ሊሰጥ የሚችላቸውን መረጃዎች ለማድረስ እንዳይችል አድርጎታል፡፡

ከዚያ በተጨማሪ ቤተክርስቲያኑ ሊያገኘው የሚችለውን ገቢ እያጣ በመሆኑ በሙዚየሙ አገልግሎቱ የሚቀጥልበት ሁኔታ ቢመቻች፣ ሌላውና ዋነኛው ጉዳይ ረዥም ዓመት እንዳስቆጠረ የሚነገርለት ይህ ቤተክርስቲያን የቤተክርስቲያኑን ታሪክ በተጨባጭነት ለማወቅ የሚፈልጉ አካላት የመረጃ ውስንነት እንዳይፈጠር መረጃውን ሰንዶ በማስቀመጥ ቁሶቹንም እንዲሁ በተገቢው ሁኔታ በማኖር ላይ ቢሰራ፣ በመጨረሻም በቤተክርስቲያኑ ጥንታዊ እንደመሆኑ ብዙ መሰረተ ልማቶች ተጠናክረው ቢሰሩ የሚሉት ናቸው፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች


መሪማ መሐመድ። "በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት ገዳም አመሰራረትና በገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፍክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ 2009 ዓ.ም።

ምሕረት ተስፋዬ። "ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሠራረት ጋራ ተያያዥነት ያላቸው ተረኮችና ቁሳዊ ባህልች ጥናት"። አዱስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዱግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ 2003 ዓ.ም።

ሞገስ ጀንበር። "ከዲጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሠራረት ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና አምልኳዊ ሥርዓቶች"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣2003 ዓ.ም።

ሰለሞን ተሾመ። ፎክሎር ምንነቱ የጥናቱ ትኩረት አቅጣጫ። አዲስ አበባ፣ ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አሳታሚ ድርጅት። 2007 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጉለሌ ክ/ከተማ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት፣ በራሪ ጽሁፍ ፣2008 ዓ.ም።

ተስፋዬ ተገኝ። "በደብረ ነጎዴጓዴ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሠራረትና ቁሳዊ ባህል ጥናት"። አዱስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፍክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዱግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ 2003 ዓ.ም።

ተክለጻድቅ መኩሪያ። *ዐፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት*። አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1983ዓ.ም.።

ቴዎድሮስ ገብሬ። *በይነ ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ።* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2001ዓ.ም.።

ቴዎድሮስ ይበልጣል። "የደብረ ወርቅ ማርያም ገዳም አመሠራረት እና በገዲሚ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፍክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣2005 ዓ.ም።

አቤል አሰፋ። የጣራ ገዳም፣ ዋሻ እንድሪያስና ወይን ዋሻ ተክለ ሃይማኖት አብያተ ክርስቲያናትና በዙሪያቸው የሚነገሩ ተረኮች አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፍክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ 2008 ዓ.ም።

ወንድወሰን ሞላ። "በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ጥናት" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፍክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ 2007 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። *መጽሐፍ ቅደስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*። አዲሰ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተምያ ቤት፣ 2001 ዓ.ም.።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን። *ድርሳነ ራጉኤል፤ ግዕዝና አማርኛ*። አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ፣ 1991 ዓ.ም.።

የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል መጽሔት፣ ኹለተኛ እትም፣ ታህሳስ 2000 ዓ.ም።

________________ መጽሔት፣ ሐምሌ 1991 ዓ.ም።

________________ መጽሔት፣ ህዳር 2008 ዓ.ም።

ዮሴፍ በኪ። "የደብረሊባኖስ አቡነ ተክለሀይማኖት ገዳም ተረክ ጥናት"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲየኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፍክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዱግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ 2007 ዓ.ም።

ዳንኤል ክብረት። የቤተክርስቲያን መረጃዎች። አዲስ አበባ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ 2012 ዓ.ም

ፍቃደ አዘዘ። *የሥነ ቃል መምሪያ።* አዱስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1991 ዓ.ም።

ፍጹም ኩራባቸው። "የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህልች ጥናት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፍክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ፣ 2006 ዓ.ም።

ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፣ *ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ*፤ አዲስ አበባ፣ 2008 ዓ.ም

Barthes, R. and Lionel, D. "An Introduction to the Structural Analysis of Narrative." *NewLiterary History*. Vol. 6, no. 2 (1975): 237-272.

Bascom, William. "Four Functions of Folklore". *The Journal Of American Folklore*; Vol.67,No.266, PP. 333-349, Jan-Mar, 1965, pp. 320.

_____________. "The Form of Folklore Prose Narretives". *The Journal Of American Folklore.* Vol.78,No.302.

Bruner Jerome. Access of meaning. Harvard University press. USA 1990 Charls H. Long. Alpha The myth of creation. New York. 1963.

Dorson, Richard. Folklore and Folklife: An Introduction. London University Press of Kentucky; 1972.

Juan Gonzalez Nunez. Addis Ababa Through the Eyes of its Founders. A historical Guide to the Ethiopian Capital. 1996.

Oring, Elliot. *Folk Groups And Folk Genres*: *An Introduction*. Logan; Utah State University Press, 1986.

Sims, Martha C. And Martine Stephens. *Living Folklore: An Introduction To The Study of People And Their Tradition.* Logan; Utah State University Press, 2005.

http://www.cliffsnotes.com

## አባሪዎች

## ዐባሪ አንድ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገሉ ጥያቄዎች

## ከቤተክርስቲያኑ ስያሜ እና መመስረት ጋር በተያያዘ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዱ ጥያቄዎች

1. አመሰግናለሁ
2. ስምዎትን ማን ልበል?
3. የስራ ድርሻዎችን ቢነግሩኝ?
4. ቤተክርስቲያኑ መቼ ነው የተመሰረተው፣ የመሰረቱትስ እነማን ናቸው?
5. ቤተክርስቲያኑ ስያሜ እንዴት እንደተሰጠ የሚያውቁትን ቢነግሩኝ?
6. ቤተክርስቲያኑ ከመመስረቱ በፊት ህዝቡ እምነቱ ምን ነበር (በምን ነበር የሚያመልከው)?
7. ዐፄ ሚኒሊክ ወደዚህ ቤተክርስቲያን ሲመጡ ይዘዋቸው የመጡት ነገሮች እንዳሉ የሚነገሩ ተረኮች ካሉ የሚያውቁትን ቢነግሩኝ?
8. ስለ አካባቢው የሚነገሩ ትንቢቶች ካሉ ቢነግሩኝ?

## ክፍል ሁለት

## ቤተክርስቲያኑ ከመመስረቱ ጋራ በተያያዘ እና በጊዜ ሂደት የተፈጠሩ ክስተቶችን አስመልክቶ የሚተረኩትን ተረኮች ለመሰብሰብ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

9. በቤተክርስቲያኑ ምን ያህል ጽላቶች ናቸው ያሉት?
10. ለዚህ ቤተክርስቲያን መመስረት መነሻው ምንድን ነው?
11. ስለ ቤተክርስቲያኑ ስናነሳ ተያይዞ የሚነሳው ዐፄ ምኒልክ ናቸው? ከዚህ ጋራ ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ካሉ?
12. ከቤተክርስቲያኑ ውጪ ያለው ጠበል አመሰራረት
13. ወደ ቤተክርስቲያኑ የተለያዩ ቅዱሳንና ነገስታት ይመጡ እንደነበር ይነገራል ከመጡት መካከል የሚያውቁትን ቢነግሩኝ? እንዲሁም ተናገሯቸው ስለሚባሉ ትንቢቶች ካሉ?
14. የቤተክርስቲያኑ መተዳደሪያ ምንድነው? (የገቢ ምንጭ)
15. ይህንን ታሪካዊ ስፍራ ለማስተዋወቅ አሁን ላይ በገዳሟ እየተሰራ ያለ ነገር ምን ይመስላል?

## ክፍል ሦስት

## በቤተክርስቲያኑ ከሚገኙ ቁሶች ጋራ በተያያዘ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዱ ጥያቄዎች

1. በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ተመዝግበው ያሉትን ጥንታዊ ቁሶች (ንዋያተ ቅዱሳት) ቢነግሩኝ
2. ከቤተክርስቲያኑ መመስረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቁሶች አሉ?
3. ከተለያዩ ነገሥታት ለቤተክርስቲያኑ የተበረኩ ቅርሶች አሉ? ካሉ በዝርዝር ቢነግሩኝ?
4. ይሄንን ስፍራ ከሌሎች ቦታዎች ልዩ ሆኖ እንዲጠራ ያደርገዋል የሚሉት ቅርስ ካለ?
5. በቤተክርስቲያኑ ከሚገኙት መጽሐፍቶች አብዛኛውን ቦታ የሚይዙት የትኞቹ መጽሐፍት ናቸው?
6. በሙዚየሙ ያሉት ቅርሶች ውስጥ አሁን ላይ አገልግሎት የሚሰጡ ካሉ ቢነግሩኝ? ካሉስ መቼ መቼ ነው ለአገልግሎት የሚውሉት?
7. የብራና መጽሐፍት እዚህ ይዘጋጅ ነበር?
8. አሁን እዚህ የሚገኙት የብራና መጻሕፍቶች ከምን ቆዳ የተሰሩ ናቸው?
9. ጥንታዊ ቅርሶች ድሮ ከነበረው ይዞታቸው አንጻር አሁን ያሉበት ሁኔታ እንዴት ይገለጻሉ?

## ዐባሪ ሁለት የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ

### ሀ. የቁልፍ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | እድሜ | የሥራ ድርሻ | የሰጡት መረጃ ዐይነት | መረጃ የሰጡበት ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | መልአከ ሀይል ቆሞስ አባ ሳሙኤል አስፋው | ወ | 66 | የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ | ስለ ቤ/ክርስቲያኑ አመሰራረት ታሪክ፣ ቤተ ክርስቲያን ስለሚገኙ ቅርሶችና ስለሚነገሩ ተረኮች | በመቅረጸ ድምጽ እና በፎቶ |
| 2. | ርዕሰ ደብር አጋፋሪ ሰለሞን ጌታነህ | ወ | 78 | መሪጌታ | ስለ ቤተ ክርስቲያኑ አመሰራረትና ስለ ተበረከቱለት ስጦታዎች | በመቅረጸ ድምጽ እና በፎቶ |
| 3. | በትረ ትጉሀን ቀሲስ ክንፈ ሚካኤል ጥላሁን | ወ | 68 | የእቃቤት ኃላፊ | ስለ ፀበሉ አመሰራረትና ስለ ጥምቀት ስነ ስርዓት | በመቅረጸ ድምጽ እና በፎቶ |
| 4. | መምህር ወልደጊዮርጊስ ገብሬ | ወ | 83 | የአብነት ት/ቤት መምህር | በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ ስላሉ ተረኮች መረጃዎች በመስጠት | በቪዲዮና ካሜራ እና በመቅረጸ ድምጽ |
| 5. | አቶ ጥሩነህ ሀይሉ | ወ | 67 | የኢትዮቴሌኮም ሰራተኛ | መረጃ ሰጪ በማገናኘት | በመቅረጸ ድምጽ |
| 6. | ዲያቆን ሳሙኤል አስረስ | ወ | 36 | ሰባኪ ወንጌል (መምህር) | ስለ ጠበሉ ግቢ፣ በጠበሉ ግቢ ስላሉ ቅዱሳን | በመቅረጸ ድምጽ |
| 7. | ዲያቆን ዮሀንስ ወልደጊዮርጊስ | ወ | 39 | የሙዚየም አስጎብኚ | በቤተክርስቲያኑ እና በሙዚየሙ ዙሪያ ስላሉ ቁሶች እና ተረኮች መረጃዎች በመስጠት | በቪዲዮ ካሜራ፣ በመቅረጸ ድምጽ እና በፎቶ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8. | ህይወት ጌታቸው | ሴት | 44 | ፀሀፊ | ለወንድሟ ስለተደረገላት ተዓምር | በመቅረጸ ድምጽ |
| 9. | ብሩቱካን አዳነ | ሴት | 56 | የጠበል ግቢ ጠባቂ | ስለ ጠበሉ ግቢ መረጃ | በመቅረጸ ድምጽ |
| 10. | ለምለም ሀይሉ | ሴት | 52 | ነጋዴ | ለእራሷ እና ለልጇ ስለተደረገላት ተአምር | በመቅረጸ ድምጽ |
| 11. | አቶ መኩሪያ ሳህሉ | ወንድ | 68 | የቤተክርስቲያኑ አገልጋይ | ቤተክርስቲያኑ ያሳተመውን መጽሔት በመስጠት፣ ቁሶችና ተረኮች በመንገር | በመቅረጸ ድምጽ እና በፎቶ |
| 12. | ሊቀ ህሩያን ቃለፅድቅ ሀይሌ | ወ | 74 | መምህር | ስለ ቤተክርስቲያኑ አመሰራረት | በመቅረጸ ድምጽ |
| 13. | ዲያቆን ኃይሉ ጌታነህ | ወንድ | 38 | የሙዚየም አስጎብኚ | በቤተክርስቲያኑ እና በሙዚየሙ ዙሪያ ስላሉ ቁሶች እና ተረኮች መረጃዎች በመስጠት ፎቶ በማንሳት | በመቅረጸ ድምጽ በቪዲዮ ካሜራና በፎቶ |
| 14. | ተመስገን | ወንድ | 47 | የቤተክርስቲያኑ አገልጋይ | በቤተክርስቲያኑ ስለ ተፈወሱ ሰዎች መረጃ በመስጠት | በመቅረጸ ድምጽ |
| 15. | ቄስ ባዩ ሲሻው | ወንድ | 88 | የመርካቶ ቅ/ራጉኤል ቤ/ክ ሙዚየም ጠባቂ | በሙዚየሙ ዙሪያ ስላሉ ቁሶች እና መረጃዎች በመስጠት | በፎቶ እና በመቅረጸ ድምጽ |
| 16. | ቄስ በለጠ ምስጋናው | ወንድ | 68 | የቤተክርስቲያን አገልጋይ | ስመረጃዎች በመስጠት | በፎቶ እና በመቅረጸ ድምጽ |
| 17. | አቶ ተክሉ ማሞ | ወንድ | 72 | የቤተክርስቲያን አገልጋይ | መረጃዎች በመስጠት | በፎቶ እና በመቅረጸ ድምጽ |

## ዐባሪ ሦስት የመጀመርያዎቹ የደብሩ ካህናት

ርዕሰ አድባራት እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን በ1872 ዓ.ም በደብረ ሊባኖሱ እጨጌ ገብረ ሥላሴ ባራኪነት በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ መሠረቱ ቀጥሎ ሥራው ቀጥሎ ለ7 ዓመት ከተጓዘ በኋላ 1877 ዓ.ም ሕዳር 25 ቀን ቅዳሴ ቤቱ እንደተከበረ የዘመንና የታሪክ አቆጣጠር ታሪክ በአለቃ ዓይነ ዓለም ገብረ ማርያም በ1944 ዓ.ም የታተመው ያስረዳል። ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ በጊዜያቸው ከአሰባሰቧቸው ታላላቅ ሊቃውንት መካከል ለማስታወስ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-

1. ሊቀጠበብት ኃይሉ — የብሉይ መምህር የነበሩ
2. ሊቀጠበብት አወቀ — የብሉይ መምህር የነበሩ
3. አለቃ ገብረሐና — የአቋቋም መምህር የነበሩ
4. መምህር ወልደ ጊዮርጊስ — የሐዲስ መምህር የነበሩ
5. መምህር ገብረ መስቀል — የሐዲስ መምህር የነበሩ
6. መምህር ስሙዬ — የቅኔ መምህር የነበሩ
7. ሊቀጠበብት ድንቄ — የቅኔ መምህር የነበሩ
8. መምህር ብርሌ — የአቋቋም መምህር የነበሩ
9. መምህር ደባልቄ — የአቋቋም መምህር የነበሩ
10. መምህር ወልደ ሥላሴ — የአቋቋም መምህር የነበሩ
11. መምህር ወልደ ገብርኤል — የድጓ መምህር የነበሩ
12. መምህር ደስታ — የድጓ መምህር የነበሩ
13. መምህር አፈወርቅ ወልደ አማኑኤል — የድጓ መምህር የነበሩ
14. መምህር ዘለዓለም ደስታ — የቅኔ መምህር የነበሩ
15. የወሎዉንጉስ ሚካኤል — ቄሰ ገበዝ ሆነዉ ያገለግሉ ነበር

ባለፉት ዘመናት ይህን ታላቅ ደብር በመምምራት በጥንቱ አጠራር አለቃ ይባሉ የነበሩት፦

1. ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴ ወልደ አረጋይ

2. ነጋድራስ ጸምሩ ገብረ ሥላሴ

3. መልአከኃይል ገብረ ክርስቶስ ልቂ በኋላ /አፈንጉሥ/

4. መልአከኃይል ኃይለሥላሴ / በጠላት ዘመን/

5. መልአከኃይል ተድላ ወ/ጻድቅ ይገኙበታል። (የደ/ኃ/ቅ/ራ/መፅሔት ሁለተኛ እትም ታህሳስ 2000፡36)

# ዐባሪ አራት በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ስዕላት



ምስል፡ የአስራ ሁለቱ ኃዋርያት



ምስል፡ እየሱስ ክርስቶስ ሲቀበር እና ከሙታን ሲነሳ የሚያሳይ



ምስል፡ የማርያምን ሞት፣እርገት የሚያሳይ ምስል



ምስል፡ የመቅደስ በር




ምስል የእ/ቅ/ራጉኤል ወ/ኤልያስ ቤተክርስቲያን መግቢያ በር



ምስል የእ/ቅ/ራ/ወ/ኤ ቤተክርስቲያን ፀበል መፍለቂያ



ምስል፡ የእ/ቅ/ራ/ወ/ኤ ጸበል ቤት የምትገኝ ጸሎት ቤት



ምስል፡ የዐጼ ሚኒሊክ ቤተ መንግስት ፍርስራሽ

